“የኮሌጅ ቀን” ገጣሚያን ማህበረ ፖለቲካዊ አመለካከት እና ሒስ

በ

ገዛኸኝ ፀጋው

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር
ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ሰኔ፣ 2002 ዓ.ም.

"የኮሌጅ ቀን" ገጣሚያን ማህበረ ፖለቲካዊ አመለካከት እና ሒስ

በ

ገዛኸኝ ፀጋው

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር
ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ ፊርማ

የውጭ ፈታኝ ፊርማ

የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ADDIS ABABA UNIVERSITY
ቋ.ጥ.ተ. ቤተ መጻሕፍት
ILS LIBRARY

"የኮሌጅ ቀን" ገጣሚያን ማህበረ ፖለቲካዊ አመለካከት እና ሒስ

በ

ገዛኸኝ ፀጋው

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር
ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

አማካሪ

ዮናስ አድማሱ (ዶ/ር)

ሰኔ፣ 2002 ዓ.ም.

አበርክቶ

በዚች ዓለም ያለአንዳች ጥቅም ፍለጋ፣ ያለምንም ራስ ወዳድነት ልባዊ ፍቅሯን የለገሰችኝ አንዲት ምስኪን እንስት አውቃለሁ - እማዬን፡፡

እማ፣ ሀቀኛና መንፈስ ጠንካራ እንድሆን በነቢብሽም በገቢርሽም እየባተልሽ ማሳደግሽ አልበቃ ብሎሽ፣ በመጨረሻዋ ደቂቃሽም ባመላከትሽኝ ጉዳና እንድገፋበት በቃልሽ ልታፀኝኚ ብትቃትችም፣ እኔ ግን ልቡና ቅስሙ የተሰበረ ከርታታ እንደሆንኩ ይሰማኛልና የየዕለት የውስጥ ሀዘኔን ባለማየትሽ እንዴት ታደልሽ !?

ለግብርሽ እና ለፍቅሬ ባይመጥንም፣ ይህን ጥናታዊ ሥራ ለአንቺ ለእናቴ ለወይዘሮ አልማዝ አድማሱ መታሰቢያሽ እንዲሆን አበርክቼዋለሁ እና እባክሽ ተቀበይኝ?

ምስጋና

በመጀመሪያ የኔን ጠያቂ ባህሪ እየሞገቱ፣ ይህን ጥናት አሁን ባለበት ደረጃ እንዲገኝ ላደረጉት መምህሬና አማካሪዬ ለዶ/ር ዮናስ አድማሱ የላቀ ምስጋና አቀርባለሁ።

ይህን የጥናት ርዕስ ለመምረጥ ፈራ ተባ በምልበት ጊዜ፣ ርዕሡ ሊያስራኝ እንደሚችል መረጃዎችን በመጠቆም ጭምር ላበረታቱኝ መምህሬ ለአቶ ዘሪሁን አስፋው፣ በተለያዩ ሰነዶች ከታጨቀው ቢሮዎት ውስጥ ጉንበስ ቀና ብለው (እኔ እንዳየሁት ከዶሴዎች ስር ፈልፍለው በማውጣት) ያልታተመ ጥናታዊ ሥራዎትን ለሰጡኝ ለመምህሬ ለዶ/ር ፈቃደ አዘዘ፣ እንዲሁም፣ ለጥናቱ የሚሆኑ የተለያዩ መረጃዎችን ከመስጠት አልፈው፣ ተግቼ እንድሠራ በተግሳፅ ጭምር ላነቁኝ መምህሬ ለአቶ ደረጀ ገብሬ (ጋሽ ደረጀ) ውለታችሁን አስታውሼ ያመሰገንኳችሁ ክብሩ ለእኔው እንደሆነ በማወቁ ጭምር ነው።

<u>የአዲስ አድማስ</u> ጋዜጣ ከፍተኛ አዘጋጅ ሰለሞን ገብረ እግዚአብሔር፣ ለዚህ ጥናት ላደረከው ፈርጀ ብዙ አስተዋጽኦ በተለይ፣ ከ"ነጭ ካፒታሊዝም" አቀንቃኝነትህ አንፃር በርዕዮተ ዓለም ልዩነት እንድንሟገት ፈቅደህ ብዙ እንዳነብና እንድጠይቅ ስላደረከኝ ውለታህ ከምስጋና በላይ ነው፤ የብዕር ስምህን ጠቅሼ፣ ሃገር የሚሞግቱ ፍልስፍናዎችህን ብናገር እንዴት ደስ ባለኝ? እንዳለ ጌታ ከበደ (ደራሲ)፣ ለጥናቴ የሚበጁኝን መጻሕፍት ከማዋስ አልፈህ፣ ስታነብ ያጋጠሙህን መረጃዎች "ለገዛኸኝ ፀ. ያስፈልገዋል" እያልክ በማሰባሰብህ፣ ውለታህ ከባልንጀርነትህ በላይ ገዘፈብኝ፤ በጉራጊኛህ "ኬር ሻዶ" ብዬሃለሁ።

ጋሽ አስፋው ዳምጤ (ደራሲና ሃያሲ)፣ ጋሽ መስፍን ሃብተማርያም (ደራሲ) እና ጋሽ አጥናፍ ሰገድ ይልማ (ደራሲና አንጋፋ ጋዜጠኛ) ወደ ሃመሮች መንደር ስንጓዝ የወይጦ በርሃ እና የቡስካ ተራራ ሳይበግሯችሁ (በጥያቄ ስነዘንዛችሁ) ስለዛ ዘመንና ስለዛ ትውልድ ያወጋችሁኝ ሁሉ ለጥናቴ ትልቅ ስንቅ ሆኖኛልና ፈጣሪያችሁ እረጅም እድሜ እንዲሰጣችሁ ከመለመን በቀር ምን ላደርግ ይቻለኛል?

ለጥናቴ አንዳንድ መረጃዎችን ከመስጠት አልፈህ፣ "አንተ በርትተህ ሥራ፤ የመመረቂያህ ሱፍ የእኔ እዳ ነው" እያልክ በንቢርህ ጭምር ያነቃኸኝ ሰለሞን ከበደ (የብዕር ስምህን ብጠቅስ ክብሩ የኔ ነበር)፣ የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠት የመልካም

ወዳጅነታችሁ ባለውለታ ያደረጋችሁኝ ኢዮብ ካሳ ("የፍቅር" አባት)፣ ተፈሪ መኮንን፣ ተፈራ ደምሴ እና መልካሙ ተክሌ እባካችሁ ምስጋና እንዳደርስ ፍቀዱልኝ?

ይህን ጥናት እየሰራሁ ባለሁበት ጊዜ የግዕዝ ቋንቋ ሲፈትነኝ ፈጣን ምላሽህን ያልነፈግሽኝ ወዳጄ ይስማዕከ ወርቁ ("ዶርቶጋዳ")፣ ቀጭን ትዕዛዜን አክብረህ ያልኩህን መረጃ በፍጥነት ያቀረብክ ወንድሜ አለባቸው ሞልቶት (የቢ.ሲ. አባት)፣ ንጭንጬን ታግሰሽ ይህን ጽሁፍ በመተየብ ባለውለታሽ ያደረግሽኝ የቅርብ አማካሪዬ ባንችጊዜ ስንታየሁ (የ"ሚኪ." ሃና)፣ በጥናት ሥራው ተደፍቼ ስውል ስረሃቤ የደረስሽልኝ የስጋም የመንፈስም ህብስቴ ፍጹም ገብረ እግዚአብሔር፣ መብራቱን አብርቼ ሳድርና ቤተመጻሕፍት አምሽቼ በሌሊት ስገባ አንድም ቀን ክፉ ፊት ሳታሳዩኝ የተከራየሁት ቤት የሰራሁት እስኪመስለኝ ድረሥ ነፃነቴን የጠበቅሽልኝ ትሁቷ አጉራሼ እየሩስ መንግስቱ ሁላችሁንም ምን ብዬ እንደማመሰግናችሁ ግራ ገብቶኛል፤ እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

በመጨረሻም፣ ለኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ቤተመጻህፍት ሠራተኞች በተለይ ለፍጹም ወልደ ማርያም እና ለጋሽ ደመቀ፣ ለብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መፃህፍት ኤጀንሲ ሰራተኞች፣ ለጥናቱ መስሪያ የሚሆን ብር (2700.00) ለሰጠኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ደመወዜን እየከፈለ እንድማር ለፈቀደልኝ ለአክሱም ዩኒቨርሲቲ የላቀ ምስጋናዬን ሳቀርብ እወዳለሁ። ያለ እናንተ ተሳትፎ ይህ ጥናት አሁን ላለበት ደረጃ አይበቃም ነበርና ባለውለታችሁ መሆኔን እወቁልኝ።

አጠቃሎ

ይህ ጥናት፣ "'የኮሌጅ ቀን' ገጣሚያን[ን] ማህበረ ፖለቲካዊ አመለካከትና ሂስ" ለመፈተሽ እና የኮሌጅ ቀን ክብረ በዓል (የገጣሚያኑን ዳራ ጭምር) ለመመርመር ሞክሯል። ጥናቱ፣ ተመራጭ እንደሆነ ያመነበትን ዲያሌክቲካዊ የትንተና ስልት (dialectical analytical method) በአጠናን ዘዴነት ተጠቅሞ፣ ለጥናቱ የተመረጡ ግጥሞችን፣ ከዩኒቨርሲቲውና ከሃገር አቀፉ ማህበረ ፖለቲካዊ ክስተቶችና አውዶች ጋር እያናበበ ተንትኗል። ታሪካዊ ዳራው በታየበት ክፍል፣ ጥናቱ፣ እስከ አሁን በውል የማይታወቁትን የሁሉንም ዓመት አሸናፊ "የኮሌጅ ቀን" ገጣሚያን፣ የግጥም ርዕሦቻቸውን፣ በውድድሩ ያገኙትን ደረጃ እና እስከ አሁን ተፈልገው ያልተገኙ ሦስት ግጥሞችን አግኝቶና መዝግቦ፣ በግኝት መልክ አስፍሯል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባሳተመው በ<u>የኮሌጅ ቀን ግጥሞች</u> (1993 ዓ.ም.) መድበል ውስጥ ያጋጠሙ ህፀፆችን ጠቁሟል። ግጥሞቹ ሲተነተኑ፣ ገጣሚያኑ በርካታ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ርዕሠ ጉዳዮች ማቀንቀናቸውን፣ ማህበራዊ ሂሶቻቸው ጐላ ብለው ቢታዩም ሰበበ ግጥሞቹ በአብዛኛው ፖለቲካዊ ጥያቄዎች እንደሆኑ መታወቁን፣ ለሁሉም ግጥሞች መለዮ የሚሆኑ ፈሮች (patterns) ሲፈለጉ በቅርፃቸው፤ ረዣዥምም፣ ዘርዛሪና አብዛኞቹም ተራኪ ግጥሞች መሆናቸውን፤ የግጥሞቹ የሀሳብ ታሪኮች ሲፈተሹም ከዓመት ዓመት ባይተዋርነታቸው (alienation)፣ ተጠራጣሪነታቸው (skepticism)፣ ተስፋ ቆራጭነታቸው (despairing) እና ባዶነታቸው (Nihilism) እየገነነባቸው መምጣቱን፤ ግጥሞቹ በ1951 ዓ.ም. ስነ ምግባርን በማዕከላዊ ጭብጥነት በማቀንቀን ጀምረው፣ በ1960 ዓ.ም. ለፖለቲካዊ ችግራቸው መፍትሔው የትጥቅ ትግል እንደሆነ እስከ መግለፅ የደረሱ ገጣሚያን መኖራቸውን ጥናቱ አረጋግጧል። በመጨረሻም፣ ገጣሚያኑ ያነሱት የመናገር ነፃነት እጦትና ተጨባጭ እንቅስቃሴያቸው አለመጣጣሙ፣ እንዲሁም ከኮሌጅ ቀን ገጣሚያን ሁሉ በተለየ ሁኔታ፣ በየጊዜው በሚወጡ መጻሕፍት ላይ አዳዲስ መረጃዎች የሚዘከሩለት "የየካቲቱ ገጣሚ" ማንነት ዙሪያ ጥልቅ ጥናት ማስፈለጉ በጥያቄ መልክ ቀርበዋል።

ማውጫ

ገጽ

አበርክቶ .... ፪

ምስጋና .... ፫

አጠቃሎ .... ፬

ማውጫ .... ፭

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ 1

1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 2
2. የጥናቱ ዓላማ 4
3. የጥናቱ አስፈላጊነት 4
4. የአጠናን ዘዴ 5
5. የጥናቱ ወሰን 8
6. ያጋጠመ ችግር 9

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት 10

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 10

2.2 ከ1950-1960 ዓ.ም. ያለውን ሃገራዊ ሁኔታ የሚጠቁሙ የአማርኛ ሥነ ጽሁፎች፣ ከማህበረ ፖለቲካዊ አውዱ ጋር ሲቃኙ 18

2.2.1 ከ1950-1960 ዓ.ም. የታዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ክስተቶች 18

2.2.2 ከ1950-1960 ዓ.ም. ያለውን ሃገራዊ ሁኔታ የሚጠቁሙ የአማርኛ ስነ ጽሁፎች ቅኝት 20

2.3 ግጥም እንደ ትግል መሣሪያ 23

2.3.1 ግጥም እንደ ገጣሚያኑ ዳራ 24

2.3.2 ግጥም እንደ ርዕዮተ ዓለም ማቀንቀኛ 25

ምዕራፍ ሦስት

"የኮሌጅ ቀን" በዓል ታሪካዊ ዳራ እና የገጣሚያኑ ሚና 28

3.1 1950 - "የኮሌጅ ቀን" አሠያየምና የቅድመ ግጥም ውድድሮች ቅኝት 28

3.2 1951 - "የኮሌጅ ቀን" ግጥሞች ውድድር አጀማመር እና የዓመቱ
አንኳር ሁነቶች ቅኝት 29
3.3 1952 -የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር 32
3.4 1953 -የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር 34
3.5 1954 -የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር 35
3.6 1955 -የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር 38
3.7 1956 -የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር 39
3.8 1957 -የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር 40
3.9 1958 -የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር 40
3.10 1959 -የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር 42
3.11 1960 -የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር 43

ምዕራፍ አራት

የአሸናፊ ግጥሞች ትንተና

4.1 የ1951 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና 45
4.2 የ1953 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና 47
4.3 የ1954ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና 54
4.4 የ1956 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና 60
4.5 የ1958 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና 64
4.6 የ1959 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና 71
4.7 የ1960 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና 80

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ 88

ዋቢዎች 93

አባሪዎች

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

በአማርኛ የሥነግጥም ታሪክ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ተፅፎ ተገኘ ከተባለው ከንጉስ አምደ ፅዮን የውዳሴ ግጥም ጀምሮ፣ በየዘመኑ ግጥም፣ የፖለቲካና የማህበራዊ እውነቶቻችን ማቀንቀኛ አንጋፋ የትግል መሣሪያችን ነው ማለት ይቻላል።[1]

ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ እነ Abrams[2] (1999፣ ገጽ 282) እንደሚሉት ግጥም ከሁሉም የሥነ ጽሁፍ ዘውጎች የበለጠ ለስሜት ቅርብ በመሆኑ እንደሆነ ይጠቁማሉ፤ በሌላ በኩል፤ ከግዕዝ ቋንቋ ጀምሮ በአማርኛም የቀጠለ፣ ህዝቡ "በሠምና ወርቁ" ግለሰባዊም ሆነ ሃገራዊ ርዕዮተ ዓለሙን የሚያቀነቅንበት የዳበረ የቅኔ ልምዱና ባህሉ [Greenfield, 1968: 17] ጭምር እንደሆነ መግለፅ ይቻላል። ነቃሽ ይጠራ ከተባለም፣ እነ ዮሐንስ አድማሱ፣ አቤ ጉበኛ በዚሁ "የሠምና ወርቅ" የኑሮ ፍልስፍና ተገርተው የሠሉ ባለቅኔዎች መሆናቸውን ማስተንተን ይቻላል (ሳህሉ፣ 1992)።

ግጥም የተዋጣለት የሃሳብ ማሄጃ ለመሆኑም "የጥበበ ተፈጥሯዊ ባህሪያት" መሰረት እንደሆኑ የመስኩ ባለሙያዎች ያስረዳሉ (ብርሃኑ፣ 1999፣ ገጽ 11)።

ቀዳሚዎቹ "ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አዲስ አበባ" ተማሪዎችም፣ ግጥምን በወቅቱ ላነሷቸው ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሂሶች ማሄጃነት ተገልግለውበት ነበር። ገጣሚያኑንም "ይህ ትውልድ ኋላ በመጠኑም ሰፍቶ በጥራቱም ፈክቶ ለተከተለው የዐመፅ ትውልድ ፋና አብሪ ነበር። ዋና መሣሪያው ብዕሩ ነበር" በማለት ዮናስ አድማሱ በጦቢያ (7ኛ ዓመት ቁ.3፣ 1992) መጽሔት ላይ በጻፉት መጣጥፍ ገልፀዋቸዋል።

በወቅቱ የተገጠሙት "የኮሌጅ ቀን ግጥሞች"ም በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ለሚካሄደው የስፖርት ውድድር ማድመቂያነት የሚቀርቡ፣ እያደርም "የበዓሉ ቁንጮ፣ ተናፋቂ እና መቋጫ ..." እየሆኑ የመጡና በውድድር ተመርጠው፣ በ "ዩኒቨርሲቲው ኮሌጅ ቀን" ንጉሠ ነገስቱ በተገኙበት ጭምር ይነበቡ የነበሩ፣ የተማሪ ግጥሞች ናቸው። እነዚህ ግጥሞች የሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮችና ጭብጦች ያልኖሩበትን ዘመን ሁሉ የኋሊት የመረመሩ፣ የወደፊቱን እንደ ደረቅ ትንቢት የሚናገሩ ዘመን ተሻጋሪ የሥነ ፅሁፍ ሥራ እንደሆኑ በጨረፍታ እንኳን የተመለከቷቸው ብዙ አጥኚዎች ጠቁመዋል (ባህሩ፣ 2000፥233፤ ደረጀ፣

---

[1] ዮናስ አድማሱ፣ "The Image of the Hero in an Early Amharic Panegyric: Towards a Discourse of Empire" በሚል ርዕስ በአንድ የውዳሴ ግጥም ላይ ተወስነው ባቀረቡት ትንታኔና ፍካሬ በጊዜው ተፈጥሮ የነበረውን ነባራዊ ምስል አሳይተዋል፣ የወቅቱን የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም የማስረፅ ሥልትንና የማህበራዊ ኑሮ ፍልስፍናን በጨረፍታም ቢሆን አመላክተዋል።

[2] በእንግሊዝኛ የተፃፉ የሰው ስሞች ሁሉ ያስከተሏቸው ዓ.ም. በአውሮፓውያን አቆጣጠር የቀረቡ ናቸው።

2001፤ ዘሪሁን፣ 1985፥36፤ Balsvik, 2005: 106; Molvaer, 1997: 295; Samuel, 1994; Fekade, 1988: 232; Greenfield, 1968: 18)::

"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ" የተቋቋመበት 50ኛ ዓመት ሲዘከር፣ እነዚህ ኪነታዊ ብቃታቸው ከርዕስ ጉዳይ ጥልቀታቸው ሰምረው የሚታዩባቸው ግጥሞች፣ በ1993 ዓ.ም. ተሰብስበው መታተማቸው፣ ለስነ ጽሁፋችን ብቻ ሳይሆን ለታሪክ ጥናታችንም ትልቅ ሚና ያለው ይመስለኛል። ለግጥሞቹ ህትመት የታተሩ የስነ ጽሁፍ ወዳጆችም ሊመሰገኑ ይገባል። በሌላ በኩል፣ የተባሉት ግጥሞች በሙሉ አለመገኘታቸው (ለምሳሌ ከ1952 ዓ.ም. ለናሙና አንድም አልቀረበም) ደግሞ ያሳስባል፤ ያስቆጫል - ለፍለጋ ያነሳሳልም። በእነዚህ ግጥሞች ላይ የሚደረግ ጥናትና ምርምር፣ የዩኒቨርሲቲውንና የገጣሚያኑን ዱራ ማካተት እንዳለበት፣ የታተመው መጽሐፍ በነቢቡም በገቢሩም ይጠቁማል።

2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

"አዲስ የምርምር ሃሳብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ቀደም ሲል የተሞከሩና የተጠኑ ርዕሶችን (ችግሮችን) በመመርመር ላይ ቢመሰረት ጠቀሜታው የጐላ ነው።"

(አንበስ እና ሌሎች፣ 1994፥ 53)

ለዚህ ጥናት መነሻ የሆኑ ምክንያቶች አሉ። በመጀመሪያ ለ"ኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ ሴሚናር (EtLi 616) ኮርስ" ማሟያ የቀረበ መጠነኛ የጥናት ወረቀት (Term Paper) በዮሐንስ አድማሱ ግጥሞች ላይ በመስራቴ፣ <u>የኮሌጅ ቀን ግጥሞች</u>ን በሂሳዊ ንባብ ደግሞ የመመልከት አጋጣሚ አገኘሁ። በዚህ ሳቢያም፣ ፊቃደ አዘዘ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ የ"ኮሌጅ ቀን ግጥሞች" ይሄ ነው የሚባል ጠንከር ያለ ምርምር ስላልተደረገባቸው ከተለያዩ አውዶች ጋር እየተገናዘቡ በስፋት እንዲጠኑ ያመላከቱበት ሙያዊ ጥቆማ፣ ርዕስ ጉዳዩን እንዳስብበት አነቃኝ።

የፊቃደ የመግቢያ ፅሁፍ፣ ነቅቶ ከማሰብም ባለፈ ቁጭት ውስጥ የሚያስገባ፣ "የሥነ-ጽሁፍ ተማሪ ነኝ" የሚል ያለበትን ኃላፊነት እያስታወሰ እልህ ቢጤ የሚያጭር፣ ግጥሞቹን ለማጥናት የፈለገም ታሪካዊ ዱራቸውን ሁሉ በወጉ እንዲመረምር የሚያተጋ የተለያዩ የጥሪ ደወሎች አስተጋቢ አጭር ሙያዊ ትንተና ጭምር ነው። በመሆኑም፣ ለጥናቱ ከመነሻነት አልፎ፣ የምርምሩን አስፈላጊነት፣ ዓላማዎችና የአጠናን ሥልቶች ሁሉ ስላመላከተ፣ ዋና ዋና ሀሳቦቹን አለፍ አለፍ እያሉ እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

> ... <u>መድበሉ ግጥሞቹን ሁሉ ያካተተ አይመስለኝም</u> ... ያልተገኙትን በነበረው አጭር ጊዜ አፈላልጐ ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ ይመስለኛል።

አንዳንዶቹ እንደ ጓደኞቻቸው ... የመታተም ዕድላቸው እየደበዘዘ እንዳይሄድ የምንሰጋ ጥቂት አይደለንም።
... የታተሙት ግጥሞች በሙሉ "የኮሌጅ ቀን ግጥሞች" ናቸው ብሎ በሙሉ አፍ ለመመስከር የሚያስችል የጽሁፍ ማስረጃ ገና የለኝም።
... ገጣሚያኑን፣ ግጥሞቹን እና የዘመኑን ሕይወት ለመረዳት ጠለቅ ያለ ምርምር ማድረግ የግድ ያስፈልጋል።
... በብዙ ረገድ ገጣሚያኑ ቀድመው የተገኙ ይመስለኛል። ይህ ግን በምርምር እስካልተረጋገጠ ድረስ ያው የእኔ "ይመስለኛል" ሆኖ ይቆያል ማለት ነው። ... የኮሌጅ ቀን ገጣሚያን፣ ... ስንቶቹ በዚህ ድርጅታዊ ፖለቲካ ውስጥ በቀጥታ ተሳተፉ? ... አስተዋጽኦዋቸውና መጨረሻቸው ምንድን ነው? ... ጉበዝ ሀያሲ ጠለቅ ያለ ምርምር አድርጎ የደረሰበትን በቅርቡ ይነግረናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እስከዚያ እኔም ወደዚያ ማዝገሜን አላቋርጥም... (አጽንኦቱ የእኔ ነው። የኮሌጅ ቀን ግጥሞች፣1993፥v-ix)።

"ይህን መግቢያ ያነበበ እነዚህን ግጥሞች ለማጥናት አይደፍርም" እንዲሉ፣ አጭር ምልከታውም ሆነ ግጥሞቹ ከታተሙ ዓመታት ቢቆጥሩም፣ እስከ ዛሬ አለመጠናታቸው በአንድ በኩል "ለእኔ ቢላቸው ነው" ብዬ ሥደሰት፣ በሌላ በኩል "አጉል ድፍረት" ይሆንብኝ ይሆን? ብዬ መስጋቴም አልቀረም። በቅንጭብ ፅሁፍ ውስጥ ያሰመርኩባቸው ተተኳሪ ሀሳቦችንም፣ የጥናቱ አካል ሳያደርጉ ገሸሽ ማለትም ለህሊናም ሆነ ለሙያው እንደሚከብድ ተረዳሁ። የጥናት ርዕሱን ከማስመዝገቤ በፊትም የቅድመ ጥናት፣ ዳሰሳ ንባብ አደረግሁ።

በሌላ በኩል ቀደም ሲል ፊቃደ እንደጠቆሙት ገጣሚያኑና ግጥሞቻቸው በወጉ ባለመጠናታቸው በእነሱ ዙሪያ የሚነሱ ሀሳቦች (በወቅቱ ተሳታፊ በነበሩት የያኔው ትውልድ አባላት ሣይቀር) ከእውነታው ጋር ሲጣረሱ ታዘብኩ፤ አንዳንድ ጊዜ ከማስቆጨት አልፎ ቢያሳዝንም።[3] ታሪካዊ ዳራቸው በወጉ ባለመጠናቱም፣ በእነሱ ዙሪያ የተነሱ መረጃዎች እየተፋለሱ ዛሬም ድረስ እንደሚዛፉ የተወሰነ ፍንጭ አገኘሁ። ለምሳሌ፣ የBalsvikን (2005፡ 337-338) የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኮሌጅ ቀን ግጥሞች መድበል፣ የኮሌጅ ቀን ገጣሚያኑን ያወሱ የተለያዩ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶችና የተለያዩ ወቅታዊ የመረጃ ምንጮችን (ጋዜጦች፣ መጽሔቶች) ማጣቀስ ይቻላል። ስለዚህ የተባሉት

---

[3] ለምሳሌ አዲስ ነገር ጋዜጣ (1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 042) በነሀሴ 3 ቀን 2000 ዓ.ም. እትሙ፣ በርዕሰ አንቀጹ ላይ "... በተማሪዎች የትግል ታሪክ እንደ መሬት ላራሹና የብሔር ብሔረሰብ መብት ሀሳብን ስለመግለጽ ነፃነት የጠየቀ፣ የሞተ ወይም የተጐዳ ሰው የለም፤" የሚል ሀሳብ አትቷል። የዚህ ጥናት አቅራቢ ግን፣ የተማሪዎች እንቅስቃሴ አነሳስና የትግል ስልት ያላገናዘበውን አስተያየት ለማረም በሚል በአዲስ አድማስ ጋዜጣ (ቅጽ 8 በቁጥር 455 እና 456) በጥቅምት 8 እና 15፣ 2000 ዓ.ም እትሙ "ዮሐንስ አድማሱ ሀሳብን ስለ መግለጽ ነፃነት የተሟገተ ባለቅኔ" እና "የኮሌጅ ቀን ገጣሚያን ሀሳብን ስለመግለጽ ነፃነት የተሟገቱበት ስልት" የሚሉ ሁለት መጣጥፎች በተከታታይ በማስነበብ እውነታውን ለማስገንዘብ ያቅሙን ያህል ተፍጨርጭሯል (ዮሐንስ አድማሱን ከኮሌጅ ቀን ገጣሚያን በተለየ በቀዳሚነት ለብቻ እንዲዘከር ያስቻለው፣ ሀሳብን ስለመግለጽ ነፃነት በተለይም ስለ ሳንሱር በግልጽ የሄሰ፣ ከኮሌጅ ቀን ገጣሚያን ቀዳሚው ተሟጋች ነው በሚል እሳቤ መሆኑ ተገልጿል)።

ጉዳዮች፣ ጥናቱን በኮሌጅ ቀን ግጥሞችና ገጣሚያን ላይ እንዳደርግ መነሻና ብርታት ሆነውኛል።

3. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት፣ "የኮሌጅ ቀን ግጥሞች"ን ዳራ፣ የኮሌጅ ገጣሚያኑን ማህበረ ፖለቲካዊ አመለካከታቸውን እና ሂሳዊ ስልታቸውን ይመረምራል። ይህ አጠቃላይ የትኩረት አቅጣጫ መሰረት ተደርጎም፣ የሚከተሉትን መሪ ጥያቄዎች በዝርዝር ለመመለስ ይጥራል። ጥያቄዎቹም፣ እንደሚከተሉት ቀርበዋል።

1ኛ "የኮሌጅ ቀን ግጥሞች" መቼ፣ እንዴት፣ ለምን እና በማን ... ይቀርቡ ነበር? በምንስ አይነት ማህበራዊና ፖለቲካዊ አውድ ውስጥ ተገጠሙ?

2ኛ ገጣሚያኑ በግጥሞቻቸው ያነሷቸው ዋና ዋና ማህበራዊና ፖለቲካዊ ርዕሰ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

3ኛ ገጣሚያኑ በግጥሞቻቸው የወቅቱን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ የሄሱበት ስልት ምን ይመስላል?

4ኛ ገጣሚያኑ የተከተሏቸው ወይም ተፅዕኖ ስር የወደቁባቸው የአስተሳሰብ ፈለጎች (ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፍልስፍናዎች) አሉ? ካሉ ምን ምን ናቸው?

5ኛ በግጥሞቹ ውስጥ የታዩ ለሁሉም መለዮ የሚሆኑ ፈሮች (patterns) አሉ?

4. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ከ1951 ዓ.ም. ጀምሮ በተነሱ "የኮሌጅ ቀን" ገጣሚያን ላይ ቢያተኩርም፣ የዛን ዘመን የሃገሪቱን ማህበራዊና፣ ፖለቲካዊ ሁኔታ ጭምር ከግጥሞቹ ጋር እያናበበ ስለሚመረምር፣ "የአብዮተኛውን ትውልድ" አሻራ መነካካቱ አይቀርም። "ያ ትውልድ" ደግሞ፣ ዛሬም ድረስ የሃገሪቱን የፖለቲካ አቅጣጫ እየመራና እየወሰነ ያለ፣ ለታዩት እድገቶች እና ውድቀቶችም ግንባር ቀደም ተጠቃሽ እና በብዙ መልኩም ቀድሞ የተገኘ ፋና ወጊ እንደሆነ ይነገርለታል (Balsvik, 2007:177 እንዲሁም ባህሩ፣ 2000 ፥ 234 ይመልከቱ)። የዚያ ትውልድ አባል የሆኑት የኮሌጅ ቀን ገጣሚያንም፣ በትውልዱ ውስጥ የላቀ ድርሻ ስላላቸው[4] እነሱን አስመልክቶ የሚደረግ ጥናት በበዙ መልኩ ተፈላጊ እንደሚሆን ይታመናል።

---

[4] የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር የኢትዮጵያን ዘመናዊ ሥነ-ጽሁፍ የመቶኛ ዓመት ልደት ምክንያት በማድረግ፣ ከግንቦት 24-28 ቀን 1999 ዓ.ም. ባዘጋጀው መድረክ ላይ ከቀረቡት 15 ጥናቶች ውስጥ 3ቱ (የዮናስ አድማሱ፣ የጌታቸው በለጠና የብርሃኑ ገበየሁ) የተመካከሩ እስኪመስል ድረስ በአንድ ጊዜ ገጣሚያኑ

ገጣሚያኑም የዛ ትውልድ ታላቅ የታሪክ ባለድርሻዎች ቢሆኑም እንደ አፈ-ታሪክ፣ በስማ በለው ከሚነገርላቸው ዝናቸው በስተቀር፣ በወጉ ተጠንቶ የተሰነደ ታሪክ እንደሌላቸው እነ ፈቃደ አዘዘን (1993) የመሰሉ የተለያዩ አስተያየት ሰጪዎች ይጠቁማሉ። በሌላ በኩል፣ ዛሬም ድረስ በህይወት ያሉት ገጣሚያን የራሳቸውንም ሆነ የሌሎችን የኮሌጅ ቀን ገጣሚያን እና ግጥሞች ሁኔታ ከነባራዊው አውድ ጋር አዋደው እስከ አሁን ድረስም የፃፉቸው አላጋጠሙኝም። በመሆኑም፣ ይህ ሁኔታ ስለ ገጣሚያኑም ሆነ ስለዛ ትውልድ በሚኖር እውቀት ላይ ትልቅ ክፍተት እንደሚፈጥር መገመት ቀላል ነው።

ስለዚህ ይህ ጥናት፣ ይሄን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት የራሱ የሆኑ አስተዋፅኦዎች ይኖሩታል ተብሎ ስለሚታሰብ በቀዳሚነት ተፈላጊ ሊሆን ይችላል። ዛሬ በህይወት ያሉት ገጣሚያንም ከእድሜያቸው ጋር እየተሸቀዳደሙ ተገቢውን መረጃ በወጉ ሰንደው እንዲያኖሩ ያነቃቸው ይሆናል። በዋናነት በዛ የዘመን ምዕራፍ ላይ ስለዛ ትውልድ በተለይም ስለ ቀዳሚዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ መስራቾች ጥናት ለሚያደርጉ የታሪክ፣ የፖለቲካ እና የሥነ-ጽሁፍ ተመራማሪዎች አቅጣጫ አመላካች ከመሆኑ በተጨማሪ ጥሩ የመረጃ ምንጭ ይሆናቸዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ጥናቱ መደረጉ አስፈላጊ ነው ተብሎ ታምኖበታል።

5. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት የኮሌጅ ቀን ግጥሞችን አጠቃላይ ዳራ፣ እንዲሁም የገጣሚያኑን ማህበራዊና ፖለቲካዊ አመለካከት፣ እስከ ጥልቅ ሂሳቸው ድረስ ከወቅቱ ፖለቲካዊና ማህበራዊ አውድ ጋር እያነፃፀረ መርምሯል።

ግጥሞቹ ምን ምን ርዕሰ ጉዳዮችን እንዳነሱ፣ ምን አይነት የዘመን ፈለግ እንደተከተሉ፣ ደረጃቸው በንጽጽር ምን እንደሚመስል፣ ወዘተ. ላይ ስላተኮረ፣ ጥናቱ የሥነጽሁፍ ታሪክ መርምር ውስጥ ይመደባል። ይህ ከሆነ ደግሞ፣ ማቀንቀኛችን "ሥነ-ፅሁፍና ሀሳብ" (Literature and Ideas) የሚለው ነው። ለዚህ፣ Warren እና Wellek (1984:111)፣ "To be sure, literature can be treated as a document in the history of ideas and philosophy, for literary history parallels and reflects intellectual history" ያሉትን መጥቀስ ይቻላል።

የኮሌጅ ቀን ገጣሚያንና ግጥሞች ዳራ ሲቃኝ፣ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ታሪክ አካል እንደሆነ ይታመናል (Balsvik, 2007)። የተማሪዎች እንቅስቃሴ ደግሞ አለማቀፋዊና ሃገራዊ መልክ አለው። Fentahun (1990:6)፣ አለማቀፋዊና አህጉራዊ መልክ ያለውን

በሃገሪቱ የፖለቲካና የሥነጽሁፍ ታሪክ ቀዳሚ ድርሻ እንዳላቸውና የአጥኚዎችንም ቀልብ እንደሚሥቡ ተናግረዋል። ማህበሩ 12ቱን ጥናቶች <u>መድበለ ጉባኤ</u> በሚል ርዕስ 2001 ዓ.ም አሳትሟቸዋል።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በተሟላ መንገድ ለማጥናት ዲያሌክቲካዊ የትንታኔ ስልት (dialectical analytical approach) መከተል ተመራጭና የጥናቱ ባህሪ የሚጠይቀው ዋና ዘዴ እንደሆነ በአፅንኦት ይገልፃሉ። ተራማጅ መዝገበ ቃላትም (1968 ዓ.ም.) በማርክሳዊ ተፅዕኖ ውስጥ ወድቆ፣ ጥናትና ምርምር በሁለት መንገድ ብቻ እንደሚጠና ወይም መጠናት እንዳለበት የገለጸበት ጭፍን ብያኔ ተቀባይነት ባይኖረውም ዲያሌክቲክስን የገለጸበት መንገድ ከዚህ ጥናት አካሄድ ጋር ስለሚስምር እንደሚከተለው ቀርቧል።

> የተፈጥሮ ባህርያት፥ የህበረተሰብን አቋምና ታሪክ ለማጥናት በሁለት መንገዶች መጓዝ ይቻላል። አንደኛው መንገድ ዲያሌክቲክስ ሲሆን ሌላው ደግሞ ሜታፊዚክስ ይባላል። የፍጥረታትም ሆነ የህበረተሰብ ጥናት ትክክለኛ ውጤት እንዲሰጥ የሚረዳውና ከሚጠናውም ጉዳይ ባህርይና የእድገት ህግጋት ላይ የሚመሰረተው የጥናት ዘዴ ዲያሌክቲክስ የሚባለው ነው (ገጽ 63)።

"ዲያሌክቲክስ ተፈጥሮን እንደ አንድ ሙሉ አካል" ስለሚመለከት ያሏትን ነገሮች እየነጣጠሉ መመርመርን፣ እንደሚደጋገፉ አለማወቅን ይኮንናል፤ ለእርስ በርስ መያያዝና መተሳሰርም ቅድሚያ ይሰጣል። እነ Allen (1997) Intertextuality በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ 46 ላይ "ዲያሌክቲክስ" እና "ኢንተርቴክስቿሊቲ" አብረው ሊሄዱ እንደሚችሉ መጠቆማቸው ግምት ውስጥ ገብቷል። ስለዚህ የኮሌጅ ቀን ግጥሞችና ገጣሚያን ለማጥናት የዩኒቨርሲቲውን አውድ፣ የሃገሪቱን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አውድ፣ ከአህጉራዊና ከአለማቀፋዊ ሁኔታዎች አውድ ጋር በቁርኝት መመርመር ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ጥናቱ፣ ግጥሞቹን እርስ በርስ እና ከሌሎች የስነ-ፅሁፍ ዘመነኛ ሥራዎች ጋር ማናበብን (Intertextuality)፣ ገጣሚያኑ ካጠቃላዩ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጋር ማገናኘትንና በንጽጽር መመርመርን ሁሉ ስለሚጠይቅ ዲያሌክቲካዊ ገላጭ ትንተና አቀራረብን ተግባራዊ አድርጓል።

ዮናስ አድማሱም (June, 2001) ቀደም ሲል የተነሱ የውጭ ሃገር አጥኚዎች[5] የኢትዮጵያ የሥነ-ጽሁፍ ሥራዎችን "መርምረው" የስነ ምግባር ሰባኪነት (Didactism)፣ እውነታዊ (Realistic) አለመሆን ወዘተ. የሞገቱበትና የአማርኛ ስነ-ጽሁፍ የራሱ የአነባበብ ሥልት እንዳለው ያመለከቱበት ጥናታቸው፣ከዲያሌክቲካዊ የትንታኔ ሥልት ጋር አብሮ ስለሚሄድ ለዚህ ጥናታዊ ሥራ አገልግሏል።

በዮናስ ከተጠቆሙ የአነባበብና የአመራመር አማራጮች (possibilities) ውስጥ አንዱ የሚከተለው ነው።

---

[5] የኛ ሃገር አጥኚዎችም ይሄን ሲጋሩ ይታያል። ለምሳሌ፣ ፍቅሬ ቶሎሳ የራሻን እውነታዊነት (Realism) መሰረት አድርገው የአማርኛን ሥነ-ጽሁፍ ሲያጠኑ ጦቢያን ሀገረሰባዊ ተረት (Folktale) እስከ ማለት ደርሰዋል (ታየ አሰፋና ሽፈራው በቀለ፣ 2000 እ.ኤ.አ ገጽ 48)።

One possibility is, as I have already suggested, reading the individual works themselves, first by the same authors, then by groups of authors who have written on related subject matters and themes, until we have been able to trace, however vaguely, some kind of pattern or perspective that would later serve as a guide for developing a general framework within which to consider the literature in question. Moreover, this involves (1) describing subject matters and themes; (2) indicating the various literary "forms" developed by the authors over the years, with a view to exploring the reasons for the emergence of those forms, and hope, from here on, that the discipline will take its own course (PP: 38) .

ይህ የአነባበብ ሥልት፣ ለዚህ ጥናትም ተመራጭ ከመሆኑም በላይ፣ ጥናቱ ሊመልሳቸው የሚገቡ ጥያቄዎችን ለማርቀቅም አገልግሏል። ጥናቱ፣ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ተጠቅሟል። ገላጭ ትንተና የተደረገው በዋናነት በመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች (primary sources) ላይ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች (secondary sources) ደግሞ በማጠናከሪያነትና በማመሳከሪያነት አገልግለዋል። የ50 ዓመት የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን በትዕግስትና ባስተውሎት መመርመር የጠየቀው "'የኮሌጅ ቀን' በዓል ታሪካዊ ዳራ እና የገጣሚያኑ ሚና" የሚለው ክፍል፣ ቢያንስ እስከ ዛሬ ያልተነገረላቸውን ገጣሚያን ስለሚያስተዋውቅ፣ በሃገሪቱ የሥነ ጽሁፍ ታሪክ የራሱ ድርሻ ሊኖረው ስለሚችል፣ መረጃዎቹ እንዴት እንደተጠናቀሩ ማሳየት እንዲቻልና በተሟላ መንገድ እንዲነበቡ በሚል፣ በምዕራፍ ሦስት ለብቻ ሠፍሯል።

በግጥሞቹ ላይ ለሚደረገው ትንተና ድጋፍ የሚሆኑ የንድፈ ሀሳብ መሠረቶችና የተዛማጅ ጥናት ቅኝቶች፣ ዮናስ (June፡ 2001) ባመለከቱት መሠረት ግጥሞቹ በጥንቃቄ ከተነበቡ በኋላ እየተገናዘቡ በምዕራፍ ሁለት ቀርበዋል።

በሌላ በኩል የኮሌጅ ቀን ገጣሚያን ዳራና የዩኒቨርሲቲያቸው አውድ የቀረበበት ምዕራፍ ሦስት እና ትንተና የተደረገበት ምዕራፍ አራት የተዋቀሩት በየአንዳንዱ ዓመተ ምህረት የጊዜ ምዕራፍ እየተለኩ ነው። ለምሳሌ በ1951 የተከበረው "የኮሌጅ ቀን" በዓልና በዓመቱ ውስጥ የተከናወኑ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁነቶች በአንድ ክፍል ተጠናቅረው ቀርበዋል።

ጥናቱ፣ ይህን የትንተና እና የግኝት ማዋቀሪያ መንገድ የተከተለው፣ ባህሩ (2000፥235) እንዳሉት፣ "ተማሪዎች የሚያነሷቸው ነጥቦችና ጥብቅና የሚቆሙላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ከዓመት ዓመት ይለያዩ ነበር" ስለሚባልና በእርግጥም የአጠቃላይ የተማሪዎቹ እንቅስቃሴም ሆነ የግጥሞቹ የትኩረት አቅጣጫ ከዓመት ዓመት ይለዋወጡ

ስለነበር ጭምር ነው። በርግጥ የግጥሞቹ የትኩረት አቅጣጫ እና የገጣሚያኑ አመለካከትና ስሜት የሚቀያየረው ከዓመት ዓመት ብቻ አይደለም፤ በአንድ በተመሳሳይ ዓመት (ለምሳሌ በ1959 ዓ.ም.) ላይ ባሸነፉ ግጥሞች መካከል፣ የተራራቀ ልዩነት ያጋጥማል። በተለይም ገጣሚያኑ ከአጠቃላይ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጋር ያላቸው ግንኙነትና ቅርበትም በየዓመቱ ይለያይ ነበር። ከአንድ ዓመት ጊዜ በላይ ካሸነፉ ገጣሚያን መካከልም (ከተማሪዎች እንቅስቃሴና በተለይ ከመንግስታዊ ስርዓቱ አንፃር) አንዳንዶቹ ገጣሚያን ከዓመት ዓመት ያመለካከትና የአቋም ለውጥ ያደርጉ ስለነበር ግጥሞቹ፣ ከተመሳሳይነታቸው (similarity) ይልቅ፣ ልዩነታቸው (difference) የሚያይል ይመስላል።

ይህ ጥናት ደግሞ በሥነ ጽሑፍ (በሀሳብ) ታሪክ ላይ የሚያተኩር፣ ሥነ ጽሑፍንና ታሪክን የሚያናብብ በመሆኑ፣ ግጥሞቹ የሀሳብ ልዩነት በግልፅ እየታየባቸው አሁን ባሉበት ደረጃ በናሙና መርጦ መተንተን ተመራጭ አካሄድ አልሆነም፤ ምክንያቱም፣ በናሙና የሚመረጡት ግጥሞች የሚያነሷቸውን ሀሳቦች፣ ከማይመረጡት ግጥሞች ውስጥ ያሉትን ሃሳቦች ሊወክሉ የማይችሉበት አጋጣሚ በርከት በማለቱ ነው። (የ1951 ዓ.ም. በከፊል፣ የ1952፣ የ1955 እና "የ1957" አሸናፊ ግጥሞች በሙሉ አለመገኘታቸውም ግምት ውስጥ ገብቷል)። ስለዚህ፣ የጥናቱ ትኩረትና የአጠናን ዘዴው በሚፈቅደው መሰረት ግጥሞቹን በየአሸነፉበት ዓመት ፈርጆ፣ በያዟቸው ሀሳቦች ስፋትና ጥልቀት መሰረት አንዳንዶቹን በረዥሙ፣ ሌሎቹን በአጭሩ በመተንተን ለሁሉም መለዮ የሚሆኑ ፈሮችን (Patterns) መለየት የሚያስችል አመክንዮዋዊ (logical) አካሄድ ለመከተል ጥረት ተደርጓል።

ግጥሞቹ፣ በየዓመቱ የአነሷቸው ርዕሠ ጉዳዮችን ለመመርመር እና ከዓመት ዓመት የታየውን የሀሣብ ታሪክ (history of ideas) ለመገምገም እንዲረዳም፣ የግጥሞቹን ማዕከላዊ ጭብጥ ጨምቆ በማውጣት እርስበርስና ከሌሎች የዘመኑን ሁኔታ ከሚጠቁሙ ሥነ ጽሁፎች ጋር እያናበቡ ለመተንተን ተሞክሯል።

6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በዋናነት ከ1951-1960 ዓ.ም. በተገጠሙ "የኮሌጅ ቀን ግጥሞች" እና ገጣሚያን ላይ ተወስኗል። ማጠንጠኛውም፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተመሰረተበትን 50ኛ ዓመት በዓል ሲዘክር በ1993 ዓ.ም. ያሳተመው የኮሌጅ ቀን ግጥሞች ሲሆን፣ በመፅሐፉ ያልተካተቱ፣ በኮሌጅ ቀን በዓል ላይ ቀርበው የነበሩ (በአጥኚው ምርምር የተገኙ) ሌሎች ግጥሞችም የጥናቱ አካል ሆነዋል።

ጥናቱ፣ የዲያሌክቲካዊ የትንታኔ ዘዴ በሚጠይቀው መሠረት፣ የወቅቱን የሃገሪቱን ሁኔታ እያነፃፀሩ መገምገምን ይጠይቃል። ስለዚህ ጥናቱ፣ የዩኒቨርሲቲውንና በአጠቃላዩም

የሃገሪቱን ማህበራዊና ፖለቲካዊ አውድ ከ1951-1960 ዓ.ም. ባለው የጊዜ ምዕራፍ ተወስኖ ይመረምራል። ይህ ማለት ግን ከተጠቀሱት የሥነ-ጽሁፍ ሥራዎች እና ከተቀነበበው የጊዜ ምዕራፍ ውጪ ምንም ነገር አይመለከትም ማለት አይደለም።

6. ያጋጠሙ ችግሮች

ጥናቱ፣ ገጣሚያኑና ግጥሞቻቸውን ከሃገሪቱ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ጋርም ሆነ፣ በ1950ዎቹ በአፍሪካም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከታዩት የተማሪዎች እንቅስቃሴና የትግል ሥልት ጋር እያገናዘቡና እያናበቡ መመርመርን፣ የ50 ዓመት ሠነድ ሁሉ ማገላበጥን ጠይቋል። አንዳንዶቹ መረጃዎች ደግሞ በኢትዮጵያ ጥናት ተቋምም ሆነ በብሔራዊ ቤተዘመዛግብት እና ቤተ መፃህፍት "ኤጀንሲ" በብዙ ጥረት እንኳ ሊገኙ አልቻሉም። በተለይም በካታሎግ ላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች በየቤተ መፃህፍቱ ሲፈለጉ በቀላሉ አለመገኘትና ከነጭራሹ መጥፋት በዋናነት ያጋጠመኝ እልህ አስጨራሽ ችግር ነበር። ስለዚህ፣ የተፈለጉትን መረጃዎች ከግለሰቦች ጭምር በትዕግስት ለማፈላለግ፣ ለጥናታዊ መርሃ ግብሩ "ከተተመነው" ጊዜ በላይ፣ ተጨማሪ የጥናት ጊዜ ተወስዶ፣ አቅም በፈቀደ መልክ ጥናቱን የተሟላ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል።

በተጨማሪም አጥኚው በመጀመሪያ ላይ ካቀደው በተለየ መንገድ የገጣሚያኑን ዳራ ጭምር ስለመረመረ፣ ጥናቱ በልዩ ሁኔታ ተጨማሪ ገጽ እንደሚያስፈልገው በተጨባጭ ቢታይም የታሰበውንና የሚቻለውን ያህል ገጽ በመጨመር ግጥሞቹን እርስ በርስ እያናበቡ የበለጠ አብራርቶ ለመተንተን እድል አላገኘም። በአንድ በኩል፣ የገጣሚያኑና የግጥሞቹ ስነጽሁፋዊ ታሪክ በብዙ ቦታ እየተጣረሰ በመታየቱና የተወሰኑ የጠፉ ግጥሞች የሚገኙበት መንገድ በመታወቀ (ለአካዳሚያዊ ተጨባጭ ግኝቶቹ (facts) ጊዜና ቦታ መስጠት በማስፈለጉ)፤ በሌላ በኩል በትንታኔ የሚብራሩ አካዳሚያዊ እውነቶች (truths) መፈለግም የጥናቱ ዋና ዓላማ በመሆኑ እነዚህን ሁሉ ርእስ ጉዳዮች በተፈቀደው ገጽ ማቅረቡ በዚህ ጥናት ሥራ ያጋጠመ ችግር ነበር። ይሁን እንጅ በትንተናው ክፍል በተለይ በግጥሞቹ ማዕከላዊ ሐሳቦች ላይ ትኩረት በማድረግ፣ አቅም በፈቀደ መጠን ገጹን አመጣጥኖ በብልሃት በማቅረብ ችግሩን ለመቅረፍ ተሞክሯል።

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ለዚህ ጥናት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ደጀን፣ ነቃሽ የሚሆኑ የተዛማጅ ጥናቶችና ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶች ይከለሳሉ።

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ቀደም ሲል በመግቢያ ላይ እንደተጠቀመው የኢትዮጵያን የሥነ-ዕሁፍ ታሪክ ያወሳ ሰው፣ የኮሌጅ ቀን ገጣሚያንን በጨረፍታ እንኳ ቢሆን ሳያነሳቸው እንደማያልፍ ይታወቃል፤ በተመሳሳይ መድረክ ላይ ዮናስ አድማሱ፣ ብርሃኑ ገበየሁና ጓደኞቻቸው በለጠ ያወሷቸውን ልብ ይሏል (ደረጀ፣ 2001)። በዚህ ክፍል ታዲያ በጨረፍታ ያወሷቸውን መጻህፍት ሁሉ እንከልስ ቢባል የጥናቱ መጠነ ርዕይ አይፈቅድም። ነገር ግን፣ እንደ ጥናቶቹ ዓላማና ከፍታ እየተመዘኑ በዚህ ክፍል ሁለት የሁለተኛ ዲግሪ እና አራት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ተቃኝተዋል።

ከስድስት ጥናቶች ሁለቱ በዮሐንስ አድማሱ ሕይወትና ሥራዎች ላይ የሚያጠነጥኑ ሲሆኑ፣ እነሱም "የባለቅኔው የአቶ ዮሐንስ አድማሱ የህይወት ታሪክ" የሚለው የኃይሉ ጀማነህ (1972) እና "ራሮትና የተቃውሞ ድምጽ በዮሐንስ አድማሱ *እስኪ ተጠየቁ* ውስጥ" የሚለው የአዲሱ ዘገዬ (1995) ጥናቶች ናቸው። የአይናለም አበበ (1972) ጥናት ደግሞ፣ "የገሞራው ግጥሞች ትችት በ'በረከተ መርገም' እና በ'የወንድ ያለህ' ላይ የተመሠረተ" የሚል ነው። የSamuel Adal "The Development of Modern Amharic Poetry (1930-1980 E.C)" (1994) እና የያሲን ዑመር "በአማርኛ ግጥሞች የምግባራዊነት ፍልስፍና፣ የተማረው ወጣት የማንነት ጥያቄ (ከ1933-1966 ዓ.ም. ባለው የስነ-ጽሁፍ ዘመን)" (1998) የድህረ ምረቃ ጥናቶች በከፊልም ቢሆን የኮሌጅ ቀን ገጣሚያንን ስላነሱ ለቅኝት የተመረጡ ናቸው። የግርማ ባህሩ፣ "የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የቅስቀሳ ግጥሞች ከ1953-1958" (1976) የሚለው ጥናት በቀጥታ በኮሌጅ ቀን ግጥሞች ላይ ያተኮረ የዲግሪ ማሟያ ጥናት ነው።

ከግርማ ባህሩ ጥናት በቀር ሌሎቹ ሁሉ የሚቃኙት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለዚህ ጥናት ግብዐት (input) ይሆናሉ ተብለው ነው። ለምሳሌ፣ በዮሐንስ አድማሱ ህይወትና ስራዎች ላይ የተሰሩትን ጥናቶች መመርመርና መከለሥ፣ ቢያንስ በ1954 ዓ.ም.

"የኮሌጅ ቀን በዓል" ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ንጉሡ ከሥፍራው እንዳይገኙ እስከ ማድረግ የደረሰ ደፋር አብዮተኛ ግጥም ስለማንበቡ ታሪካዊ ዳራውን ሊጠቁሙ ይችላሉ።

በመጀመሪያ የምንመለከተው፣ "በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የተገጠሙ የቅስቀሳ ግጥሞች ይዘታዊ ትንተና፡- 1953-1958" የሚለውን ግርማ ባህሩ በ1976 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ያቀረበው የዲግሪ ማሟያ ጥናት ነው። እዚህ ላይ፣ ጥናቶቹ የተሰሩበትን የጊዜ ቅደም ተከተል ሳልጠብቅ የግርማን ጥናት ያስቀደምኩት፣ ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ከሁሉም ጥናቶች በተለየ ከእኔ ጥናት ጋር የቀረበ ግንኙነት ያለው በመሆኑ ነው።

ጥናቱ፣ በክፍል አንድ እና ሁለት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የግጥም ውድድር መቼ እንደተጀመረ፣ የቅስቀሳና የሥነ ግጥም ግንኙነት ምን እንደሆነ ለማስረዳት ይሞክራል። በክፍል ሦስት ደግሞ፣ "የሥርዓቱን አስከፊነት" የሚያመለክቱ እና "ሕብረተሰቡን የሚቀሰቅሱ" የሚሉ ሁለት ዋና ዋና የመተንተኛ ፈርጆችን ተጠቅሟል። የሥርዓቱን አስከፊነት ለማመላከት "መደህየት፣ መታረዝ፣ መበዝበዝ የሚያመላክቱ ግጥሞችን" ተንትኗል። "ህብረተሰቡን የሚቀሰቅሱ ግጥሞች ይዘታዊ ትንተና" በሚለው ስር "የወታደሩን ወገን የሚቀሰቅሱ" ያላቸውን ("ሙት ወቃሽህ መጣሁ" እና "ሜዳ የቀረሽው" ከሚሉት ግጥሞች የተቆነጠሩ) ስንኞችን ተንትኗል። "የተማረውን ወገን የሚቀሰቅሱ ግጥሞች ይዘታዊ ትንተና" በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር ደግሞ "ከምሽት እስከ ጐህ" ከሚለው ከመሀመድ ኢድሪስ የተቀነጨቡ ስንኞችን ለመተንተን ሞክሯል።

በ "መደምደሚያ" ክፍል፣ ግጥሞቹ፣ የቀድሞው ሥርዓት ህብረተሰቡ ላይ ግፍና በደል ስለማድረሡ፣ ገገርዎች ህዝቡን "የቁም ስቃይ እያሳዩ ደሙን ሲመጡትና አጥንቱን ሲግጡት" ስለመኖራቸው፣ "መብትና ግዴታ ትርጉም የለሽ፣ ለይስሙላ ብቻ የተቀመጡ" ስለመሆናቸው፣ ህብረተሰቡም ክንዱን አስተሳብሮ ሥርዓቱን ለመገርሰስ መነሳት እንዳለበት የሚቀሰቅሱ፣ የሚያነቁ ፖለቲካዊ ግጥሞች እንደሆኑ ተገልጿል።

> ባጠቃላዩ ግጥሞቹ የሥርዓቱን ጉድ በማጋለጥ፣ የህብረተሰቡን ብሶት በማንፀባረቅ፣ ለሥርዓቱ መገርሰስ ተገቢውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ለታለመለት ዓላማ ግብ መምታት ታላቅ ሚና ተጫውተዋል። ለዚህም የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ አሁን የተያያዘውን አዲስ ሕይወት፣ የደረሰበት ደረጃና ያስመዘገባቸው ድሎች ታላቅ ምስክር ናቸው (ገጽ 43)።

በአጭሩ ጥናቱ ከዚህ በላይ የቀረበውን "መደምደሚያ" የጥናቱ ግኝት አድርጐ አቅርቧል።

የግርማ ጥናት፣ "በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የተገጠሙ የቅስቀሳ ግጥሞች" ላይ በመመሥረቱና የይዘት ትንተና በማድረጉ ከእኔ ጥናት ጋር በጣም ይመሳሰላል። ልዩነቱ፣ በአጠናን ሥልቱ፣ በትኩረት አቅጣጫው፣ በጥናት ወሰኑ ስፋትና ጥልቀት ላይ ሁሉ በግልፅ ጉልቶ ይታያል።

ከአጠናን ሥልቱ ስንጀምር፣ ጥናቱ ይህ ነው የሚባል የአጠናን ሥልት እንደተከተለ አልገለጸም። የትኩረት አቅጣጫውም መደባዊ ባህሪ የሚታይበት ሲሆን፣ ጥናቱ ከመነሻው የሶሻሊዝም ወገንተኝነቱን ተቀብሎ ስለተነሳ ግጥሞቹን ፀረ ፊውዳልና ፀረ ካፒታሊስት ከመሆናቸው አንፃር ብቻ እየመዘነ ተንትኗል። ለምሳሌ፡- "የሶሻሊስቱ ቅስቀሳ … በድርጊት የሚገለፅ ነው። እንደ ካፒታሊስት አገሮች ቅስቀሳ በቅጥፈት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን…?" (ገጽ፥ 16 አፅንኦቱ የኔ ነው) የሚሉ አይነቶች ወገንተኛ ትንታኔዎችንና ማብራሪያዎችን ማየት ይቻላል። ስለዚህ፣ ትኩረቱ ግጥሞቹን እየተነተነ የሚሉትን ሀሳብ መለየትና ከሀሳባቸው ላይ ተመስርቶ መደምደሚያ ላይ መድረስ አይደለም፤ ይልቁንም፣ ጥናቱ ቀድሞ ለመለመላቸው "ፀረ ፊውዳላዊ" ሀሳቦች ይሆናሉ የተባሉ ስንኞችን (ለምሳሌ፣ የአበበ ወርቁ "ሙት ወቃሽህ መጣሁ" ወታደሩ፣ የፊውዳሉን ሥርዓት ተቃውሞ እንዲያምጽ ለመቀስቀስ ብቻ ተብሎ መቅረቡን /ገጽ 38 ይመልከቱ/ ይገልፃል) ብቻ እየመረጠና ዋቢ እያደረገ መተንተን ላይ አተኩሯል። ለዚህ ይመስላል፣ ከግጥሞቹ ሀሳብ ያልወጡ፣ በጥናቱ ሂደት ያልተረጋገጡ እና እንደውም ከጥናቱ ጋር የማይገናኙ የመደምደሚያ ሀሳቦች የተሰነዘሩት። ለምሳሌ፡- "… ግጥሞቹ የሥርዓቱን ጉድ በማጋለጥ፣ … ታላቅ ሚና ተጫውተዋል። ለዚህም የኢትዮጵያ ህብረተሰብ … ያስመዘገባቸው ድሎች ታላቅ ምስክር ናቸው" (ገጽ 43) የሚለውን የመደምደሚያ ሀሳብ ብናይ፣ "ግጥሞቹ የሥርዓቱን ጉድ ስለማጋለጣቸው" የህብረተሰቡ ድሎች እንዴት ትልቅ ምስክር ሊሆኑ ይችላሉ? ተብሎ አመክንዮዋዊ (logical) ጥያቄ ቢነሣ መመለስ አይችልም።

ሁለቱ ጥናቶች፣ በጥናት ወሰናቸውም ይለያያሉ። የኔ ጥናት ከ1951-1960 ዓ.ም. በተገጠሙት በሁሉም የኮሌጅ ቀን ግጥሞች ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ የግርማ ጥናት ግን ከ1953-1958 ዓ.ም. በወጡት ላይ ብቻ ተወስኗል። እዚህ ላይ፣ የኮሌጅ ቀን ግጥሞች ታሪካዊ ዳራቸው ባለመጠናቱ ብዙ የታሪክ መጣረሶች (distortions) ተከስቶባቸዋል የሚል፣ ለጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች በተገለጹበት ክፍል ላይ ለጠቆምኩት ሀሳብ ይህም ጥናት አንዱ ምስክር መሆኑን ማሳየት ይቻላል። ምክንያቱም፣ ጥናቱ "የቅስቀሳ ግጥሞች" ("የኮሌጅ ቀን

ግጥሞች") የተነበቡት ከ1953 ጀምሮ እንደሆነ አድርጐ ይጠቁማል፤ ልክ ባህሩ ዘውዴ (2000፣ 233) በመጽሐፋቸው እንደጠቆሙት ማለት ነው።

ቀጥለን የምናየው፣ "የገሞራው ግጥሞች ትችት በ'በረከተ መርገም' እና በ'የወንድ ያለህ' ላይ የተመሰረተ" በሚል ርዕስ አይናለም አበበ በ1972 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ያቀረበውን ዲግሪ ነው። ይህ ጥናት፣ በኃይሉ ገብረ ዮሐንስ ሁለት ግጥሞች፣ በ"በረከተ መርገም" እና በ"የወንድ ያለህ" ላይ የተመሰረተ ሲሆን የእኔ ትኩረት ከኮሌጅ ቀን ግጥሞች አንዱ በሆነው በ"በረከተ መርገም" ትንታኔ ላይ ይሆናል።

አይናለም፣ "በረከተ መርገም በዓለማችን ላይ የሚታየውን የምጣኔ ሀብት መዛባት ያደረሰውን አስከፊ ገጽታ በማየት ኡኡታ አቅራቢ መሆኑን" የገጣሚውን መግለጫ አጣቅሶ ይመሰክራል።

> በዚህ ውላዊ ዓላማችን ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ፤ በዓለሙ የጋራ ውጤት እኩል መጠቀም ሲገባቸው፤ እኩል አልተጠቀሙበትምና፥ በጋርዮሽ ሲጠቀሙበት ይገባል ማለት ይሆናል። የአንዲቱ ምድራችን ሲቃውንት ለሰው ልጅ ዘር ያበረከቱት ከፍተኛ የጥበብ ጸጋ ለሁሉና ለእያንዳንዱ እንዲደርስ አድርገው ያልፈለሰፉት ከሆነ፥ በኔ ግምት፥ አሁንም ቢሆን፤ ሰዎችን ለመለየት ያቀዱበት ተንኮል ነውና፤ ወንጀለኞች ናቸው ባይ ነኝ። ለዚህም ወንጀላቸው መርገም ሲያንሳቸው ነው (ኃይሉ፣ ገጽ "ረ")።

ይህን ከጠቀሰ በኋላ "... የሰው ልጅ በጋራ ጥረቱ የፈጠረውን ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለጋራ ጥቅም ለማዋል አለመቻሉ በታሪክ ውስጥ መሆን ስላለበት የተከሰተ እንጅ ለዘላለም እንዲህ ሆኖ የሚቀር አይደለም" (ገጽ 25) በማለት የገጣሚውን ሀሳብ ይቃወማል። "መርገም ካለበት ገገር መደቡ እንጂ ሳይንቲስቶችን ለመርገም ከሆነም ... ተቀባይነት የለውም" (ገጽ 25) ይላል። የግጥሟ ስንኞች፣ ሳይንቲስቶችን መርገሟ ከገጣሚው የእውቀት ማነስ እንደሆነ፣ "የግጥም ባለቤት የሆኑት ታህታይ መደቦች የደረሰባቸውን ጭንቅ መከራና ስቃይ በአጠቃላይ ከገገር መደቦች ጋር የተፋጠጡበትን የትግል አውድ አገናዝበው የፃፉት አይመስልም" (ገጽ 25) በማለት ገልጾታል። አይናለም "ከግጥሞቹ መሃል ያለውን ትተን ወደ መጨረሻው እንሂድ ..." ይልና የመጨረሻዎቹን ስንኞች ጠቅሶ፣

> ለመርገም ተፈጥሮ ተረግሞ ያለውን መርገም ላይመልሰው
> ሁለተኛ አልረግምም
> የሆነ ሆኖ እንደሆነ ይኑር ለዓለም ዓለም [ገጽ አልተጠቀሰም]

የሚከተለውን ይላል፤

> እዚህ ላይ ደግሞ ተጠቃለለ። ሲቃውንት ለብቻቸው የሚረገሙበት ምክንያት ተሰጥቶት የርግማን ውርጅብኝ ሲያወርድባቸው ከቆየ በኋላ አሁን ደግሞ ሁሉም የሰው ልጅ የተፈጠረው ሌላውን ለመርገም እራሱም የተረገመ መሆኑ ተነገረን። ስለዚህ ምን ይሻለዋል? መፍትሔውስ ምንድን ነው? የግጥሙስ ፍሬ ሀሳብ

የሆነውስ የምጣኔ ሀብት ፍትህ እንዴት ይገኛል? ብለን ብንጠይቅ ... አሜባ፣ ድንቁርና ... የሚጫወቱበት ጭቁን ህዝብም በመኪና በቴሌቭገርን፣ ... በአውሮፕላን ... በአጠቃላዩ ዘመናዊ ሳይንስ ባፈራቸው እየተጠቀመ የተደላደለ ኑሮ የሚኖረውም በአጠቃላይ ሁሉም የሰው ዘር የአርባ ቀን ዕድሉ የፈቀደችለትን ኑሮ ተቀብሎ ለዓለም ዓለም ይኑር የሚል መልስ እናገኛለን። "የሆነውን ሆኖ እንደሆነ ይኑር ለዓለም ዓለም" (ገጽ 28)።

የአይናለም የጥናት መደምደሚያ፣ "በረከተ መርገም" ገጣሚው እንዳለው "ኡኡታ" አቅራቢ ብቻ ሳይሆን፣ ተስፋ የተንጫለጠበት፣ የፍፃሜው ሙሾ እንደሆነ ተደርጐ (በስሱ፣ ላይ ላዩንም ታይቶ ቢሆን) የቀረበበት አካሄድ፣ ከእውነታው ብዙም አልራቀም። ነገር ግን፣ "በዓለማችን ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ በዓለሙ የጋራ ውጤት እኩል መጠቀም ሲገባቸው ... ሊቃውንቱ ... ያበረከቱት ... ፀጋ ለሁሉና ለእያንዳንዱ እንዲደርስ አድርገው ያልፈለሰፉት ከሆነ ... መርገም ሲያንሳቸው ነው" የሚለው ሀሳብ ተራ የገጣሚው ቅዠት ብቻ ተደርጐ የታየበት ድፍረትና ወቀሳ ግን ትክክል አይመስለኝም።

በመሠረቱ ገጣሚው በ"ብጣቂ" መግለጫቸው ያሰፈሩት ቀደም ሲል የተጠቀሰው ሀሳብ፣ የራሳቸው አይመስለኝም፤ ሀሳቡን እንደ ፍልስፍና ተቀብለው ሊያስተጋቡት ሞከሩ እንጂ። Bloom (1987፡ 256-257) የተባሉት ተመራማሪ፣ የሀሳብን (Idea) ታሪክና ህብራዊ ሚና ከሶቅራጥስ ፍልስፍና ጀምሮ አጥንተው የትውልዱን፣ በተለይ የአሜሪካን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እጣ ፋንታ ባመለከቱበት፣ The Closing of The American Mind በሚለው መጽሐፋቸው፣ የዘመኑ ፈላስፎች ዓለም በከንቱ ዓምልኮ ከምትዳክርበት የጨለማ ዘመን፣ ምክንያታዊነትን ወደሚጠይቀው የሳይንስ እውቀት በተለወጠችበት "የብርሃን ዘመን" (Enlightenment)[6] የተፈጥሮን ሳይንሳዊ እውቀቶችና ግኝቶች ለሰው ልጆች ሁሉ እንዲደርሱ ለማድረግ ሀሳብ ማቅረባቸውን ያወሳሉ። ስለዚህ፣ ገሞራው ያቀረቡት ሀሳብ የሳቸው ላይሆን ይችላል መባሉ እነዚህ ቀዳሚ የብርሃን ዘመን ፈላስፎችና ሳይንቲስቶች ያሉትን በማገናዘብ ነው። ገጣሚው፣ የብርሃናማውን ዘመን ፈላስፎች ሀሳብ ነው የሚያስተጋባው ላልነውም ጉዳይ ዋቢ የሚሆን ከራሱ ከገጣሚው "ብጣቂ" መግቢያ ላይ እናገኛለን፣

የኔ አስተሳሰብ ላለሁበት ጊዜና ስፍራ የኖረ መስሎ መታየቱ ግን ለጠቅላላው የሰው ልጅ ዘር ወገኖቼ ያለኝን የምኞቴን ከፍተኛነት ያሳያል እንጂ፥ የሚያስነቅፈኝ

[6] ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት በ1978 ዓ.ም. ያሳተመው ማርክሳዊ ሌኒናዊ መዝገበ ቃላት ገጽ 286 ላይ "Enlightenment" የሚለውን ቃል "አብርሆት" በማለት ይገልፀዋል።

አልነበረም፡፡ ሆኖም በባለ ብሩሃን ኅሊናዎች ዘንድ ምንጊዜም ቢሆን እንደማያሳፍረኝና እንደማያስነቅፈኝ አምናለሁ (ገጽ ሰ አፅንኦት የኔ ነው)፡፡

ስለዚህ፣ ገጣሚው ያነሳው የፍፁም እኩልነትና ፍትሃዊነት ጥያቄ ተምኔታዊነት (utopianism) ቢታይበት፣ መነሻ መሰረት እንዳለው፣ እንደውም አለምን ከቀየሩት ከብርሃናማው ዘመን ብሩህ ሊቃውንት ሀቲት (Discourse) የተወሰደ እንጂ፣ ገጣሚው በድንገት የፈጠረው፣ የግሉ "ቅዠት" እንዳልነበረ መገንዘብ መልካም ነው፡፡ ባይሆን ያን ያህል የርግማን መዓት ማውረድ ለምን አስፈለገ? ብሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ የሚዳሰሰው፣ ኃይሉ ጀማነህ፣ "የባለቅኔው የአቶ ዮሐንስ አድማሱ የሕይወት ታሪክ" በሚል ርዕስ በ1972 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ያቀረቡት ዲማጽ ነው፡፡ ጥናቱ፣ ዮሐንስ ገና ዩኒቨርሲቲ እንደገባ የሶሻሊስት መፃሕፍት በጥንቃቄ ማንበብ እንደጀመረ (ገጽ 5)፣ ተማሪዎችን ለአመጽ ባነሳሳው ግጥሙ ሳቢያ ተቀጥቶ በ1958 ዓ.ም. ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲመለስ[7] በችሎታው ተመርጦ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎችን በትርፍ ጊዜው እንዲያስተምር እድሉን ቢያገኝም የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ (ተማሪዎችን የማነሳሳት ተግባር) በመጣሱ ከማስተማር ስራው እንደታገደ፣ የዮሐንስ ግጥሞች ሜታፊዚክሳዊና ፖለቲካዊ ተብለው በሁለት ተከፍለው እንደሚታዩ፣ ዮሐንስ ገጣሚ ብቻ ሳይሆን ሐያሲ እንደነበር፣ ሳይፈልግ በሄደበት በ"ዓለማያ" ዩኒቨርሲቲ ሊቃውንትም ብዙ ይማረርባቸው እንደነበር፣ በ"እስቲ ተጠየቁ" ግጥሙ የፊውዳሉ ሥርዓት የበሰበሰ መሆኑንና መገርደሱ የማይቀር መሆኑን (በ1954 ዓ.ም. ነበር) ማመላከቱ፣ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ግጥሞቻቸውን እንዳያቀርቡ ሲያስፈራሩ ሌሎቹ ፈርተው ሲያንገራግሩ፣ ዮሐንስ ግን አሻፈረኝ ብሎ በቀዳሚነት [የገደል ስር አጥንትን] ማቅረቡ፣ በቃልና በጽሑፍ መጠይቆች ያገኘውን መረጃ አጠናቅሮ አቅርቧል፡፡

አጥኚው፣ የተጠቀመባቸው የመረጃ ምንጮች አስተማማኝ ይመስላሉ፡፡[8] በአጠቃላይ ጥናቱ ብዙ የተለፋበት፣ አጥኚው ስለማን እያጠና እንደሆነ ጠንቅቆ ያወቀበትና ቆርጦ የተነሳበት፣ ወዘተ. እንደነበር መመስከር ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ቀደም ሲል እንደጠቀስነው

---

[7] ዮሐንስ አድማሱ፣ በ1958 ዓ.ም. የተመለሰት ከቅጣት ሳይሆን ከካሊፎርኒያ መሆኑን ዮናስ አድማሱ (ዶ/ር) ነግረውኛል፡፡

[8] ኃይሉ ጀማነህ፣ ለጥናታቸው የሚሆኑ መረጃዎችን ያሰባሰቡት በአብዛኛው በቃልና በጽሑፍ መጠይቆች ሲሆን፣ ከጠየቋቸው ሰዎች መካከል የባለቅኔውን ወላጅ አባት፣ አስተማሪዎቹን፣ ተማሪዎች (ለምሣሌ፦ ክፍል ውስጥ ባያስተምሯቸውም መምህርነቱን አምነው የተቀበሉና "ስንብት ለጋሼ ዮሐንስ" የሚል ግጥማቸውን ጭምር ለአጥኚው የሰጡት ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ)፣ ታዋቂ ደራሲዎችንና ሃያሲዎችን (ለምሣሌ፦ ፀጋዬ ገ/መድህን እና አስፋው ዳምጤ)፣ የቅርብ ባልንጀሮችና የሥራ ባልደረቦች (ለምሳሌ፡ ዳኛቸው ወርቁ እና ዶ/ር አብርሃም ብስራት) በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

የኮሌጅ ቀን በዓል እና የኮሌጅ ቀን ገጣሚያን ታሪካዊ ዳራ ባለመጠናቱ በዚህም ጥናት ብዙ የተዛቡ ታሪካዊ ሁነቶች ያጋጥማሉ። ለምሳሌ፣ ዮሐንስ፣ በኮሌጅ ቀን በዓል ላይ "የገደል ስር አጥንት"ን፣ "ግንባሩን ሳያጥፍ በንጉሱ ፊት አንቧል" (ገጽ 32) የሚል የተሳሳተ መረጃ ቀርቧል። ዮሐንስ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንቱ እንዳያቀርቡ እያስጠነቀቁዋቸው አሻፈረኝ ብሎ ያቀረበው ግጥም "እስኪ ተጠየቁ" እንጂ "የገደል ስር አጥንት" አልነበረም። ዮሐንስ "እስኪ ተጠየቁ" ባቀረበበት ጊዜ ደግሞ ንጉሱ የቃላት ጦሩን ፊርተው መቅረታቸው ይታወቃል፤ እዚህ ላይ የገጣሚያኑ የመጀመሪያ አብዮታዊነት ያየንበት ወሳኝ ታሪካዊ ሁነት መሆኑ ሊስተዋል ይገባ ነበር።

ሌላው የዚህ ጥናት ውስንነት፣ የአጥኚው መደባዊ ወገንተኝነት ጉልቶ መውጣቱ ነው። አጥኚው የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም አቀንቃኝ ስለመሆኑ ሳይጠየቁ የሚመሰክሩ በርከት ያሉት ስሜታዊ አገላለፆቹ ያሳብቁበታል፤ ለምሳሌ፣ "እንደ ዮሐንስ ቅኔ (የአርዩ) ቆንጆ የኛዋ እማማ ሳትሆን ትቀራለች? <u>አዎ ለንጉስ ኃይለ ሥላሴ ፍትወት ማርኪያ የሆነችው</u> እሷው ነች፤ - ኢትዮጵያ" (አጽንኦቱ የኔ ነው፤ ገጽ 76) የሚለውን ስናይ ጥናቱ፣ ወገንተኛ ሳይኮን፣ ነፃ ሆኖ የተሰራ መሆኑ ያጠራጥራል። "የኦርዮን ሚስት"፣ ለንጉሡ "ፀያፍ" ግብር ማሟያ ተምሳሌት መሆኗም ተገቢ ነገረ ማንፀሪያ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል። በመሠረቱ፣ ኦሪዮንን አስገድሎ ሚስቱን ቤርሳቤህን ያገባው ንጉስ ዳዊት፣ ጥፋቱን አምኖ በመፀፀቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን እንዳገኘ ይታወቃል። ዳዊት ይቅርታን ካገኘ በኋላ የኦሪዮን ሚስት የነበረችው ቤርሳቤህ ከዳዊት ጋር ፊቅዳ መኖሯን ቀጥላለች። ታዲያ፣ በቤርሳቤህ የተመሰለችው "ኢትዮጵያ" እና በንጉስ ዳዊት የተመሰሉት "አፄ ኃይለ ሥላሴ" መካከል ያለው ግንኙነት (እግዚአብሔራዊውን ጉዳይ ትተን እንኳ) ከግርማ ፍካሬ ጋር በንጽጽር ቢታይ የአጥኚውን ስሜታዊነት የሚጠቁም ይመስለኛል።

በመቀጠል የምናየው፣ አዲሱ ዘገዬ "ራሮትና የተቃውሞ ድምጽ በዮሐንስ አድማሱ *እስኪ ተጠየቁ* ውስጥ" በሚል ርዕስ በ1995 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ያቀረበውን ዲማጽ ሲሆን፣ "ራሮት" የሚለውን የጥናቱን ቁልፍ ቃል "የርህራሄ ስሜት" በሚል ፍች እንደተገለገለበት ጠቁሟል።

ይህ ጥናት በሦስት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን ምዕራፍ አንድ፣ የጥናቱን መቅድሞችና ክለሳ ድርሳናት ይዟል። በመቅድሙ ውስጥ ደግሞ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፤ ዮሐንስ፣ በኮሌጅ ቀን ክብረ በዓል ላይ በተደጋጋሚ አሸናፊ ገጣሚ መሆኑ ትኩረቱን ስቦት እንደነበር አጥኚው ጠቁሟል። ምዕራፍ ሁለት፣ "ራሮቱን የሚያስማላቸው የተለያዩ

የማህበረሰብ ክፍሎችና በራሮቱ መንስኤ ያቀረበባቸው የይሆናል መፍትሔ ሀሳቦች"ን ይዟል። የመፍትሔ ሀሳቦቹን በምፀታዊ ዘይቤና እንዳለ በገለፃዊ ዘዴ በቀጥታ በማሳየት እንዳቀረባቸው ተደርጐ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል። በምዕራፍ ሦስት ለተቃውሞ ድምፆቹ መነሻ የሆኑ ማህበራዊ እውነታዎችና ተቃውሞዎቹ የተገለፁበት አበይት መንገዶች ቀርበዋል። ማህበራዊ እውነታዎቹ በወቅቱ ከነበረው ከገዢው መደብ ፊላጭ ቆራጭ ፊውዳላዊ ሥርዐት አንፃር ተቃኝተው ቀርበዋል። ተቃውሞውን የገለፀባቸው አበይት መንገዶች ደግሞ ምፀታዊና ቀጥታዊ እንደሆኑ ተደርጐ በተጠየቃዊ ትንታኔ ተደግፊው ተብራርተዋል።

የአዲሱ ጥናት፣ አመክንዮዋዊ (logical) የሆኑ የአጠናን ዘዴዎች ተከትሎ፣ በአላማው ላይ የነደፋቸውን ርዕሰ ጉዳዮች በትንታኔ አስደግፎ መደምደሚያ ላይ የደረሰ፣ ደረጃውን የጠበቀ ሥራ ነው ማለት ይቻላል። "ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አንድም ጥሩ የመመረቂያ ጽሁፍ አይገኝም!" የሚል በጥናት ያልተደገፈ ደፋር አስተያየት ለሚሰጡ አፈ-ልሂቃን በአለበት እርከን ሊሞግት የሚችል ተጠቃሽ ሥራ ይመስለኛል።

በሌላ በኩል፣ ጥናቱ በራሱ ስናየው ደረጃውን የጠበቀ ተመስጋኝ ሥራ ቢሆንም፣ ከኃይሉ ጀማነህ (1972) ጥናት ጋር በብዙ መልኩ የሚመሳሰል ይመስላል፤ ስላላቸው አንድነትና ልዩነት ለመግለፅ የተጠቀመበት መንገድም ብዙም ሚዛን አይደፋም። በርግጥ የኃይሉ ጥናት፣ ክለሳ ድርሳናት ያልተሰራበት በመሆኑ፣ የአዲሱ ደግሞ ክለሳ ድርሳናት በወጉ በማቅረቡ ይለያያሉ። አጠቃላይ ዋነኛ ሥራቸው ላይ፣ ማለትም ግጥሞችን መተንተን፣ የዮሐንስን የሕይወት ታሪክ አዛምዶ መከለስ በሚመለከት ይመሳሰላሉ። ልዩነታቸው ኃይሉ የዮሐንስን ሁለት ጥናታዊ ፅሁፎቹን ጨምሮ በሁሉም ግጥሞቹ ላይ ትንተና ሲያደርግ፣ አዲሱ ግን ራሮታዊ ይዘት ያላቸውን ግጥሞች ብቻ መተንተኑ ነው። በሌላ አነጋገር የአዲሱ ሥራ በኃይሉ ሥራ ውስጥ የሚጠቃለል ይመስላል።

የዮሐንስን የሕይወት ታሪክ በሚመለከት ሊጠቀስና ሊመሰገን የሚገባው የኃይሉ ሥራ ነው። አዲሱ ኃይሉ ከገለፀው መካከል የተወሰነውን ጠቆመ እንጂ ከተባለው ውጭ አዳዲስ መረጃዎችን ተጠቅሞ ያመላከተው አዲስ ነገር የለም። እንደውም ኃይሉ የሠራውን የታሪካዊ ሀነት ሥህተት እሱም ደግሞታል፤ ዮሐንስ "የገደል ሥር አጥንት" የተባለውን ግጥሙን በኮሌጅ ቀን ክብረ በዓል ላይ በማንበቡ፣ "የተሸለመው ሽልማት ከዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ መባረር ነው" (ገጽ 11) በማለት ሁለቱም የገጣሚያኑን የተዛባ ሥነ ፅሁፋዊ ታሪክ ሊታደጉት አልሞከሩም።

በመጨረሻም፣ የSamuel (1994) እና የያሲን ዑመር (1998) የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት በቀጣዩ ክፍል ከቀረበው የሥነ ፅሁፍ ታሪክ እና የወቅቱ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አውድ ጋር እየተናበቡ፣ ሲያስፈልግ በምስክርነት፣ ካልሆነ በታሪክነት ይዳሰሳሉ።

2.2 ከ1950-1960 ዓ.ም. ያለውን ሃገራዊ ሁኔታ የሚጠቁሙ የአማርኛ ሥነ ጽሁፎች፣ ከማህበረ ፖለቲካዊ አውዱ አንጻር ሲቃኙ

የኮሌጅ ቀን ግጥሞቹን በወጉ ለመረዳት፣ የቀረቡበትን ዘመን (ከ1950-1960 ዓ.ም.[9]) አሻራ ያነሱ ሌሎች የሥነ ፅሁፍ ሥራዎችን ከነበረው ማህበራዊና ፖለቲካዊ አውድ ጋር እያገናዘቡ መቃኘት እንደሚገባ የመስኩ ባለሙያዎች ይመክራሉ (Yonas, 2001: 82)። የአንዲት ሃገር ሥነ ፅሁፍ ከሃገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አውዶች ተነጥሎ ሊታይ እንደማይገባው ይታመናል። ይህን አስመልክቶ፣ ዘሪሁን (1985) የሚከተለውን ሀሳብ በአፅንኦት ገልፀዋል።

> ያንድ ዘመን ሥነ-ፅሁፍም (ከሚፈፀሙት) ታሪካዊ ክስተቶች ውጭ አይጠናም፤ በአንድ አገር በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ዘመን የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በስነጽሁፍ እድገትም ሆነ ውድቀት ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸው አይቀርም። የአንድን ስነጽሁፍ ሁኔታ ይበልጥ ለማወቅና ለመረዳትም የበቀለበትን፣ የኖረበትንና ያለፈበትን ማህበራዊ ታሪክ አበይት መልኮች ማጤን ያስፈልጋል (ገጽ 35)።

የባለሙያዎቹን ምክር በመቀበል፣ በምዕራፍ ሦስት፣ የዩኒቨርሲቲውን አውድና የገጣሚያኑን ዳራ ከሚያቀነቅኑት የጥናት ውጤቶች ውጭ ያሉትን አጠቃላይ ሃገር አቀፍ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አውዶችን፣ በገጣሚያኑ ላይ ከሚያሳድሩት ተፅዕኖ አንፃር እየተመረመሩ በቀጣዩ ክፍል በአጭሩ ተቃኝተዋል።

2.2.1 ከ1950-1960 ዓ.ም. የታዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ክስተቶች

ከ1950ዎቹ ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም. አብዮቱ መባቻ ድረስ የመሬት ሽያጭ እየተስፋፋ የመጣበት ጊዜ ነበር። የሽያጩ መጧጧፍ የግል ይዞታን እያጠናከረ መጣ። በግል ይዞታ አብራክ ውስጥ፣ ከምንጊዜውም በላይ ጭሰኝነት እየተስፋፋ ሄደ። በተጠቀሱት ዓመታት፣ "ከጠቅላላው ባለመሬቶች ውስጥ 25 ከመቶው እያሳረሱ እነሱ በከተማ የሚኖሩ ነበሩ።" ጭሰኛው፣ ካመረተው ላይ ለባለ መሬቱ ሩቡን፣ ሲሶውን ወይም ግማሹን

---

[9] ከ1950-1960 ያሉት ዓመታት የተመረጡት፣ የኮሌጅ ቀን ግጥሞች ለንባብ የቀረቡበት ጊዜ በመሆኑና ሥራዎቹ የወጡበትን ዘመን አሻራ ያንፀባርቃሉ ተብሎ ስለሚታሰብ፣ የተጠቀሰውን የጊዜ ምዕራፍ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን፣ ከተጠቀሱት ዓመታት አጠቃላይ ሃገራዊ ክስተቶችና አውዶች ጋር እያገናኘን በመመርመር ለጥናት የተመረጡትን ግጥሞች ለማናበቢያነት እንድንገለገልባቸው ሲባል ነው።

ከመስጠቱም በላይ የአስራትና የመሬት ግብር ሁሉ እንዲከፍል የሚገደድበት ብዙ አጋጣሚ ነበር። ይህን በመሰለው በሰፋፊ የመሬት ይዞታ ላይ የተመሰረተው የአፄው ሥርዓት የገነነ የመደብ ክፍፍል እየፈጠረ መጣ። በጭሰኛውና በፊውዳሉ መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት ከመሥፋቱ አልፎ አመጽ ሁሉ ወደ መቀስቀስ መሸጋገር ጀመረ። "መንግስት ትኩረቱን ወደ ተራው ገበሬ ያዞረው እጅግ ዘግይቶ" ነበር (ባህሩ፣ 2000፥ 200-205)።

ይህ የፊውዳል ስርዓቱ፣ ህዝቡ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ፣ ችግሩን ሳያማርር እንደ አንድ የኑሮ ዘይቤው ተቀብሎ እንዲቀጥል፣ ሃይማኖትን እንደ መግዣ መሳሪያ ይጠቀም ነበር። የቤተ ክህነት ሰዎች፣ ከንጉሳውያኑ ቤተሰቦችና ከሥርዓቱ አስፈፃሚዎች ጋር በአንድ ወግነው በአድርግ አታድርግ "የፈጣሪ ትዕዛዝ" እያስፈራሩና እየገዘቱ የሰፋፊ መሬት ባለቤት የሆኑበትን ሁኔታ ታሪክ መዝግቦታል። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የፊውዳሉ ሥርዓት አቀንቃኝና አስፈፃሚ በመሆን ትልቅ ሥልጣን የተቆናጠጠችበት አጋጣሚም እንደነበር እነ Levine (1965, 212) ያስረዳሉ።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ ህዝቡ በሥርዓቱ ላይ እንዳያምፅ፣ ዛሬ በምድር ላይ የሚደርስበት ግፍና መከራ ለሰማያዊው ህይወቱ መሰረት እንደሚሆን መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ እየጠቀሱ፣ ("ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ" ሮሜ.13 ፥ 1 የሚሉት አይነት ጥቅሶችን ልብ ይሏል) በመስበክ፣ በመገዘትና በመገሰፅ የቤተክህነት ኃላፊዎችም ትልቅ ድርሻ ነበራቸው።

የ1948ቱም ህገ መንግስት፣ "ከ1923ቱ በበለጠ አኳኋን ለፍፁማዊ አገዛዝ ህጋዊ መሰረት" በመስጠት የሥርዓቱን ቀጣይነት አይቀሬ መሆኑን አፅንኗል። "የመናገርና የፕሬስ ነፃነትን የመሰሉ ሰብአዊ መብቶችን የሚያስከብሩ አንቀጾች" ቢታከሉም፣ "በሕግ መሰረት"፣ "በሕግ ተዘርዝሮ በሚወሰነው መሰረት" በሚሉ አፋኝ ቅዕሎች እየተጉላመሱ፣ እንዳያፈናፍኑ ተደርገው ስለተቋጠሩ ለይስሙላ መጠቀሳቸውን ባህሩ (2000፥ 217) ጠቁመዋል። እንደውም፣ የአፄው መንግስት፣ ዜጎችን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ለመቆጣጠር እንዲያመቸው፣ በ1952 ዓ.ም.፣ "ልዩ ካቢኔ" የተባለ የስለላ ድርጅት በቁንጮነት አዋቅሮ ነበር (ባህሩ፣ 2000)።

የሥርዓቱ መረን የለቀቀ አፋኝነትና ወግ አጥባቂነት፣ ህዝቡ የፖለቲካ አመለካከቱን በተደራጀ መንገድ ሁሉ እንዳይገልፅ ከለከለ። ይህ ፖለቲካዊ አውድ ደግሞ ይበልጥ

ተጠናከረና የታህሳሱ (1953) የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ እንዲደረግ መሰረት ሆነ። ምንም እንኳ አማፅያኑ ቢወገዱምና ሙከራው የጥቂት ውስታ ቢስ ዜጐች ሴራ መስሎ ለመንግስት ቢታየውም፣ የተቀጣጠለው የለውጥ ችቦ እንደታሰበው በቀላሉ የሚጠፋ አልነበረም። ህዝቡ፣ "እንደ ሺ ቀኖች በግ ሆኖ ከመኖር አንድ ቀን አንበሳ ሆኖ መሞት ይሻላል" የመሳሰሉ መፈክሮች እየፃፈ ወረቀት መበተን ጀመረ (ባህሩ፣ 2000፥ 229)። ወዲያው፣

"አውሮፕላን ሲሄድ ሰማይ ለሰማይ፣
የድሆች ጠበቃ መንግስቱ ነዋይ።" (ዘሪሁን፣ 1985፥ 34)

እየተባለ ሁሉ መዘፈን ተጀመረ። በ1955 በአፄ ኃይለስላሴ ሊቀመንበርነት የተመሰረተው "የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት" የሥርዓቱን "ጥንካሬ" ለውጪ ማህበረሰብ ቢገልጥም፣ ከ1954 ጀምሮ፣ በኤርትራ የተካሄደው የትጥቅ ትግል ማዕከላዊ መንግስቱን ከምንጊዜውም በላይ እየተፈታተነው መጣ።

"በ1958 ዓ.ም. የታወጀው ሦስተኛው የመሬት ግብር ዐዋጅ በመንግስትና በገበሬ መካከል ለዘመናት" (ባህሩ፣ 2000፥ 202) ሰፍኖ የቆየውን ጉልተኛነት ለማስወገድ፣ አመፆችን ለማብረድ ይችላል ቢባልም እንደታሰበው ግን አልሆነም። ለሃገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ከሆነው ግብርና የሚገኘው ገቢ በአጠቃላይ 7 በመቶ ያህል ብቻ ስለነበር፣ የእርሻ ገቢን ለማሳደግ ሲባል በ1960፣ "የእርሻ ገቢ ታክስ" በመታወጁ፣ የገበሬዎች አመጽ እንደ አዲስ ተለኮሰ [ለምሳሌ፣ የጐጃም ገበሬዎች በ1960 ዓ.ም. አምፀው ነበር።]። እስከ አሁን የተገለፁትና ሌሎች አመጾችም እየተጠናከሩ ሄደው የ1966ቱ አብዮት ፍንዳታን እውን አደረጉ (ባህሩ፣ 2000፥ 236)።

2.2.2 ከ1950-1960 ዓ.ም. ያለውን ሃገራዊ ሁኔታ የሚጠቁሙ የአማርኛ ስነ ጽሁፎች ቅኝት

"1950ዎቹ ከቀዳማዊዎቹ አስርት ጋር ሲነጻጸሩ በስነጽሁፍ የተሻለ ሁኔታ የታየባቸው ናቸው። ስነ ምግባራዊ በሆነ መልክ መስበክና ማስተማር እየቀነሰ የማህበረሰቡን እውነታ ማሳየት የተጀመረበት ጊዜ ነው" በማለት ዘሪሁን (1985፥ 34) Albert S. Gerard'ን (1971) ጠቅሰው ተናግረዋል። እንደተባለውም፣ በዚህ የጊዜ ምዕራፍ የወጡ የሥነ-ፅሁፍ ሥራዎች፣ የማህበረሰቡን ማህበራዊና ፖለቲካዊ እውነቶች ለመግለጥ፣ ለማሳየት እንደታተሩ ሌሎች መረጃዎችም ይጠቁማሉ፤ ለምሳሌ፣ Fikrie, (1983፡ 129) እነ

በዓሉ ግርማን፣ ዳኛቸው ወርቁን፣ ሀዲስ አለማየሁን፣ አቤ ጉበኛን እና ሌሎች ጥቂት ደራሲያንን ጠቅሰው የደራሲዎቹ ሥራዎች ማህበራዊና ፖለቲካዊ እውነቶችን እንደሚያሳዩ አስረድተዋል።

በዚህ ዘመን የወጡ ድርሰቶች፣ ለጋብቻ ሀብትና ዘር እንደዋነኛ መለኪያ መቆጠር እንደሌለበት፣ ለትዳር መስፈርቱ ፍቅር እንደሆነ፣ ከጥንቱ ባህል ለዘመነኛው ኑሮ ሁሉ የሚጠቅሙ መልካም ማህበራዊ እሴቶች ስላሉ ትውልዱ እነዚህን አጥብቆ መያዝ እንዳለበት፣ ወዘተ. የሚሰብኩ ናቸው። "ከነዚህ በተጨማሪም የፍትህ መዛባትን፣ አድልዎን ... የሚያወግዙ፣ በገጠርና በከተማ መካከል ያለውን የኑሮ መራራቅ የሚያሳዩ" እንደሆኑ የዘሪሁን (1985 ፥38) ጥናት ይተነትናል።

በዚህ ዘመን ከወጡ ድርሰቶች፣ መካከል የታደሰ ሊበን አጭር ልቦለዶች እንደ ቀዳሚው ዘመን ስነፅሁፎች ስነምግባር ከመስበክ ወጥተው፣ የማህበረሰቡን እውነት ለማሳየት እንደቻሉ Fikrie (1983፡ 148)[10] በጥናታቸው ገልፀዋል። ታደሰ ሊበን ከMolvaer (1997) ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ "ትንሹ ልጅ" (መስከረም ከሚለው መድበል የተወሰደ 1949) በሚለው አጭር ልቦለዳቸው በዘመኑ የነበረውን የመናገር ነፃነት እጦት ለማሳየት እንደሞከሩ ጠቁመዋል (ገጽ፡ 310)።

ጥናቶች እንደመሰከሩት በዚህ ዘመን፣ ሥርዓቱን በብዕሩ በመድፈር ብዙ መከራና እንግልት ያሳለፈ ደራሲ ቢኖር አቤ ጉበኛ ነው ማለት ይቻላል። ከታህሳሱ መፈንቅለ መንግስት በፊት፣ በጥቅምት 1953 ዓ.ም. ያሳተመው የሮም አወዳደቅ የተሰኘው የተውኔት መጽሐፍ የመንግስታዊ ሥርዓቱን እጣ ፋንታ አመላከተ፤ ለሥርዓቱ መውደቅ ተጠያቂዎቹ "መኳንንት፣ ነገስታት፣ ባላባትና ካህናት" መሆናቸውን አጋለጠ፤ ከሰሳቸውም። ጥር፣ 1955 የታተመው አልወለድምም፣ "የዚያን ሥርዓት አይቀጥሬነት በግልፅ በማጋለጡ አገዛዙን በብርቱ ደፍሮታል።" መጽሐፉ ዳግመኛ እንዳይታተም፣ የታተመውም ተሰብስቦ እንዲቃጠል ቢደረግም፣ ህዝቡ ግን በድብቅ እያባዛ ያነብ ነበር - ዋጋው 50 እና 60 ብር ቢደርስም። ድሬደዋ ውስጥ ሲያበዛ የተገኘ አንድ ሰውም አምስት ዓመት ታስሯል (ኤልያስ፣ 1991፥ 10 እና 11)።

---

[10]ፍቅሬ ቶሎሣ፣ እንደ ልብ ግራና ቀኝ፣ ፊትና ኋላ ተፈክሮ ሊነበብ የሚችለውንና ሀገራዊ ምስል የሚያመላክተውን [Narrating Ethiopia: A Panorama of the National Imaginary" የሚለውን የዮናስን የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት ይመልከቱ] ጠቢያን (ልቦለድ ታሪክ) "ሀገረ ሰባዊ ተረት" (Folktale) በማለት ሲገልጹት፣ በአንፃሩ የታደሀን "ትንሹ ልጅ" እንዴት አድርገው ይህን ያህል ለጥጠው እንደፈከሩት ወይም የMolvaerን መረጃ እንዳለ እንደተቀበሉት ሲታይ ጥያቄ የሚያስነሳ ይመስለኛል።

ሌላው በዚህ የጊዜ ማዕቀፍ መነሳት ያለበት የወቅቱን ሁኔታ ጠቋሚ መጽሐፍ፣ የሀዲስ አለማየሁ ፍቅር እስከ መቃብር ነው። Fekade (1988: 232) የፊውዳሉን ሥርዓት የሞገቱ፣ እነ አበጀን የመሰሉ ያመፁ ገበሬ ገፀባህሪያትን ዋቢ እያደረጉ፣ በሃገረኛው አማካይነት፣ ለሃገር በቀሉ ችግር፣ ሃገር በቀል መፍትሔ ለመጠቆም የሞከረ የመጀመሪያ መጽሐፍ ብለውታል።

በዚህ የዘመን ምዕራፍ ውስጥ ያለው የአማርኛን የሥነ ዕሁፍ ታሪክ ሲቃኝ፣ አይቀሬ የሆነ፣ በአንድ ተቋም የተሰበሰበ (የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ) ነውጠኛ፣ ተሟጋች ገጣሚ ትውልድ አለ። ይህን ወኔያም ትውልድ ዮናስ አድማሱ፣ "የአማርኛ ሥነ-ዕሁፍ ጉዞ" በሚለው "ጥናታቸው" እንደሚከተለው ገልፀውታል።

> … በፊተኛው ትውልድ እምነት ተጋርዶ "ሰማይ አይታረስ፣ ንጉስ አይከሰስ" በማለት ተንጠልጥሎ የቀረውን፣ በቋረኛው ወግ ይመስል "ሰማይ በመብረቅ ይታረሳል፣ ንጉሥም በነውሩ ይከሰሳል" የሚለውን ብሂል መድፊያ አድርገው የብዕር ጦራቸውን፣ የጎሊና ሚዛናቸውን ይዘው ተነሱ። አንዱ "ተጠየቁ" አለ፣ ተጠየቁ ብሎም አልቆመ፣ "እኛም ራሳችን እንጠየቅ" ሲል፣ ሌላው "እምቧ በሉ ሰዎች" ብሎ ምሬቱን ገለጸ - የራሱንም ትውልድ ፊት ለፊት፣ ኮስተር መረር ብሎ ሞገተ። ሌላው ጽንፍ ሄዶ የ"መርገም በረከት" ይገፍላችኋለሁ ብሎ የገሞራ ድምጹን አሰማ። … ሌላው "ኢትዮጵያዊው ማነው?" ብሎ ኢትዮጵያዊነትን ፍለጋ ሁሉንም ጠየቀ። የመረረው … "ምላሱን ብቻ እንዲተዉለት" ለመነ … "ሙት ወቃሽህ መጣሁ" [ም] ብሎ አስጠነቀቀ። ሌላው "ሜዳ የቀሩትን" ዘከረ። ብቻ ወረደ፣ አወረዱት፣ … ስድሳ ስድስት ሦስተኛውን 6 ጥሎ … መጀመሪያ እንደ ካፊያ፣ ከዚያ እንደውሽንፍር፣ ከዚያ እንደ ዶፍ፣ እንደ ማዕበል እያለ መጣ መጣና ያደረገውን አድርጐ እቆመበት ቆመ (<u>መድበል ጉባኤ</u>፣ 2001፥ 16)።

ከዚህ በላይ በቀረበው በዮናስ ማብራሪያ በስልት የተጠቆሙት የኮሌጅ ቀን ግጥሞች በሌሎች ጥናቶችም ተተንትነዋል። Samuel (1994) ከ1950-1980 ያሉትን ግጥሞች ባየበት "The Development of Modern Amharic Poetry" በሚለው ጥናቱ፣ ከኮሌጅ ቀን ገጣሚያን መካከል ዮሐንስ አድማሱን፣ ዳኛቸው ወርቁንና ኃይሉ ገብረ ዮሐንስን አካቶ፣ ሥራቸውን መርምሯል። የገጣሚያኑ ሥራዎች ባይተዋርነት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ፅንፈ ባዶነት (Nihilism) እንደተጠናወታቸውም ጠቁሟል። ሥራዎቻቸው፣ ከዘመናዊ (modern)[11] የአማርኛ ግጥሞች መካከል በመጀመሪያው ረድፍ እንደሚመደቡም አረጋግጧል። የያሲን ዑመር (1998) ጥናት ደግሞ፣ የዮሐንስን እና የዳኛቸውን ግጥሞች ጨምሮ ተመልክቷል። ከ"1933-1966 ዓ.ም. ባለው የሥነ-ዕሁፍ ዘመን" ላይ ተመስርቶ

---

[11] Samuel (1994) በጥናታዊ ጽሑፋቸው፣ "Modern implies a historical discontinuity, a sense of alienation, of loss, and despair. […] It rejects traditional values and assumption and it rejects equally the RHETORIC by which they were communicated." በማለት <u>A Hand Book of Literature</u> (1980, page 274) ጠቅሰው "Modern" (ዘመናዊ) የሚለውን ቃል ትርጓሜ ጠቁመዋል።

በተደረገው በዚህ ጥናት፣ የዮሐንስና የዳኛቸው ግጥሞች፣ የማንነት መለዮ እጦት"፣ "የሀገርኛ መለዮ እጦት" እና "ግለ ፍርቅነት (self-alienation)" የተጠናወተውን የወቅቱን ትውልድ ውስጣዊ ማንነት እንደሚያሳዩ አስረድቷል።

2.3 ግጥም እንደ ትግል መሣሪያ

"የኮሌጅ ቀን ግጥሞች"፣ "የማህበራዊ ሂስ" (Social criticism)፥ "የፖለቲካ" (political)፥ "የተቃውሞ" (protest)፥ "የፕሮፓጋንዳ" (propaganda) "የፍልስፍና" (philosophical)፥ ግጥሞች ናቸው ማለት ይቻላል። በተለይ ከ1953 በኋላ የቀረቡት ደግሞ የፖለቲካና የተቃውሞ ግጥሞች እንደሆኑ ጥናቶች ይጠቁማሉ (ክፍሉ፣-፤ Balsvik, 2005)። ስነገሩ፣ "All Literary writing is ultimately a form of protest" (አዲሱ፥ 1995፥10) በማለት ሁሉም የስነ ጽሁፍ ሥራዎች የተቃውሞ መልክ እንዳላቸው የሚገልፁም አሉ።

ተቃውሞን፣ ፕሮፓጋንዳን፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሂሶችን ወዘተ. ለማቅረብ ደግሞ ከሥነፅሁፍ ዘውጐች ውስጥ ግጥም የበለጠ ተመራጭ እንደሆነ ባለሙያዎች ይገልፃሉ። Hight የተባሉ ባለሙያ <u>The Power of Poetry</u> (1960) በሚለው መጽሐፋቸው፤

> It is easier to write prose of any kind than it is to write poetry of any kind, it is actually more difficult to convey a propaganda message in prose than it is in poetry. This is because poetry (like music) makes a more immediate appeal to the emotions, while prose asks to be meditated and criticized. ... prose makes us think; poetry sets our heart's beating faster and more strongly (pp. 197).

በማለት ግጥም፤ ስሜትን ለመግለፅ፣ የልብን ሀሳብ እየተናገሩ ለመታገል ያለውን ኃይል (power) አስረድተዋል። ከፖለቲካዊ የተቃውሞ ግጥሞቹ ገጣሚያን መካከልም፣ ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ፣ በ<u>ፍንዳታ</u> ቁ. 1 ("በረከተ መርገም") መግቢያ ላይ፣ "... ፅንሰ ሐሳብ ሲብላላና ሲጋጋል ከቆየ በኋላ በልዩ ልዩ መልክ በአንደበት በኩል ይፈነዳል። አንደበት ሐሳብን ከሚገልፅባቸው አይነቶች አንደኛው መንገድ ግጥም ነው" (ገጽ፥ ተ) በማለት እነዚህን የተለየ ስሜትና አላማ ያፈነዱበትን የትግል መሳሪያዎቹን (ግጥሞቹን) "ፍንዳታ" በሚል እንደሚጠራቸው ጠቁሟል።

"ፍንዳታ" የሚለው ቃል በአንዳች ኃይል መታመቅን፣ መብላላትና መጋጋልን ተከትሎ የሚመጣ ክስተትን ይወክላል። "መታመቅ" ደግሞ መደባዊ ባህሪ አለው ማለት ይቻላል። "የሚያምቅ" እና "የሚታመቅ" ነገር አለ። "የሚታመቀው" ሲፈነዳ የሚወጣው

ነገር፣ መታመቁን እስከወዲያኛው የሚያስቀር ወይም ለማስቀረት የሚጥር ነገር ይሆናል። ይህ በፍንዳታው የሚፈስ ነገር የመታገያ፣ የመቀስቀሻ ንጥረ ነገር አለው። በቅስቀሳ ወይም በተቃውሞ ጊዜ የሚወጣው ንጥረ ነገር "ሀሳብ" (Idea) ወይም "ርዕዮተ ዓለም" (Ideology) ሊሆን ይችላል። Havlick (1976) የሚባሉ ባለሙያ፣ "Without ideological and concrete contents agitation degenerates into phrase and mere noise." (ገጽ 67) በማለት ርዕዮተ ዓለምና ይዘት የሌለው ቅስቀሳ (ተቃውሞ) ትርጉም የለሽ ጩኸት እንደሆነ ይናገራሉና።

እዚህ ላይ የኮሌጅ ቀን ገጣሚያኑ፣ በግጥሞቻቸው ይብዛም ይነስም፣ ግለሰባዊም ይሁን ማህበረሰባዊ ብቻ፣ የሚያቀነቅኑት "ርዕዮተ ዓለም" እንዳላቸው ሊታወቅ ይገባል። ርዕዮተ ዓለም ደግሞ "በማህበረሰብ ታሪካዊ ሕይወት እጅግ ጠቃሚ መዋቅርና የማህበራዊነትም አንድ ገጽታ" እንደሆነ ባለሙያዎች ያስረዳሉ (ብርሃኑ፣ 1992፥ 46)። እናም በዚህ ጥናት ገጣሚያኑ ለምሳሌ፣ የራሳቸውንም ሆነ የማህበረሰባቸውን ርዕዮተ ዓለም በግጥሞቻቸው ለምን አስተጋቡ ወይም "አፈነዱ" የሚል ጥያቄ ማንሳት አልተፈለገም። ይልቁንም፣ በግጥም መሣሪያነት፣ ገጣሚያኑ እንደወጡበት ማህበረሰባዊ እውነት (ዳራቸው)፣ ርዕዮተ ዓለማቸውን እንዴት ባለ ስልት አቀነቀኗቸው? የወቅቱን የሀሳብ ታሪክ (history of Ideas) የሚገልጡ ምን ምን ጉዳዮችን አነሱ? የሚሉት ላይ ትኩረት ይደረጋል።

2.3.1 ግጥም እንደ ገጣሚያኑ ዳራ

ጥቂቶቹ የኮሌጅ ቀን ገጣሚያን፣ በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ታሪክ ግንባር ቀደም ሚና እንደነበራቸው ታውቋል። የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ደግሞ፣ የዓለም አቀፉም ሆነ የአህጉር አቀፉ እንቅስቃሴ አካል ነበር (Hanna, 1975)። እንደውም፣ ከተለያዩ የአፍሪካ ሃገራት ወደ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የመጡ ተማሪዎች፣ ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የፖለቲካ ንቃተ ህሊና መዳበር ትልቅ አስተዋፅኦ እንደነበራቸውም በምዕራፍ ሦስት ተወስቷል። እነዚህ አፍሪካውያን ተማሪዎች ደግሞ በየሃገራቸው በፈታኝ የፀረ ቅኝ ግዛት ትግል ያለፉ እንደሆኑ ይታወቃል። የፀረ ቅኝ ግዛት ትግሉ፣ የወለደው "Black Arts Movement" የሚባል፣ የቬትናምን ወረራ የሚቃወም፣ ስለ ጥቁሮች መብት የሚከራከር ታላቅ የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ በአሜሪካ የተለያዩ ከተሞች (በ1950ዎቹ) መደረጉ (Abrams, 1999: 23)፣ አፍሪካዊያን በኪነ ጥበብ መታገልን፣ የርዕዮተ ዓለም መግለጫ አድርጉ በስነ ጽሁፍ መገልገልን የበለጠ እንዳስተማረና እንዳነቃም መገመት ይቻላል፤ እነ Léopold Sédar Senghor የፈጠሩትን አፍሪካዊ የፖለቲካ ንቃተ ህሊናም ልብ ይሏልና።

የኮሌጅ ቀን ገጣሚያኑ ግን ከዓለም አቀፋም ሆነ ከአህጉር አቀፍ ስነጽሁፍን እንደ ትግል መሣሪያ ከመጠቀም ልማድ የበለጠ፣ የሃገራቸው የቅኔ ባህል፣ እንደ ትግል መሳሪያ በግጥም ለመጠቀም በቂ ዳራ እንደሆናቸው ይታሰባል፤ Gereenfield (1968) እና Levine (1965)ም ይህን ሁኔታ አስረድተዋል። እነዚህ የገጠመኝ እውቀቶች፣ በግጥም ርዕዮተ ዓለምን ማስተጋባት፣ እንዲችሉ መሰረት እንደሆኗቸው ይገመታል። በዋቢነት፣ ዮሐንስ አድማሱን፣ ዳኛቸው ወርቁን፣ ኃይሉ ገብረ ዮሐንስን፣ ጸገየ ወይን ገብረ መድህን፣ መጥቀስ ይቻላል። ከጸገየ ወይን በቀር፣ ሌሎቹ ከዩኒቨርሲቲ ከወጡም በኋላ በገጣሚነት ስለመቀጠላቸው መፃሕፍታቸው ይመሰክራሉ።

የኮሌጅ ቀን ገጣሚያኑ ግጥሞች ደግሞ "ከዘመናዊው" ("Modern") እንደሚመደቡ የSamuel (1994) ጥናት ተጠቅሶ ቀደም ብሎ ተጠቁሟል። እዚህ ላይ "It is impossible to understand modern poetry unless we understand it historically in motion" በማለት "ዘመናዊያኑን" ግጥሞች በቀረቡበት አውድ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመረዳት መሞከር ተመራጭ እንደሆነ የሚገልፀውን የCaudwell (1977: 84)ን አባባል መገንዘብ ይጠቅማል።

2.3.2 ግጥም እንደ ርዕዮተ ዓለም ማቀንቀኛ

አረጋው Mao Tse Tungን ጠቅሶ "ዞሮ ዞሮ የሁሉም ሥነ-ጽሁፍና የኪነጥበብ ሥራዎች የርዕዮተ ዓለም መልኮች እንደመሆናቸው፣ በሰዎች አእምሮ ውስጥ ያለ የአንድ ማህበረሰብ ሕይወት ጸብራቂ [ነፀብራቅ] ውጤቶች ናቸው" (1974፥ 7) ብሏል። ግጥምም ርዕዮተ ዓለም ለማቀንቀን ከሚያገለግሉ መሳሪያዎች አንዱ ነው ማለት ይቻላል። Wauthier (1979) የተባሉ ተመራማሪ The Literature and Thought of Modern Africa በሚለው መጽሐፋቸው የሚከተለውን አስፍረዋል።

> 'AFRICAN LITERATURE is politically committed', declared Léopold Sédar Senghor at the first International Congress of Negro Writers and Artists at the Sorbonne in 1956. Indeed, African poetry and novels do appear on the whole to be conditioned by the colonial situation; African poets and novelists have usually regarded their work, as Césaire did, as 'miraculous weapons' to defeat their 'omniscient and native conquerors' (PP፡ 144).

Wauthier፣ አፍሪካዊያን ሥነፅሁፎች ፖለቲካዊ (ርዕዮተ ዓለማዊ) መሆን እንዳለባቸው እስከ ማወጅ እንደተደረሰ፣ ስነ-ፅሁፍም የመታገያ መሳሪያ እንደሆነ ገልጸዋል፤ አንዳንዶቹ የኮሌጅ ቀን ገጣሚያንም በብዕራቸው፣ "የኢትዮጵያ ደራሲያን የህበረተሰቡን

ትክክለኛ ሁኔታና መሰረታዊ ፍላጐት የመግለጽ ግዴታ አለባቸው"[12] በማለት ሥነፅሁፍ የርዕዮተ ዓለማቸው ማቀንቀኛ መሆን እንደሚገባው በአፅንኦት እስከ መግለፅ ደርሰዋል።

እነዮሐንስ አድማሱ፣ "የኪነት ሥራ ከያኒው የሚኖርበት የእውነተኛው ዓለም ከውጭ ወደ ውስጥ፣ ከውስጥ ወደ ውጭ የሚያሳይ መስታወት መሆን አለበት።"[13] ያሉትን ስናይ፣ ከያኒው ወይም ኪነት እውነተኛውን ዓለም እንደ "መስታወት" ማሳየት ይችላል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ለጊዜው ትተን ቢያንስ የዛን ዘመን የስነ-ፅሁፍ ሥራዎች ምን ያህል ርዕዮተ ዓለማዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ መጠቆማቸውን ግን መገንዘብ ይገባል። በርግጥ፣ የስነፅሁፍና የሀሳብን ወይም የርዕዮተ ዓለምን (Literature and Ideas) ጥምረት ስናስብ እነ Wellek (1984)፣ "The Parallelism of the arts can be accepted only with large reservation. The parallelism between philosophy and poetry is even more open to doubt" (ገጽ፥ 120) ያሉትን ልብ ማለት ብልህነት ነው።

ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ (1966፥ ተ) "በረከተ መርገም"ን አስመልክቶ፣ "ይህች ግጥም ግን በተለይ ስለጠቅላላው የሰው ልጅ ዘር በይበልጥም ለጋራ ችግራቸው የምትናገር በመሆኗና በአሁኑም ጊዜ የሚከናወነው የህላዌ ተጋድሎ ዐይነተኛ እንብርቱ ይኸው ስለሆነ" (አፅንኦቱ የእኔ ነው) በማለት ቀድሞ እንዳሳተማት መስክሯል። ግጥም ምን ያህል ርዕዮተ ዓለማዊ የትግል መሣሪያው እንደነበረችም በግልፅ መረዳት ይቻላል። ዮሐንስም ቀደም ሲል በተገለፀውና "የኢትዮጵያ ደራሲያን የህብረተሰቡን ትክክለኛ ሁኔታና መሰረታዊ ፍላጐት የመግለጽ ግዴታ አለባቸው" በሚለው ፅሁፍ፣ ደራሲ (ገጣሚው) በህብረተሰቡ መካከል በተፈጠረው የምጣኔ ሀብት ልዩነት፣ የተከሰተውን "የኅብረተሰቡ የፖለቲካ አቋም" እየመረመረ በሥነ-ፅሁፍ የመግለፅ ሙያዊ ግዴታ እንዳለበት አትቷል።

የገጣሚያኑን ርዕዮተ ዓለማዊ መግለጫ ሳንዘነጋ፣ Bahiru (2005፡ 211) በመጽሐፋቸው፣ በ1957 ዓ.ም. ተማሪዎች "መሬት ላራሹ" የሚለውን መፈክር ሲያነሱ "Marxist-Leninist ideology became the preferred recipe for social and political change" ማለታቸውን ስንመለከት፣ "ማርክሲዝም ሌኒኒዝም" የሥነ ጽሁፋዊ ሥራዎቻቸው ሁሉ ርዕዮተ ዓለማዊ ማዕቀፍ ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ። በርግጥ፣ Gebru Tareke በቅርቡ ባሳተሙት መጽሐፋቸው Hobsbawmን ጠቅሰው "... Third world intellectuals were driven into revolution by Leninism without really being Marxist" (2009፡ 28) በማለት ትውልዱ የጠራ ርዕዮተ ዓላማዊ መሠረት ያልነበረው "ጥራዝ ነጣቂ"

---

[12] ዮሐንስ አድማሱ፣ በአንድ መድረክ ላይ ተጋብዘው፣ "ጥበብ ለጥበብነቱ" የሚሉ የኪነ ጥበብ ሰዎችን ለመሞገት ያቀረቡት ጽሑፍ ርዕስ ቢሆንም ሃሳቡ ግን ስሜታዊነት ያየለበት ይመስላል። አንድ ደራሲ የህብረተሰቡን ሁኔታ እንዲገልጽ እንዴት ይገደዳል? ግዴታውን አውቆ ቢጽፍስ፣ "የህብረተሰቡን ትክክለኛ ሁኔታና መሰረታዊ ፍላጐት" መግለጹን መለኪያው ምንድነው? ተብሎ ቢጠየቅ ተጨባጭ መልስ ማግኘት የሚከብድ ይመስለኛል። ዮሐንስ የግዴታ ጉዳይ ሲያነሱ፣ በ1954 ዓ.ም. የተሟገቱለት የሳንሱር ችግር፣ ፊቱን አዙሮ ይምጣ ማለታቸው እንደሆነ ዘንግተውት ይሆን? እኔ ግን አይመስለኝም።

[13] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 12።

እንደነበር አስረድተዋል፤ ዮናስ አድማሱም፣ ጦቢያ (7ኛ ዓመት፣ ቁ.3፤ ጥቅምት፣ 1992፥ ገጽ 16) መጽሔት ላይ፣

> የኔ የምለው ትውልድ በትንሹም ቢሆን ጥራዝ ነጣቂ የመሆን አዝማሚያ ነበረው፡፡ የንድፈ ሐሳቡም ይሁን የሚያቅዳቸው እቅዶች መሰረት በብዙው ድምጹን ያሰማለትና ደሙን ያፈሰሰለት ህዝብ እውነታ ከመሆን ይልቅ በሌላ ጊዜና ሁኔታ የተካበቱ ሐሳቦችን አምጥቶ ባለውና ሙሉ በሙሉ አወቅን ልንለው በማንችለው ሁኔታ ላይ ለመጫን የሞከረው ረቂቅ እውቀት ነበር…

በማለት የሳቸውን ትውልድ ዛሬም ወደ ውስጥ መመልከት እንዲችል፣ "በዚህ ባለንበት አውድ የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ስህተትን መገንዘብ ነው" የሚል የማንቂያ ደወል ደውለውለታል፡፡

ይህ ጥናት ግን የገጣሚያኑን ርዕዮተዓለም ልክ ነበር ወይም ተሳስቷል ማለት ሥራው አይደለም፤ ይልቁንም ገጣሚያኑ ግጥም እንደ ርዕዮተዓለም ማቀንቀኛ የመጠቀማቸውን ስልት ይመረምራል፤ ያነሷቸው ርዕዮተ ዓለማዊ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ ያስተነትናል፡፡ የገጣሚያኑ ሥራዎች ርዕዮተ ዓለማዊ ማዕቀፍ "ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ነው" ተብሎ ስለሚታሰብ፣ ጥናቱ ግጥሞቹን ሲተነትን Abrams (1994: 147) ያነሳቸውን የ"Marxist criticism" ንድፈ ሀሳባዊ መሠረቶች ማንፀሪያው ያደርጋል፡፡

ምዕራፍ ሦስት

"የኮሌጅ ቀን" በዓል ታሪካዊ ዳራ እና የገጣሚያኑ ሚና

በዚህ ክፍል ከ1950-1960 ዓ.ም. ያለው "የኮሌጅ ቀን" ክብረ በዓልና በዩኒቨርሲቲው ላይ የታዩ አንኳር ሁነቶች፣ ለኮሌጅ ቀን ገጣሚያኑ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ምልከታ ላይ ከሚያሳድሩት ተፅዕኖ አንፃር እየተመዘኑ በየተፈፀሙበት ዓመተ ምህረት በ11 ንዑሳን ክፍሎች ተደራጅተው ቀርበዋል። የጥናቱ ማሄጃ የሆነው የኮሌጅ ቀን ግጥሞች መጽሐፍ አዘጋጆች "… የዩኒቨርሲቲው ታሪክ ሲቃኝና ሲተነተን ተሸላሚ ገጣምያንን መዘከር፣ ግጥሞቻቸውም ተገቢ ቦታቸውን እንዲያገኙ ማድረግ የሚታለፍ ጉዳይ አይደለም …" (1993፣ ገጽ÷1) ቢሉም፣ የተገኙ ግጥሞች እንኳ ታሪካዊ ዳራቸው በትክክል እንዳልሰፈረ ግጥሞቹም በኮሌጅ ቀን በዓል ላይ አሸናፊ እንደነበሩ ማረጋገጥ እንዳልተቻለ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ተገልጿል። በርግጥ በጥድፊያ ጊዜ፣ ያውም በተደራቢ ሥራነት መረጃዎቹን ለማግኘት መሞከር ፈታኝ እንደሆነ ይታወቃል። ስለዚህ፣ በሠሩት ሥራ ከማመስገን በቀር ወቀሣ ሊቀርብባቸው ከቶውንም አይገባም።

መጽሐፉ፣ ገጣሚያኑንና ሥራዎቻቸውን አሁን ባሉበት ደረጃም ማሳወቁ መግለጡን ትልቅ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባ ይመስለኛል። ባይሆን፣ ግጥሞቹ የገጣሚያኑ ስለመሆናቸው መረጃ የለም እየተባለ፣ የኮሌጅ ቀን ገጣሚያን ግጥሞች እንደሆኑ አድርጐ (በመጽሐፉ ላይ) ጥናት ማድረግ ግን ጥያቄ ስለሚያስነሳ (መነሳትም አለበት) የኮሌጅ ቀን በዓልንና የገጣሚያኑን ዳራ ማጥናት አይቀሬ ጉዳይ ሆኗል። ጥናቱ፣ የተለያዩ ቀዳማይ መረጃዎችን መሠረት አድርጐ አሸናፊ ገጣሚያኑንና በተወሰነ መልኩም እስከ ሥራዎቻቸው ድረስ አፈላልጐ በማግኘት በየተወዳደሩበት ዓመተ ምህረት ሥር ዘርዝሯል።

2.4 1950 — "የኮሌጅ ቀን" አሠያየምና የቅድመ ግጥም ውድድሮች ቅኝት

የአፄ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በተከፈተ በሦስተኛው ዓመት፣ በ1946 ዓ.ም. ጀምሮ የኮሌጁ ተማሪዎች በየዓመቱ የሚካሄድ የስፖርታዊ ጨዋታ ጀመሩ[14]፤ የሚሰባሰቡበትን ሁኔታም ፈጠሩ።

[14] የኮሌጅ ተማሪዎቹ በ1946 ዓ.ም የጀመሩት ዓመታዊ በዓል "የኮሌጅ የስፖርት ቀን" በሚል ይጠሩት ነበር (አዲስ ዘመን የካቲት 30 ቀን 1951)። በኋላም፣ ከ1950 ጀምሮ ሌሎች ባህላዊ ዝግጅቶችም ተጨምረው "የኮሌጅ ቀን" መባል እንደተጀመረ ይታወቃል (አስፋው፣ 1998)።

በርግጥ በ1940ዎቹ መጀመሪያ ውጭ ሃገር የሚማሩ የኢትዮጵያ ተማሪዎች፣ የሚሰባሰቡበት ማህበር እንደመሰረቱ፣ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተማሪዎች ባይመራም፣ ተማሪዎችን በማሰባሰብ በማሣሳተፍ የአርበኝነት ተግባር የተወጣው "የጥቁር አንበሶች ንቅናቄ" ተቋምም በ1920ዎቹ አካባቢ፣ ቀድሞ ተመሥርቶ ነበር። ስመ ጥሩ ፀሀፊ ተውኔትና ባለቅኔ ዮፍታሔ ንጉሴም ትግሉ ያፈራቸው ከያኒ እንደሆኑ ይነገራል (ክፍሉ፣-፥13)። በ1950 ዓ.ም. የተለያዩ ዝግጅቶች ተጨምረው መቅረብ ሲጀምሩ፣ (በፈረስና በበቅሎ የተተወነ ተውኔትም ቀርቦ ስለነበር) ሁሉንም እንዲወክል ታስቦ "የኮሌጅ ቀን"[15] ተብሎ እንዲከበር ተደረገ። ዓመታዊ በዓሉን ከተጀመረበት ከ1946 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1954 ዓ.ም. ድረስ አፄ ኃይለ ሥላሴ ባለሟሎቻቸውን እያስከተሉ ዕለቱን ከተማሪዎቻቸው ጋር ያከብሩት ነበር። በዚህ ክብረ በዓል ላይ (እስከ 1950 ዓ.ም.) የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች ብቻ ይደረጉ ነበር።

3.2 1951 - "የኮሌጅ ቀን" ግጥሞች ውድድር አጀማመር እና የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት

ይህ ዓመት ተማሪዎቹ ከአዳዲስ የታሪክ አጋጣሚዎች ጋር የተዋወቁበት ጊዜ ነበር። በ1950 ዓ.ም. ጋና ዋና ከተማ አክራ ላይ በተደረገው የአፍሪካ መሪዎች ጉባኤ አፄ ኃይለ ሥላሴ ለ200 እንግሊዝኛ ተናጋሪ አፍሪካዊያን የትምህርት እድል በሰጡት መሰረት፣ የመጀመሪያዎቹ ተማሪዎች አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የደረሱት በዚሁ በ1951 ዓ.ም. ነበር (Greenfield, 1965: 366)። አስፋው ዳምጤ (1998፥40) በዚሁ ዓመት "... ሞደርን ቲንኪንግ ወይም የዘመኑ አስተሳሰብ የሚል ትምህርት "ሜኬሊዴስ" በሚባል ግሪካዊ መስጠት እንደተጀመረ፣ የተማሪ ተወካዮች በሁለት ዓለም አቀፍ የተማሪዎች ስብሰባ ላይ እንደተሳተፉ፣ አፍሪካውያኑ የስኮላርሺፕ ተማሪዎች ኢትዮጵያውያን "ረጅም ታሪክ አለን ብለው ስለሚኩራሩ ይንቁናል" እያሉ ጥላቻ እንዳደረባቸውና በኋላም ተደራጅተው "የአፍሪካ ተማሪዎች ክበብ" እስከ መመስረት እንደደረሱ ያስረዳሉ።

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ቀን በዓል፡- የ1951 ዓ.ም. የኮሌጅ ቀን በዓል ንጉሡ ነገስቱ በተገኙበት የካቲት 28 ቀን ተከብሯል። ንጉሡ፣

[15] አስፋው ዳምጤ፣ ስያሜውን እሳቸው እንዳወጡት ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓ.ም ለአጥኚው ነግረውታል፤ ግርማ (1976)ም በጥናቱ ጠቁሟል።

በዓሉን አስመልክቶ የተማሪዎች መማክርት ፕሬዝዳንት የሆነው ሀጕስ ገብረ የሱስ[16] ከዚህ በታች ተቀናንሶ የቀረበውን ንግግር አድርጓል።

ግርማዊ ጃንሆይ፤

... "የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ቀን" ዓመት በዓላችን ግርማዊነትዎ በመካከላችን ስለተገኙ ... ምስጋናችንን እንድናቀርብ ግርማዊነትዎ ይፍቀዱልኝ። ... ግርማዊነትዎ [የሚያደርጉልን] ያባትነት ጥንቃቄና ርኅራኄ ምንጊዜም ከኛ ከተማሪዎችም ልብ አይጠፋም። በዘንድሮው ... ፳ቱ ሴቶች ተማሪዎች ስለሆኑ፤ የሴቶች ተማሪዎች ቁጥር ካለፉት ዓመታት የበዛ ሆኖ ይገኛል። ... የተማሪዎች መማክርት በግርማዊነትዎ መልካም ፈቃድ በአፍሪቃና በአለም ተማሪዎች ጉባኤ ተካፋይ በመሆን ተገቢ ቦታቸውን ይዘው ይገኛሉ። ...

ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገስት፤

ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘላለም ትኑር፤[17]

የግጥም ውድድር፦ "በኮሌጅ ቀን" በዓሉ ላይ በውድድር የአሸነፉት ግጥሞች ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረቡት በዚህ ዓመት በመሆኑ የዚያን ዓመት በዓል ታሪካዊ ነው ማለት ይቻላል። የግጥም ውድድሩን አጀማመር አስመልክቶ፣ አስፋው ዳምጤ የህይወት ልምዳቸውን በሚዘክረው መጽሐፋቸው የሚከተለውን አስፍረዋል።

... ለ1951 ታስቦ የነበረው አድዋን የሚዘክር ቲያትር ፐሮግራሙ ላይ ለማቅረብ ነበር። ተቃውሞ እንዳለበት ከቤተ መንግሥት ተደውሎ በጸሐፊ ትዕዛዛ ተፈራ ወርቅ በስልክ መነገሩን፣ መጨረሻ ሰዓት ላይ በተማሪዎቹ ዲን ለተማሪዎች ም/ቤት ጠቅላይ ጸሐፊ ለእኔ ለአስፋው ዳምጤ (በዚያን ሰዓት ፕሬዝዳንቱ ሐጎስ ገብረየሱስ ስላልነበረ፣ እኔ ተ/ፕሬዝዳንት ነበርኩና) ተነገረኝ። እኔ ያኔ የታየኝ ብቸኛ አማራጭ ቲያትሩን በግጥም ንባብ መተካት ነበር። ከሁለቱ የዘርፉ ፕሬዝዳንቶች፣ ማለትም፣ አስፋው ደስታ (ኋላ ዶ/ር) - የስፖርት፣ መክብብ ገበየሁ (ኋላ አምባሳደር) - የባህል እና ፋንታዬ ቢፍቱ (ገንዘብ ያዥ) ጋር ተመካክሬ ሌላ ቶሎ የሚደርስ አማራጭ ስላልተገኘ፣ በግጥም ንባቡ ከተወሰነ ክርክር በኋላ ጸና። ... የወርቅ ሰዓት ሽልማቱን ሲሰጡት፣ "ጃንሆይ ለምን በእንደዚህ መፍቻ የሌለው ነገር ራስህን ታስጨንቃለህ አሉኝ" ብሎ ተገኘ የተሻወርቅ ማታ በምግብ ቤት አዳራሽ በተደረገው ግብዣ ላይ ነገረኝ። የግጥም ንባቡ የኮሌጅ ቀኑ ዓመታዊ ባህል ሆነና፣ እያደር የፖለቲካ ድምፀቱም እያየለ ላመታት በመዝለቅ ዛሬ ታሪክ ሆኗል። (1998፥17-18)

በእለቱ ስለተደረገው የግጥም ውድድርም ቀደም ብሎ የተጠቀሰው ጋዜጣ "ወጣቶች የቅኔ ውድድር ለማድረግ ከግርማዊነታቸው ዙፋን ፊት ቀረቡ" በማለት ገልፆታል።

---

[16] ዛሬ የፕሮፌሰር ማዕረግ ያላቸው የፖለቲካ ምሁር ሲሆኑ፣ በህምሌ 1960 መኢሶንን ከመሠረቱት 25 ሰዎች ውስጥ አንዱ መሆናቸውን አንዳርጋቸው (1992፥ 13) ጠቁመዋል።

[17] ተማሪዎቹ ለንጉሡ ነገሥቱ የነበራቸውን ፍቅርና አክብሮት (የወቅቱን ሁኔታ) ለመመልከት እንዲቻል ሲባል ብቻ ተቆራርጦ ቀረበ እንጂ፣ በአዲስ ዘመን (መጋቢት፣ 1951) የወጣው ንግግር በጣም ረጅምና ብዙ ጉዳዮችን የዳሰሰ ነበር።

መጀመሪያ ያቀረበው “አያሌው አሳየ” የተባለው ወጣት ሲሆን የግጥሙ ርዕስ “ጥበብ” የሚል ነበር። “የዚህም ቅኔ ሀሳብና ዓላማ እርስ በርስ ባለመተፋፈርና ባለመናናቅ ማናቸውንም ተግባር በሚገባ ለመፈፀም እንደሚቻል” የሚያቀነቅን እንደነበር ተጠቁሟል።

ሁለተኛው ተወዳዳሪ “አቶ ግርማ ሀጐስ የተባለው ወጣት ... አንዳንድ ሰነፎች ዘርና ቆዳ እንዲሁም ሥራን በማማረጥ የሚያደርጉትን ነቀፌታ አብራርቶ” የሚያስረዳ “የሥልጣኔ እንቅፋቶች” በሚል ርዕስ ግጥም አቀረበ።

በሦስተኛነት ለውድድር የቀረበው “አቶ ተገኝ የተሻወርቅ የተባለው የቅኔ ደራሲ” ሲሆን የግጥሙ ርዕስም “የኑሮ ችግር” የሚል እንደነበር ዘገባው ይጠቁማል። በሌላ በኩል፣ በኮሌጅ ቀን ግጥሞች መጽሐፍ ውስጥ የተገኘ የተሻወርቅ ግጥም “ሰው እንቆቅልሽ ነው” በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን በግርጌ ማስታወሻውም (ገጽ 1) ግጥሙ ተፈልጐ እንዳልተገኘና በኋላ ላይ አቶ አስፋው ዳምጤ ከገጣሚው ባለቤት ከወ/ሮ ሶፍያ ይልማ ተቀብለው እንዳመጡት ተገልጿል።

ከቀረበው ማስታወሻ በግልፅ ለመረዳት እንደሚቻለው በመጽሐፉ ላይ የታተመው ግጥምም ሆነ ርዕሱ፣ በእርግጠኝነት የቀረቡ አይደሉም። ግጥሙ፣ በጋዜጣው ላይ ከቀረበው አጭር ትንታኔ ጋር እያነፃፀርን ስንመረምረው ተገኝ የተወዳደረበት ግጥም ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል።

በሌላ በኩል “ሰው እንቆቅልሽ ነው” የሚለው ርዕስም የቀረበውን ግጥም በደንብ ይወክላል ማለት ይቻላል። ፈቃደ አዘዘ ካጣቀሱት የተማሪዎች ጋዜጣ ላይ የሰፈረው “Man is a Riddle” የሚል የእንግሊዘኛ ትርጉም ስለሆነ፣ ከአማርኛ ትርጉሙ (“ሰው እንቆቅልሽ ነው”) ጋር ይሰምራል። ጥያቄው ግን በውድድሩ ዕለት ተገኝ ያቀረበው ግጥም ርዕስ “ሰው እንቆቅልሽ ነው” የሚለው ነው ወይ? የሚል ነው። እዚህ ላይ የ“UCAL NL” ጋዜጠኞች በበዓሉ ላይ የተነበበውን (“የኑሮ ችግር” የሚለውን) ርዕስ ወይም አጠቃላይ የግጥሙን መንፈስ ለመወከል ሲሉ “Man is a Riddle” ብለውት ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ አለኝ። ከአጠቃላይ አውዱ አንፃር ግን የተገኝ ግጥም ርዕስ “የኑሮ ችግር” የሚለው ነው ቢባል አጉል ድፍረት አይሆንም። ለማንኛውም ግን ወደፊት ተጨማሪ ምርምር ሊደረግበት እንደሚገባ መጠቆም ይቻላል።

ወደ ውድድሩ ፍፃሜ ስንሄድ፣ የካቲት 30 ቀን 1951 ዓ.ም. የወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ "... በዚህ የቅኔ ውድድር አሸናፊ አቶ ተገኝ የተሻወርቅ[18] ሆኗል" የሚል ዘገባ አቅርቧል። በመጨረሻም፣ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱም ለተወዳዳሪዎች ሽልማት ሲሰጡ የተናገሩትን ንግግር ግን የኋላ ኋላ የኮሌጅ ቀን ገጣሚያኑ የህዝብ ስሜት የሚገዙ፣ ወጣቱን እያቀሰቀሱ ታምር የሚፈጥሩ ... መሆናቸውን እንደ ደረቅ ትንቢት የጠቆመ ሰለሞናዊ ጠቢብ ንግግር ነበር፤ "መሬት ታርሶ ባይለሰልስ፤ ጥሩ እህል ሊያበቅል አይችልም። የሕዝቡን መንፈስ በማነቃቃት የወጣቱን ልብ ለመቀስቀስ የተናገራችሁት ዋጋ ያለው ነው። ለወደፊቱም እንዲሁ እንድትበረቱ" ብለዋል።

3.3 1952 - የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር

ይህ ዓመት ተማሪዎች የራሳቸው ጋዜጣ እንዲኖራቸው ብዙ ከጣሩ በኋላ "News and Views" የተባለውን ጋዜጣ የጀመሩበት ጊዜ እንደሆነ ይታወቃል። በርግጥ ጋዜጣው ላይ የሚወጡት ጽሑፎች በፋኩልቲ አማካሪዎች መጽደቅ እንደልባቸው (ሳንሱር እንዲደረጉ) ህግ ስለወጣ፣ "ጋዜጣውን ከባለሥልጣናቱ መዳፍ ማውጣት የተማሪዎች ተቀዳሚ የትግል ዓላማ" እስከ መሆን መድረሱን (ክፍሉ፣ ዓመተ ምህረት አልተጠቀሰም ፥57፤ ባህሩ፣ 2000፥233) መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በዚህ ዓመት ተማሪዎች ማጉረምረም ቢጀምሩም፣ ቅሬታቸው ከኑሯቸው ጋር የተያያዘ ስለነበር፣ ባብዛኛው ያነጣጠረው በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አስተዳደር ላይ ነበር፤ አስተዳደሩም፣ ሁለት የተማሪ ተመራጮች ከኃላፊነታቸው እንዲወርዱ አደረገ። ተማሪዎቹ፣ በአስተዳደሩ ላይ ያላቸውን ቅሬታ "በጋዜጣቸው" ላይ ማስፈር ባይችሉም፣ በማህበራዊ ኑሮ እርስ በርስ የሚፈጥሩትን አለመግባባት በፊት ለፊት እየተቹ መፃፍ ጀመሩ። የንግግር ውድድርም (Oratorical contest) ያደርጉ ነበር።

የኮሌጅ ቀን በዓል፦ መጋቢት 3 ቀን 1952 ዓ.ም. ተከብሯል። በዓሉ፣ "... እጅግ ከፍ ባለ ሥነ-ሥርዓት ይከበር ስለነበር፤ በዚህ ዓመት ከተደረገው ታላቅ ድርጅት በቀር፤ ልዑላን መሳፍንት፤ ክቡራን ሚንስትሮችና መኳንንቶች፤ ኰር ዲፕሎማቲኮች በሥነ በዓሉ ላይ ተገኝተው" እንደነበር፣ አፄ ኃይለ ሥላሴ 10፡25 ሲል ተከታዮቻቸውን ይዘው ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሲደርሱ፣ "የኮሌጁ ፕሬዝዳንት ዶክተር ማትና በዚያ የነበሩት ሁሉ እጅ

[18] አቶ ተገኝ የተሻ ወርቅ የ"ሄራልድ" ጋዜጣ አዘጋጅ የነበሩ፣ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓት እስከ ሚኒስትር ድኤታ ማዕረግ የበቁ በኋላም፣ ደርግ ከረሸናቸው 60ዎቹ ባለስልጣናት አንዱ እንደነበሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ነስተው" እንደተቀበሏቸው፣ "የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪዎች ማህበር ፕሬዝዳንት" የሆነው ፋንታዬ ቢፍቱም "ከግርማዊነታቸው ዙፋን ፊት" ንግግር እንዳደረገ አዲስ ዘመን[19] ጋዜጣ በወቅቱ ዘግቧል።

የግጥም ውድድር፡- የዚህ ዓመቱ የግጥም ውድድር ከ1951ዱ የተለየ አካሄድ ነው የነበረው። በ1951 ዓ.ም. አሸናፊዎቹ የተለዩት በበዓሉ ላይ ከቀረቡ በኋላ ነበር። በ1952 ዓ.ም. ግን የኮሌጅ ቀን በዓል ከመከበሩ በፊት ሶስት አሸናፊ ተወዳዳሪዎች ቀድመው ተለይተው ነበር። የካቲት 11 (February 20th) ቀን 1952 ዓ.ም. በዩኒቨርሲቲው ኮሌጅ የምግብ አዳራሽ 12 ተማሪዎችን ያሳተፈ የግጥም ውድድር ተካሂዶ ነበር። በዚህ ውድድር አሸናፊዎችን ለመለየት አለማየሁ ሞገስና ሀብተማርያም ማርቆስ ዳኞች ነበሩ። የኮሌጅ ቀን በዓል ላይ ግጥሞቻቸውን የሚያቀርቡ አሸናፊ ገጣሚያንም 1ኛ ታምሩ ፈይሣ፣ 2ኛ መላኩ ተገኝ እና 3ኛ ዮሐንስ አድማሱ መሆናቸው ታወቀ።[20]

ቀደም ሲል በቀረበው መረጃ መሰረት የተማሪዎች ጋዜጣ ስለ ግጥሞቹ ርዕስ አልጠቀመንም። በአዲስ ዘመን ጋዜጣ (መጋቢት 5፣ 1952 ዓ.ም.) ላይ ግን፣ "... ባህላዊ ቅርስ በሚል አርእስት የግጥም ክርክር አድርገው፤ አንደኛነቱን ታምሩ ፈይሳ[21] የተባለው ወጣት አገኘ" በማለት የተወዳደሩበት ርዕስ "ባህላዊ ቅርስ" የሚል እንደሆነ ተገልጿል።

በዚያ ዓመት፣ ከኮሌጅ ቀን ግጥሞች ውድድር ጋር እየተደበላለቀ የዛን ጊዜ ተማሪዎችን ጭምር የሚያደናግር የግጥም ውድድር ተካሂዶ እንደነበር እ.ኤ.አ December 11, 1959 የታተመው "University College of Addis Ababa"[22] የተባለው የተማሪዎች ጋዜጣ ዘግቧል። የውድድሩ ዓላማ "ሎሬት" ገጣሚን ለመለየት ታስቦ ሲሆን፣ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ የምግብ አዳራሽ 7 ገጣሚ ተማሪዎች ተካፍለዋል። ውጤቱንም፣ "The first prize went to Mr. Dangachew Worku who was named poet laureate of the first term. The second and third prizes went to Mr. Tamru Feissa and Mr. Ayalew Assaye respectively" በማለት ጋዜጣው ገልጿል።

በሌላ በኩል የኮሌጅ ቀን ግጥሞች የተባለው መጽሐፍ፣ የ1952ቱን የውድድር ግጥሞች "ለናሙና እንኳን አላገኘንም" በማለት የመረጃውን ክፍተት በአፅንኦት ገልጿል።

---

19 አዲስ ዘመን ጋዜጣ (መጋቢት 5 ቀን፣ 1952)።
20 News and Views, Vol. 3, N 18, 1960:2.
21 ታምሩ ፈይሳ፣ ለ35 ዓመት በተለያዩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በኃላፊነት ጭምር ሲያገለግሉ እንደነበርና በኋላም ጥቅምት 2 ቀን 2001 ዓ.ም በ68 ዓመታቸው እንዳረፉ ባለቤታቸው ወይዘሮ ሰናይት ምህረቴ፣ 15-2-2002 ዓ.ም ነግረውኛል።
22 UCAA, Vol. 3 N. 9

በዚህ ጥናትም ግጥሞቹ እንኳ ባይገኙ ገጣሚያኑና የግጥሞቻቸው ርዕስ ስለተጠቆመ ለቀጣይ ምርምር የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይታሰባል።

3.4 1953 - የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር

ይህ ዓመት፣ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪዎች በታህሳሱ 1953 የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ድጋፍ በመሥጠታቸውና የመፈንቅለ መንግስት ሙከራውም በተማሪዎቹ የለውጥ እንቅስቃሴ ታሪክ ትልቅ ሚና ያለው መሆኑ ይታወቃል። ተማሪዎቹ መፈንቅለ መንግሥቱን ደግፈው፣

"ታሪክ ያለህ ያገሬ ሰው ተነሥ ተነሣ
ሰውነትህን አትርሣ"

የሚለውን መፈክራቸውን እየዘመሩ "ለመጀመሪያ ጊዜ ጐዳና ላይ ወጥተው ድጋፋቸውን ሰጡ።" (አንዳርጋቸው፣ 1992 ፥5)። ተማሪዎቹ በመንግሥቱ ንዋይ ንግግር ተመሥጠው የፊውዳሉን ሥርዓት በርግጥም ለመገርሠሥ በቀናት ቅስቀሳ ቆርጠው መነሳታቸውን ተገልጿል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮም፣ "ተቃውሞዎች በኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ መልክ የተከሰቱት ለየትና ረቀቅ ያለ ሥልት ተከትለው ነበር" በማለትም ክፍሉ ታደሰ (ያ ትውልድ /ቅጽ 1/ ፥22) ያወሳሉ።

የኮሌጅ ቀን በዓል አከባበር፡- የዘንድሮው የኮሌጅ ቀን ግንቦት 12 ቀን 1953 ዓመተ ምህረት ሲከበር የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ 10ኛ የምስረታ ዓመትም አብሮ ታስቦ ውሏል። በበዓሉ ላይ አፄ ኃይለ ሥላሴ ሚኒስትሮቻቸውንና ሌሎች ባለሥልጣኖቻቸውን አስከትለው በበዓሉ ላይ ተገኝተዋል፣ በበዓሉ ላይ የተለያዩ የስፖርት ውድድሮች ቀረቡ። የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁን 10ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግም፣ የሚሰለጥኑባቸውን የሙያ ዘርፎች ውጤት ለመጀመሪያ ጊዜ በሰልፍ ትርኢት አሳይተዋል። "በዚህ ትርኢት ውስጥ ከታዩትም ለተመልካች ይበልጥ ያሳቀው የዝብርቅርቅ ሚኒስትሩና የ… ሚኒስትሩ የሥራ ሂደት ነው።" ሚኒስትሮች ባሉበት የሚኒስትሮችን ድክመት የሚያሳይ ትዕይንት ለማሳየት መነሳትና መድፈር የመፈንቅለ መንግስቱ ሙከራ የፈጠረባቸው ንቃት ውጤት ይመስላል። ለዚህ ሳይሆን ይቀራል፣ የኮሌጅ ቀን ከተከበረ በ3ኛ ሳምንቱ፣ የተማሪዎቹ ጋዜጣ "ኤዲቶሪያል" ክፍል "Major Current Problem Discussed by Students — its significance." የሚል "ርዕሰ አንቀጽ" ጽፎ፣ "What should be attitude of African leaders towards capitalism and communism? …" በማለት የክርክር መድረክ የከፈተው።

የግጥም ውድድር፦ የኮሌጅ ቀን በዓል ላይ የቀረቡት ግጥሞች ከ1952ቱ በጠነከረ ውድድር አልፈው የመጡ ነበሩ። ከበዓሉ 3 ሣምንት ቀድሞ ሚያዚያ 15 ቀን ምሽት ላይ በምግብ አዳራሹ ውስጥ፤ ከበደ ካሣ፣ ኢያሱ ሲራክ፣ መስፍን ቸኮለ፣ ዮሐንስ አድማሱ፣ አለም እሸቱ፣ የገዛለም መንግስቴ፣ ታምሩ ፈይሣ፣ አሰፋ ወልዴ፣ ይልቃል በየነ እና አቤ ደምሴ በግጥም ውድድሩ ተሳትፈዋል። እያንዳንዳቸው ግጥማቸውን የሚያቀርቡበት 8 ደቂቃ ተሰክቶ የተሰጣቸው ሲሆን፣ በተፈቀደው ጊዜ እንዲያጠናቅቁ ተደርጓል። ውጤቱ የሚወሰነው በተመልካቹ ሲሆን፣ ስዩም ስብሃት የዳኝነት ውሳኔ የሚሰጡትን አካላት እንዲመራ ሲቀመንበር ተደርጎ ነበር። ግጥሞቹ የተወሰነ የድምፀትና የጭብጥ ልዩነት የታየባቸው ሲሆን በአብዛኛው ያነሷቸው፣ “such serious themes as death, life, hereafter and injustice” ነበሩ። ውጤቱም፣ 1ኛ ታምሩ ፈይሣ፣ 2ኛ ዮሐንስ አድማሱ፣ 3ኛ ከበደ ካሣ ሆነዋል።[23]

የተማሪዎቹ ጋዜጣ የአሸናፊ ግጥሞች ርዕሶችን አልገለፀም። ቀደም ሲል በተገለፀው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ግን የታምሩ ፈይሳ፣ “ደሃው ይናገራል”፣ የዮሐንስ አድማሱ፣ “የገደል ስር አጥንት”፣ የከበደ ካሣ ደግሞ “ወይዘሮ ዓለሚቱ ቤቷን አሳየችኝ” መሆኑን ጠቁሟል። ለአሸናፊዎቹም፣ “ከግርማዊነታቸው እጅ የብር ዋንጫ፤ የሰዐት፣ የብዕር፤ የካሜራ ሽልማት” ከተሰጠ በኋላ፣ “የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ተዘምሮ ሥነ በዓሉ ተፈፀመ” (አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ግንቦት 15 ቀን 1953 ዓ.ም. የታተመ)።

3.5 1954 የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር

1953 ዓ.ም. “የመፈንቅለ መንግሥት ዓመት” እንደሆነ የተገለፀው፣ (በመፈንቅለ መንግሥቱ ሣቢያ) ተማሪዎቹ በስርዓቱ ላይ ያላቸውን ዓመለካከትና ግምት የለወጠ ወሣኝ ዓመት በመሆኑ ነው። የተባለው የተማሪዎች የአመለካከትና የአሠራር ለውጥ በቀጥታ በዚህ ዓመት ላይ መታየቱን ጥናቶች ያረጋግጣሉ (Greenfield, 1968: 18)። በአሜሪካኖቹ የሚሰጠው ትምህርትም ጭራሽ ኢትዮጵያዊነቱን እያጣ በአሜሪካውያን ታሪክና ባህል መታጨቁ በተማሪዎቹ የጠነከረ ቅሬታን የፈጠረበት፣ ከአሜሪካዊያን ጋር የሚቀራረቡ “እድር ባይ” ተማሪዎች ለአንድ ዓመት የመሥክ አገልግሎት አሜሪካ ደርሰው ሲመጡ በግንባር ቀደምቶቹ የተማሪ መሪዎች “ጆሲ. ጃክ” የሚል ቅፅል ስም የወጣላቸው ዓመት (ክፍሉ፣ ዓ.ም. አልተጠቀሰም፥ 60 እና 62)፣ በዝግ የቤተ መህፍት አጠቃቀም ዙሪያ የወጣውን አዲስ ህግ ተቃውመው ሰላማዊ ሰልፍ የወጡበትን በየቦታው “Closed Libraries

---

[23] News and Views, Vol. IVB NO. 30, 1961:1

Breed Closed Minds" የሚሉ አይነት ጥቅሶች እየፃፉ በይፋ ማመጽ የቀጠሉበት ዓመት ነበር (Balsvik, 2005, 105)።

የኮሌጅ ቀን በዓል፡- የ1954 ዓ.ም የኮሌጅ ቀን ሰኔ 2 ቀን ዕለተ ቅዳሜ ከ7 ሰዓት ጀምሮ እስከ 12 ሰዓት ድረስ ተከብሯል። "በዚሁ ቀን፤ በተማሪዎቹ የተዘጋጀውን ትርኢት እንዲመለከቱ ጥሪ የደረሳቸው የተማሪዎቹ ቤተሰቦችና በብዙ ሺ የሚቆጠር ህዝብ በኮሌጁ ቅጥር ግቢ ውስጥ ተሰብስበው እንደነበር ተገልጿል።"[24]

የግጥም ውድድር፡- በ1954 ዓ.ምህረትም ለኮሌጅ ቀን በዓል የሚነበቡ ግጥሞች በውድድር የተለዩት ቀድመው ነው። News and Views[25] የተባለው የተማሪዎች ጋዜጣ "UCAA HOLDS FOURTH ANNUAL POETRY CONTEST:" በሚል ርዕስ የሚከተለውን ዜና ዘግቧል።

> The annual Amharic poetry contest was held in the College Dining Hall 1 June in the presence of a large audience, many members of which believed this year's presentment as the best of its kind. Four best poets of the year — Ato Yohannes Admasu, 1st; Ato Yilma Kebede, 2nd; Ato Melaku Tegne, 3rd; and Ato Dagnatchew Worku, 4th; out of 14 participants were chosen to reald their masterpiece before the public on college day (አጽንኦቱ የኔ ነው።)

ከላይ በአፅንኦት እንደተመለከተው፣ የዚህ ዓመት አሸናፊ ግጥሞች ከእስከ ዛሬዎቹ ሁሉ የላቁ፣ ብዙ ሰውም እንዳዳመጣቸው እና ምናልባትም የተወዳዳሪ ግጥሞቹ ጥንካሬ አራተኛ የወጣውን ግጥም ጭምር ለመድረክ እንዲበቃ ያስገደዱ ገጣሚያንና ግጥሞች እንደሆኑ መገመት ቀላል ነው። 1ኛ የወጣው ግጥም "እስኪ ተጠየቁ"፣ 2ኛ የወጣው "ኑሮ"፣ 3ኛ የወጣው "ሜዳ የቀረኸው" የሚሉት ሲሆኑ አራተኛ የወጣው የዳኛቸው ወርቁ ግጥም ርዕስን አስመልክቶ፣ በፅሁፍ የተረጋገጠ መረጃ አላገኘሁም። ዳኛቸው፣ ከMolvaer (1997) ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ግን በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው የፃፏቸው ሁሉም "የተቃውሞ ግጥሞች" (Protest Poems) "እምቧ በሉ ሰዎች" በሚለው የግጥም መድበላቸው ውስጥ እንደተካተቱ ተናግረዋል። የመድበሉን ግጥሞች ስመለከት፣ በተለይ በቅርፁና "1954 ዓ.ም." በሚለው መግለጫው "እምቧ በሉ ሰዎች" የሚለው የመድበሉ መጠሪያ የሆነው ግጥም ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ። አራተኛ የወጣው የዳኛቸው ግጥም በ"ኮሌጅ ቀን" በዓሉ ላይ እንዳልተነበበ ቀደም ሲል ከጠቀስነው ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ፣

---

[24] አዲስ ዘመን (21ኛ ዓመት ቁጥር 165፤) ሰኔ 4 ቀን 1954 ዓ.ም የታተመ።
[25] Vol. V. No. 30 (7 June, 1962: 1)

መረዳት ይቻላል። የግጥም ውድድሩንም የዳኙት፣ አብርሃም ደመወዝ፣ ስርጋው ሃብለ ሥላሴ እና ዓለማየሁ ሞገስ ነበሩ። "ዳኛቸው በውድድሩ ምሽት ከተሳተፈ በኋላ አራተኛ በመሆኑ 'ተቆጥቶ' ለበዓሉ ዕለት ለህዝብ ሲበተኑ ሊሸጡ የነበሩትን ኮፒዎቹን ሰብስቦ 'እንዳቃጠላቸው' ተወርቷል" በማለት ዮናስ አድማሱ ነግረውኛል።

የዚያ ዓመት የግጥም ውድድር፣ አብዮተኛ ብዕሮችን ያስተናገደ፣ በዩኒቨርሲቲ የኮሌጅ ቀን ክብረ በዓል ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አፄ ኃይለ ሥላሴ እንዳይገኙ (ዮናስ አድማሱ፣ "አፄ ኃይለ ሥላሴ የነበሩ ይመስለኛል። ምክንያቱም ሰዓቶቹ ጀርባ ላይ የስማቸው ምሕፃር ተቀርጾባቸዋል። ሰዓቶቹም አብዛኞቹ Certina /ምናልባትም በየመሃሉ ለሌሎቹ OMEGA/ ይሰጡ ነበሩ" ብለውኛል) ምክንያት የሆነና በብዙ ታዳሚ አድናቆትን ያገኘ የታሪክ አጋጣሚ ነበር። አፄ ኃይለ ሥላሴ ለመቅረታቸው ምክንያቱ ግጥሞቹን በቅድመ ምርመራ (ሣንሱር) ለማሳየት የተማሪዎቹ መሪዎች ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ነው። የመንግስት ባለስልጣናት የደህንነት ሰው ልከው የሚቀርቡትን ግጥሞች ከመቅረባቸው በፊት ማየት እንደፈለጉ በድብቅ ከተማሪ መሪዎች ጋር ሊደራደሩ ቢሞክሩም፣ የተማሪዎቹ መሪዎቹ "ይሄ ተግባር የገጣሚያኑን ክብር የሚነካ ብቻ ሣይሆን የተማሪዎች ማህበርንም የሚያዋርድ ነው" በማለት እንደሞገቷቸው ተገልጿል። ለ1953 ዓ.ም.፣ በእነ "ደሀው ይናገራል" የተጀመረው ጉሸማ ዘንድሮ የበለጠ ተጠናክሮ እንደሚከወን የገባቸው የንጉሠ ነገሥቱ ባለሟሎች፣ ከህዝብ ፊት ከመዋረድ እንዲቀሩ እንዳማከሯቸውና በኋላም እንዳስቀሯቸው Greenfield (1968: 18) "A Note on a Modern Ethiopian Protest Poem" በሚለው ማስታወሻቸው ላይ አስፍረዋል።

በመጨረሻ ግን እነዚህ አብዮተኛ ገጣሚያኑም ሆኑ የተማሪ መሪዎቹ ከእረፍት ሲመለሱ አንድ ነገር ተወስኖ ቆያቸው። ለአንድ ዓመት ከትምህርት ገበታቸው ላይ እንዲታገዱ ተደረገ (Balsvik, 2005: 107)። ስለሌሎቹ መረጃ ባላገኝም፣ ዮሐንስ አድማሱ ግን ደሴ ከተማ በሚገኘው የወይዘሮ ስኂን ትምህርት ቤት እንዲያስተምር መደረጉ ይታወቃል።

3.6 1955 - የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር

በዚህ ዓመት የትምህርት መክፈቻ በዓል ላይ ዩኒቨርሲቲው፣ ተማሪዎችን የሚመለከቱ አዳዲስ አፋኝ ህጎች አውጥቶ የቀየበት፣ የ1954 የኮሌጅ ቀን ገጣሚያንና የተማሪ መሪዎችን ትምህርታቸውን እንዳይቀጥሉ የታገዱበት፣ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ነፃነት ብሔራዊ መንግስቱን የሚተቹ ፅሁፎች እንደማይጨምር የተወሰነበት ... ስለነበር ይሄ የጊዜ ምዕራፍ የአፈና ዓመት ቢባል አይበዛበትም፤ "እነዚህ አዳዲስ ህጎች በተማሪውና በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር እንዲሁም በመንግሥት መሀል ለብዙ ዓመታት ለተካሄደው ፍልሚያ መሠረታዊ ምክንያቶች" ሆነዋል (ክፍሉ፣ - ፥ 60)።

የኮሌጅ ቀን በዓል፡- የዚህ ዓመቱ የኮሌጅ ቀን በዓል ቅዳሜ፣ ግንቦት 17 ቀን 1955 ዓ.ም. የተከበረ ሲሆን፣ "... የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ክቡር ልጅ ካሣ ወልደ ማርያም፤ የኮሌጅ መምህራን፤ ወጣቶችና ተማሪዎች ተገኝተዋል።"[26] የቀደመው ዓመት አከባበር ያመጣው ጣጣ የፈጠረው ምክንያት ይመስላል፣ "ካለፉት ዓመታት የኮሌጅ በዓል ቀኖች ድርጅት የተለየና ቀዝቀዝ ያለ" እንደነበር ታውቋል። በርግጥ፣ በየዓመቱ በተማሪዎች ሲቀርቡ የነበሩ ዝግጅቶች ሁሉ በቀዘቀዘ መንፈስም ቢሆን በዚህም ዓመት ቀርበዋል።

የግጥም ውድድር፡- በዚህ ዓመትም የተደረገ ሲሆን፣ News and Views[27] የሚባለው የተማሪዎች ጋዜጣ፣ "The three best poets of the year, Abi Demissie, Negede Gobeze,[28] and Aregay Fenta, who came out first, second, and third, respectively took a watch each" የሚል መረጃ አስፍሯል። የኮሌጅ ቀን ግጥሞች የሚለው መጽሐፍ ከ1952 ውጪ ባሉት ዓመታት "ቢያንስ የየዘመኑን አንድ ወይም ሁለት ያህል [ግጥሞች] አግኝተን አሳትመናል።" ቢልም፣ የ1955ን ዓ.ም. የሚወክል አንድም ግጥም እንዳልታተመ አጥኚው አረጋግጧል። ጥናቱ ቢያንስ አሸናፊዎቹ ገጣሚያንን አፈላልጎ ቢያገኝም፣ ዮናስ አድማሱ ከነገሩኝ፣ "እጉል ቦታ አምሽቼ" ከሚለው ከነገደ ጉበዜ የግጥም ርዕስ በቀር፣ የሌሎቹን ግጥሞቻቸውንም ሆነ የግጥም ርዕሶቻቸውን ለማግኘት

---

[26] አዲስ ዘመን፣ (3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 725) ግንቦት 19 ቀን 1955 ዓ.ም. የታተመ።

[27] Vol. VII, No. 29, 1963: 4

[28] በ1936 ዓ.ም በደሴ ተወለዱ። በ1953 ዓ.ም. አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብተው በ1956 በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በኋላም፣ በ1967 በህግ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ያገኙ፣ መኢሶንና በውጭ ሃገር የተለያዩ የተማሪ ማህበራት የመሠረቱና የመሩ፣ "ከተማሪነት ዘመናቸው አንስቶ በፖለቲካዊ እንቅስቅሴዎች ንቁ ተሳታፊ የነበሩ፣ "በምርጫ 97" ኢህአዴግ "እረብሻና ብጥብጥ ፈጥረውብኛል" በሚል አጥብቆ የተቃወማቸውና የከሰሳቸው ዛሬም ተሟጋች ፖለቲከኛ ናቸው። "ታጠቅ" እና "ትግላችን" ላይ "ብርሃኔ ደመቀ" በሚል የብዕር ስም ይፅፉ እንደነበር በ1997 በወጣው፣ ስለህገመንግስት ከሚያትተው መጽሐፋቸው መረዳት ይቻላል።

የተደረገው ጥረት ስላልተሳካ ወደፊት ተጨማሪ ምርምር ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያመላክታል።

3.7 1956 - የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር

ይህ ዓመት አንድ ታላቅ ታሪካዊ ክስተት አስተናግዷል። የተማሪዎች እንቅስቃሴ በተለይ በ1950ዎቹ መጨረሻ ላይ ተቀጣጥሎ ጫፍ እንዲደርስ ትግሉን የመራው ከ1954 ዓ.ም. ጀምሮ ጥንስሱን ጥሎ በዚህ ዓመት የተመሰረተው "Crocodile" ("አዞ") የተባለው የቆራጥ ተማሪዎች ቡድን ነበር። ይህ ቡድን በተማሪዎች እንቅስቃሴ ታሪክ ታላቅ ድርሻ እንደነበረው መረጃዎች ያሳያሉ። እነ ኃይሉ ገብረ ዮሐንስን የመሰሉ የኮሌጅ ቀን ገጣሚያን በቀጥታ የተሳተፉበት ይህ ቡድን፣ የማርክሲዝምን ርዕዮተ ዓለም ቀድሞ ተቀብሎ ለተማሪዎች ለማስረፅ በመታገሉም ይታወቃል። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በተማሪዎች ላይ የተጣለውን ማዕቀብ እንዲነሳ የታገለ፣ ሀሳብ ስለመግለፅ ነፃነትም በርትቶ የተሟገተ እንደነበር ጥናቶች ይጠቁማሉ (ባህሩ፣ 2000፥ 233፤Balsvik, 2005: 118)።

የኮሌጅ ቀን በዓል፡- የዚህ ዓመት የኮሌጅ ቀን ሚያዚያ 17 ቀን 1956 (April 25, 1964) የተደረገ ሲሆን፣ አፄ ኃይለ ሥላሴ በበዓሉ ላይ ለመገኘት እንደማይችሉ ቀደም ብለው አሳውቀው ስለነበረ የተማሪ ማህበሩ "በእልህ" የተሻለ በዓል ለማድረግ መጣሩን News and Views,[29] ጋዜጣ ዘግቧል። ጐንደር፣ አለማያ፣ አዲስ አበባ ኮሌጆች ሁለት ሁለት የተማሪ ተወካዮችን እንዲያሳትፉ ተደርጓል።

በዚያ ዓመት በዓል ለመጀመሪያ ጊዜ ‹ሽልማት ቁሦችን የተማሪዎች ማህበር ከዶክተር Montogomery ጋር በመተባበር አሰናድቷል፤ እንደ በፊቱ አፄ ኃይለ ሥላሴ አላሟሉላቸውም። በበዓሉ ላይ የተለያዩ የስፖርት ውድድሮች፣ የየትምህርት ክፍሉ ተማሪዎች የሠልፍ ላይ ትርኢቶችና መዝሙሮች ቀርበው ነበር።

የግጥም ውድድር፡- የዘንድሮ የግጥም ውድድር በ"ክርክር ማህበረሰብ" (Debating Society) አማካይነት፣ እለተ አርብ ሚያዚያ 9 ቀን 1956 (April 17, 1964) የተካሄደ ሲሆን፣ ውድድሩን የመሩት አለማየሁ ሞገስ፣ አብርሃም ደመወዝ እና ጻኛቸው ወርቁ ነበሩ። News and Views ጋዜጣም፣

> The winners were second year students Abebe B.M. Worke, Yonas Admassu and Wondwassen Gebre Yesus. Their three poems will be read and copies will be on sale on college Day (Vol., X, No. 21, 1964: 7).

---

[29] Vol, X, No. 21, 1964: 7

በማለት ገልፆታል። የግጥሞቹ ርዕሦች 1ኛ "ሙት ወቃሽህ መጣሁ"፣ 2ኛ "ምሕፃረ ኑሮ"፣ 3ኛ "አንተ ያንቀላፋኸው" መሆናቸው ይታወቃል።

3.8 1957 - የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር

"መሬት ላራሹ የምትሹ፣
ተዋጉለት አትሸሹ።"

ይህ ዓመት ተማሪዎች ሥርነቀል የሆኑ ጥያቄዎችን ያስተጋቡበት፣ በተማሪዎች የትግል ታሪክ ውስጥ ከረር ያሉ አቋሞች የተንፀባረቁበት፣ ተማሪዎች ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ለልመና የተሰማሩበት፣ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲው ግቢ ድረስ ዘልቆ ተማሪዎችን የደበደበበትና ያስፈራራበት ዓመት ነበር። ለነዚህ ሁሉ ችግሮች ዋና ማጠንጠኛ ደግሞ፣ ተማሪዎች "መሬት ላራሹ" የሚል ሥርነቀል ጥያቄ ማንሳታቸው ነበር። ለዚህ ነው፣ ይህንን ዓመት፣ የ"መሬት ላራሹ" ዓመት ብሎ ጥናቱ የሰየመው።

የኮሌጅ ቀን በዓል፦ አስመልክቶ በዚህ ዓመት ስለመከበሩ የሚገልፅ ምንም አይነት ፍንጭ ማግኘት አልተቻለም። የግጥም ውድድሩ መካሄዱን በሚመለከትም እንደዚሁ መረጃ አልተገኘም።

እንደሚታወቀው፣ እስከዚያን ጊዜ የኮሌጅ ቀን በዓላት የተከበሩት ከየካቲት እስከ ሰኔ ባሉት ወራት ውስጥ ነው፤ በተለይም ከመጋቢት እስከ ግንቦት። በዚህ ዓመት ደግሞ፣ ከየካቲት እስከ ግንቦት ተማሪዎች የመሬት ላራሹ ጥያቄን አንስተው ሙግት የገጠሙበትና ዩኒቨርሲቲውም የተረጋጋ የመማር ማስተማር ተግባሩን መወጣት ያልቻለበት ወቅት እንደ ነበር ቀደም ሲል በአጭሩ የተወሰሩት መረጃዎች ይጠቁማሉ። ስለዚህ፣ በዚህ ዓመት የኮሌጅ ቀን በዓል አልተከበረ ይሆን? የሚል ጥርጣሬ አለ። እርግጠኛ ለመሆን ግን ተጨማሪ ጥናት ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል፣ <u>የኮሌጅ ቀን ግጥሞች</u> የሚለው መጽሐፍ "በ1957 ያሸነፉ" በሚል የጸገየወይን ገብረ መድህንንና የኢብሣ ጉተማን ግጥም ጠቅሷል። "ናስተማስለኪ" የሚለው፣ የጸገየወይን ግጥም ያሸነፈው ግን በ1959 ዓ.ም. ሲሆን፣ "ኢትዮጵያዊው ማን ነው?" የሚለው የኢብሣ ግጥም ያሸነፈው ደግሞ በ1958 ዓ.ም. እንደሆነ በዚህ ጥናት ተረጋግጧል (ዝርዝሩን በቀጣዮቹ ክፍሎች ይመልከቱ)።

3.9 1958 - የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር

በመጋቢት ወር 1958፣ በሸዋ የታጠረውን የድሆች ማጐሪያ በመቃወም ተማሪዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩን አነጋገሩ። ጠቅላይ ሚኒስትሩም አጣሪ ኮሚቴ እንደሚያቋቁሙ፣

ኮሚቴው ተማሪዎችን እንደሚጨምር ገለፁ። ተማሪዎች ግን ከሚኒስትሩ ዘንድ ወጥተው “ወደ ፓርላማ በሚያዘግሙበት ጊዜ፣ ፖሊስ ደርሶ ትርምስ ፈጠረ፣ ተማሪዎቹን ደበደበ፣ አቆሰለ” (Balsvik, 2005)። በርግጥ፣ ይህ ሰላማዊ ሰልፍ፣ ታስቦበት የተዘጋጀ፣ የሁሉንም ግቢ ተማሪዎች ፈቃደኝነት ያገኘ ነበር። “የሾላ የመልሶ ማቋቋሚያ ጣቢያ” በተማሪዎቹ አገላለፅ “የሾላ የድሆች ማጐሪያ” የተሰራበት ዓላማ፣ የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ የውጭ እንግዶች ሲመጡ ድሆች፣ አካለ ስንኩሎች፣ በረንዳ አዳሪዎች … በከተማዋ እንዳይታዩና ከተማዋን “እንዳያረክሱ” እንግዶቹ እስኪሄዱ ድረስ ተሰብስበው “እንዲታጐሩበት” ነው። በሽተኛውም ጤነኛውም፣ ወጣቱም አዛውንቱም፣ ህፃናቱ ሴቱም አንድ ላይ ተጋፈው በሚጠራቀሙበት በዚህ “ማጐሪያ ጣቢያ”፣ ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ መብት ጥሰት እየደረሰ እንዳለ ተማሪዎች፣ ከናዚ “የማጐሪያ ጣቢያ” ጋር እያመሳሰሉ በራሪ ወረቀቶች እየፃፉ በትነዋል። በዚህ በራሪ ወረቀት ላይ የሰፈረው መፈክር “ድህነት ወንጀል ነውን?” የሚል እንደነበር (Balsvik, 2005፡ 157) በጥናታቸው ገልፀዋል። በዚህ ጥናትም 1958 ዓ.ም. የ“ድህነት ወንጀል ነውን?” ዓመት መባል የተፈለገው ለዚህ ነው።

የኮሌጅ ቀን በዓል፡- ሚያዝያ 22 ቀን 1958 (April, 30th, 1966) እንደሚከበር በተማሪዎች ጋዜጣ ላይ (News and Views, Vol. 1 No. 8, 1966:4) ከተጠቆመው ቀን በቀር ሌላ መረጃ አልተገኘም።

የግጥም ውድድር፡- በሚያዚያ 22 ቀን “በተከበረው” የኮሌጅ ቀን በዓል ላይ የሚቀርቡ አሸናፊ ግጥሞችን ለመለየት ሚያዚያ 11 (April, 19) በራስ መኮንን አዳራሽ ውድድር ተካሂዷል። አዳራሹ ውድድሩ ከመጀመሩ በፊት ቀድሞ በተመልካች የተጨናነቀ እንደነበርና ውድድሩ 4 ሰዓት እንደፈጀ ቀደም ሲል በተጠቀሰው ጋዜጣ ላይ Ogbase lassie G. Medhin የተባለ ፀሐፊ ዘግቦታል።

በውድድሩ ላይ 1ኛ የወጣው፣ መሃመድ ኢድሪስ[30] (“ከምሽት እስከ ጐህ”)፣ 2ኛ አበበ ወርቄ[31] (“ምላሴን ተውልኝ”)፣ 3ኛ ደግሞ ኢብሣ ጉተማ[32] (“ኢትዮጵያዊ ማነው?”) መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል።

---

[30] ለረጅም ጊዜ በጋዜጠኝነት ያገለገሉና በአሁኑ ጊዜ በግል ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ፣ የአ.አ.ዩ. 50ኛ ዓመት በዓል ላይ “ከምሽት እስከ ጐህ”ን ያነበቡና በተማሪነታቸው ጊዜ በአዜው ሥርአት ላይ ማመፃቸው እንደፀፀታቸው የተናገሩ እንደነበሩ፣ ደረጀ ገብሬ (የ50ኛ ዓመት በዓል አሰናጂ ኮሚቴ) ነግረውኛል።
[31] የህግ ባለሙያና የኢሰመጉ መሥራች እንደነበሩ፣ ዛሬም በሀገራቸው ፖለቲካ ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ያላቸው ሰው እንደሆኑ አዲስ አድማስ (ቁ. 28፣ ሀምሌ 2 ቀን 1997 ዓ.ም.) ጋዜጣ ላይ አብርሃም ረታ የተባሉ አምደኛ ጽፈዋል።
[32] ከደርግ ውድቀት በኋላ በሽግግር ዘመን የትምህርት ሚኒስትር የነበሩ፣ በአሁኑ ጊዜ በሥደት ላይ ያሉ የኦነግ መሪ መሆናቸውን አብርሃም (ዝኒ ከማሁ) ገልፀዋል።

3.10 1959 - የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር

በዚህ ዓመት ጥር ወር ላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ማህበር (USUAA) ሲመሰረት፣ የካቲት ወር ላይ ኡዝዋን የሚቃወም "የመልሶ ማቋቋም" (Restoration Committee) ቡድን ተቋቋመ፡፡ በሁለቱ ስብስቦች መካከል ልዩነታቸው ከረረ፡፡ "የመልሶ ማቋቋም" ቡድን ዓላማ፣ ሁሉም ኮሌጆች በራሳቸው እንዲንቀሳቀሱ፣ የራሳቸው ማህበር ጋዜጣ እንዲኖራቸው ማድረግ ነበር፤ የኮሌጆቹን በአንድ ላይ ህብረት መፍጠር (ኡዝዋን) አልደገፉም፡፡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የርዕዮተ ዓለም ልዩነትም ተከስቶ ነበር፤ መልሦ ማቋቋሞች የግራ ዘመሙን ሶሻሊዝም እንደማይደግፉና እንደማይከተሉ አስታውቀዋል፡፡ በመጨረሻ ግን የሁለቱ ቡድኖች ፉክክር የተቋጨው በኡዝዋ አሸናፊነት ነበር (ክፍሉ፣ - ፥72-73)፡፡

የካቲት 1959 ላይ ሰላማዊ ሰልፍ ከመደረጉ በፊት ፍቃድ ማግኘትን የሚጠይቅ ህግ ወጣ፡፡ ይህን በመቃወም ኡዝዋ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ወሰነ፡፡ ከፖሊስ ጋር አለመግባባት በመፈጠሩም በግቢው ውስጥ ተማሪዎች ተደበደቡ፤ ብዙዎቹ ለቀናት ታሰሩ፡፡

የኮሌጅ ቀን በዓል፡- የያኔውን የኮሌጅ ቀን በዓል አስመልክቶ አንድ መረጃ ተገኝቷል፡፡ በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ቤተ መፃህፍት ቤተ መዛግብት ክፍል "IES 2404/01" በሚል መለያ ቁጥር "የግጥሞች (መወድስ) ቅኔና የመሳሰሉት መድበል" የሚል በአረንጓዴ ክላሰር ታስሮ የተቀመጠ፣ ከተማሪዎች እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ የተለያዩ መረጃዎችን የያዘ ሠነድ ውስጥ፣ "Account No. 2 IES 2426" የሚል በካኪ ፖስታ ለብቻ የተቀመጠ "ማስታወሻ" አለ፡ የዚያን ዓመት የኮሌጅ ቀን በዓል እስከ አሸናፊ ግጥሞቹ ድረስ፣ የወቅቱን አውድ በዝርዝር በሚገባ ስለገለፀ፤ በዚህ ጥናት እንዳለ ማካተቱ በብዙ መልኩ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ፣ አባሪ "ሀ"ን ይመልከቱ፡፡[33]

ከላይ በተገለፀው "ማስታወሻ" ላይ የገጣሚያኑ ማንነት አልተገለፀም፡፡ ስለዚህ አሸናፊ ገጣሚያኑ እስከ ግጥሞቻቸው ርዕሦች ድረስ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ እነሱም፡-

1ኛ "በረከተ መርገም" - ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ

2ኛ "ናስተማስለኪ" - ጸገየ ወይን ገብረመድህን

3ኛ "እስከ ማዕዜኑ" - ዮናስ አድማሱ

4ኛ "ስሞታ" - መስፍን ሀብተማርያም ናቸው፡፡ ሁሉም ግጥሞች ግንቦት 12 ቀን 1959 በተከበረው የኮሌጅ ቀን በዓል ላይ የቀረቡና የተሸለሙ እንደሆኑ ታውቋል -

---

[33] ይህ ጥናት የሥነ ጽሁፍ ታሪክንም እየተመለከተ ስለሆነ ለዚህ "ማስታወሻ" ተገቢው አክብሮት ሊደረግለት እንደሚገባ አጥኚው ያምናል፡፡ በማስታወሻው ላይ "አቅራቢ" ብሎ የፀሐፊው ስም አልተገለጸም፡፡ የዚህ ፅሁፍ ባለቤትን የማወቅ ጉዳይ አንድ የሥነ-ፅሁፍ ታሪካዊ ምርምር ርዕስ ሊሆን እንደሚችል ማመላከት ተፈልጓል፡፡

አባሪ“ሀ”ን ይመልከቱ። ባለ 11 ገጽ የመስፍን ሀብተማርያም “ስሞታ”ን የዚህ የጥናት አካል ለማድረግ፣ 4ኛ ደረጃ ወጥቶ በኮሌጅ ቀን በዓል ላይ እንዲነበብ መደረጉ እንደ ሰበበ ጥናት ተወስዷል።[34] ይሄ ግጥም በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ቤተመፃህፍት ክፍል እንዴት እንደተገኘ ለሌሎች ተመራማሪዎች አንዳች ነገር ሊጠቅም ይችላል በሚል፣ በሚቀጥለው ክፍል ከ1960 አሸናፊ ግጥሞች ጋር በአጭሩ ተወስቷል። “ስሞታ” አባሪ “ለ” በሚለው ስር ቀርቧል።

3.11 1960 - የዓመቱ አንኳር ሁነቶች ቅኝት እና የግጥም ውድድር

ከ1954 ዓ.ም. ጀምሮ የአሜሪካዊያን ጣልቃ ገብነትና የበላይነት አሳስቧቸው በይፋ ከተቃወሙበት ጊዜ ጀምሮ፣ ተማሪዎች ጥላቻቸው እየጠነከረ ሄዷል። በዚህ ዓመትም የተማሪዎችን ትኩረት ስቦ እያስቆጣቸው ካሉ ጉዳዮች አንዱና ቀዳሚው ነው - የአሜሪካ “ወዳጅነት።” አሁን ጥላቻቸው (በተለይ በግንባር ቀደምት መሪዎቹ) ርዕዮታለማዊ መልክ ሁሉ አለው፤ ኢምፔሪያሊዝምን የምታስፋፋ ሃገር በመሆኗ በራሱ የሚጠሏት ተማሪዎች ተበራክተው ነበር።

የኮሌጅ ቀን በዓል፡- በዚያ ዓመት የኮሌጅ ቀን በዓል ስለመከበሩ የሚያወሳ የጽሁፍ መረጃ አላገኘሁም። ነገር ግን፣ የዓመቱ የግጥም ውድድር አሸናፊ ግጥሞች በኮሌጅ ቀን እንደሚነበቡና እንደሚሸጡ የሚገልፅ የፅሁፍ መረጃ ስላለ፣ በዓሉ እንደተከበረ መገመት እንችላለን።

የግጥም ውድድር፡- የዚያ ዓመት የግጥም ውድድር የተካሄደው በልደታ አዳራሽ ሲሆን ቀኑ ግን አልተጠቀሰም። የራስ መኮንን አዳራሽም ግልፅ ባልሆነ ምክንያት እንደተከለከለ በ Struggle[35] ተገልጿል ጋዜጣ። በውድድሩ የተሳተፉት 12 ገጣሚዎች ሲሆኑ፣ ብዙዎቹ ተማሪዎች እንደሚስማሙት የዚያን ዓመት ግጥሞች ከቀደመው ዓመት ከ1959 በደረጃ ዝቅ እንዳሉ ተጠቁሟል። አጠቃላይ ውድድሩን አስመልክቶ ወደ ኋላ ላይ የሚነሱ ሊያከራክሩ የሚችሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ እንዲያስችል Struggle ያሰፈረው እንደሚከተለው ተጠቅሷል፤

> Most students agreed that the poems were generally below last year's standard with the incomparable poem of imprisond Ato Hailu G.Yohannes, “Bereket Mergem”, still to be matched. The attendance was large and lively. Towards the end, boredom overpowered most of

[34] ስለዚህ ጉዳይ መስፍን ሃብተማርያምን በ5-03-2002 ጠይቂያቸው፣ “‘ግጥሙ ማርክሲስታዊ የሶሻሊዝም አቀንቃኝ ስለሆነ ለትግላችን ይፈለጋል … 4ኛ የወጣ አትሸልሙ የሚል ህግ መቼ ወጣ’ … ብለው በበዓሉ ላይ እንዳቀርብ አደረጉኝና ሰዓት ሸለሙኝ” በማለት የተማሪ መሪዎቹ ግጥማቸውን እንደመረጡት ነግረውኛል።
[35] Vol. II, No. 3, 1963: 3

the students. The poets dealt with social problems as usual. This is a great and encouraging development and is indicative of the university students shouldering their social responsibilities. Most of the poets agreed that it is the economic environment that shapes the individual. Ato Getachew Seiffu, Bussiness IV, `Artist Yelesh Kizhet` came out first with Ato Almayehu Alemneh's (Theo. III), a close second with "Bemar Telewiso." Ato Mesfin G.Hiwot, who was fourth last year, became third this year with "Felega". Ato Teklu Minas came out fourth with "erbete Tsehay." The poems will be read and sold to the public on the university day (ገጽ 5፤ ዝነክማሁ፣ አጽንኦቱ የኔ ነው).

በጥቅሱ እንደተመለከተው፣ በግጥም ውድድሩ ላይ ብዙ ታዳሚ ቢገኝም፣ ወደ መጨረሻ ላይ አሰልቺ እንደነበር፣ ገጣሚያኑ ያነሱት የተለመደው ማህበራዊ ችግር እንደሆነና ይህም የሚበረታታ እድገት እንደሆነ ተገልጿል።

ለዚህ ዓመትም "የኮሌጅ ቀን" በዓል 4 ተሸላሚ ግጥሞች የተመረጡ ሲሆን፣ በኮሌጅ ቀን ግጥሞች (መጽሐፍ) ውስጥ፣ "አርስት የለሽ ቅዠት" በሚል ርዕስ 1ኛ የወጣው የጌታቸው ሰይፉ ግጥም ብቻ ነው የታተመው። ሌሎቹ ተፈልገው እንዳልተገኙ ተገልጿል።

የዚህ ጥናት አቅራቢ የጠፉትን ግጥሞች ፈልጐ የጥናቱ አካል ለማድረግ ያሉትን አማራጮች ሁሉ ለመጠቀም ሞክሯል። የመጀመሪያ ፍንጭ የተገኘው ከ"በረከተ መርገም" የግጥም መድበል ነበር። ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ በመጽሐፋቸው መግቢያ፣ መስፍን ሃብተማርያም በኮሌጅ ቀን ግጥሞች ውድድር ላይ ሁለት ጊዜ አሸንፈው እንደተሸለሙ የገለፁትን አጥኚው አገናዘበ። በተገኘው ፍንጭ መሰረትም፣ መስፍን በ1959 "ስሞታ" በሚል ርዕስ 4ኛ ወጥተው እንደተሸለሙ በአባሪ "ሀ" በተጠቀመው "ማስታወሻ" አረጋገጠ። ግጥሙም በኢትዮጵያ ጥናት ቤተ መፃህፍትና ቤተ መዛግብት ውስጥ ተፈልጐ ተገኝቷል። ስለዚህ አንደኛው ታወቀ ማለት ነው፤ ሁለተኛው ያሸነፉበት ዓመት በ1960 ዓ.ም. ሲሆን እንደሚችል ይገምታል። በዚያ ውድድር ላይ፣ 3ኛ የወጣው "Felega" በሚል ርዕስ፣ "Mesfin G. Hiwot" የሚባል ሰው እንደሆነ ተጠቁሟል። "G.Hiwot" የሚለው የአባት ስም በስህተት ሊሆን ይችላል አለና መስፍን ሀብተማርያም በሚል "ካታሎግ" ውስጥ ሲፈልግ አገኘ። ገጣሚው መስፍን ሐብተማርያም እንደሆነ አረጋገጠ። "ፍለጋ" ብቻውን ተጠርዞ እንደተቀመጠም ገመተ፤ የቤተ መፃህፍቱ ሠራተኞች ብዙ ከለፉ በኋላ አገኙት። ሌሎቹም ለብቻ መለያ ቁጥር እየተሰጣቸው ይኖራሉ በሚል፣ አጥኚው በትጋት መፈለጉን ተያያዘው። "በማር ተለውሶ" በሚል ርዕስ 2ኛ የወጣው የዓለማየሁ ዓለምነህ ግጥምም ተገኘ። 4ኛ የወጣው የተክሉ ሚናስ "እርባዕተ ፀሐይ" በደራሲው ስም "ካታሎግ" ላይ መለያ ቁጥር ተሰጥቶት የተመዘገበ ቢሆንም ተፈልጐ ግን አልተገኘም።

እናም በዚህ ዓመት 4ኛ ከወጣው በስተቀር ሁሉም አሸናፊ ግጥሞች ስለተገኙና የጥናቱ አካል ስለሆኑ አባሪ ተደርገዋል (አባሪ "ሐ" እና አባሪ "መ"ን ይመልከቱ)።

ምዕራፍ አራት

የአሸናፊ ግጥሞች ትንተና

"የኮሌጅ ቀን" ገጣሚያንን ማህበረ ፖለቲካዊ አመለካከቶችና ሂሶች ለማርቀቅ፣ ግጥሞቻቸውን ከወጡበት ማህበረ-ፖለቲካዊ አውድ (socio political context) አንፃር መተንተን ያስፈልጋል። ምክንያቱም፣ ግጥሞቹ እንደ ሥነ ጽሁፍነታቸው የወጡበትን ማህበረሰብ አሻራ ማንሳታቸው አይቀርምና። ይህን አስመልክቶ ቴዎድሮስ ገብሬ "The role of literature is to say what a period thinks of itself" የሚለውን የMacherey'ን አባባል በቀዳሚነት አጣቅሰው፣

> ሥነ ጽሁፍ ብዙውን ጊዜ ለተፃፈበት ዘመን ጥበባዊ አንደበት ነው። በገሀድም ይገለጥ፣ በረቀቀ መንገድም ይቅረብ ሥነ ጽሁፍ፣ የዘመኑን መንፈስ የመቅረፅም ሚና አለው። የደራሲውን ፖለቲካዊ አቋም እናይበታለን፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ድምፁን እናደምጥበታለን። አንዳንዴም፣ በተለይ ከታላቅ ተመስጦ እና አንፃሮት የሚወለዱ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎች ትንቢታዊነት (prophetic voice) አያጣቸውም[36]

በማለት ርዕሠ ጉዳዩን በአፅንኦት ገልፀዋል። በመሆኑም ይህ ጥናት የባለሙያዎቹን ንድፈ ሀሳባዊ መሠረት ማንፀሪያ አድርጐ፣ ግጥሞቹ እንደቀረቡበት ዓመተ ምህረት በቅደም ተከተል ያነሱት ሀሳብ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ጭብጣዊ ትንተና አድርጓል።

4.1 የ1951 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና

በኮሌጅ ቀን በዓል ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ አሸንፈው ከቀረቡት ግጥሞች ውስጥ የተገኘውና በየኮሌጅ ቀን ግጥሞች መድበል ላይ የታተመው ተገኝ የተሻወርቅ ተወዳድረው አንደኛ የወጡበት ግጥም ነው።

የተገኝ፣ "ሰው እንቆቅልሽ"፣ የሰው ልጅን ምንነት ከክፋትና ከደግነት የስነ-ምግባር መርህ አንፃር የሚመረምርና የሚጠይቅ ሲሆን፣ ለጥያቄው እራሱ መላምት የሚገልፅና በኋላም መላምቶቹን አጠናቅሮ የሚመልስ፣ ሰብአዊ እውነቶችን ያቀነቀነ፣ ሁለንተናዊ ጭብጥ (Universal Theme) ያለው ግጥም ነው። የሰው ልጅን "ይሄ ነው ብላችሁ" ንገሩኝ የሚለው ጥያቄውም ሆነ፣ በተከታዮቹ አንጓዎች (stanzas) የሚመልሰው የሰው ልጅ አጠቃላይ ነቢባዊና ገቢራዊ ሕይወት መሠረቱ፣ ሰውነት ወይም ሰብአዊነት ነው። የአንድ ሰው ወይም ፍጡር አካባቢያዊ መስተጋብር መሠረት አድርጐ ከመጠየቅ ይልቅ የሰው ልጅን

---

[36] ይህ ማብራሪያ፣ ቴዎድሮስ በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ ከሚለው መጽሐፋቸው ገጽ 217 ላይ እንዲሁም፣ "የዘመን መንፈስ በተመረጡ የአማርኛ ልብ ወለዶች ውስጥ" የሚለው ጥናታቸው በታተመበት መድበለ ጉባኤ ገጽ 153 ላይ ቃል በቃል ሰፍሮ ይገኛል።

ጥቅል ባህሪያት ማውጠንጠን ላይ አትኩሯል። ለዚህ ነው፣ ሁለንተናዊ ጭብጥ አለው የተባለው።

የግጥሙ ተናጋሪ ወይም ተራኪ እራሱ ጠይቆ እራሱ ምላሽ የሚሰጥበት ሁኔታ ደግሞ በራሱ፣ ጥያቄ ያስነሳል፤ ጥያቄውን ግን የግጥሙ ቅርጽ መልሶታል። ግጥሙ፣ በውስጡ ካነሳቸው መሠረታዊ ሰብአዊ እውነቶች አንፃር ሰው ልንላቸው የምንችለው ሁለት ገፀባህርያት በ"ሀ" እና በ"ለ" ተመስለው ቀርበዋል። እነዚህ ምስለ ሰዎች የሚያነሷቸው ሰዋዊ ጥያቄዎች የቀረቡት በምልልስ መልክ በመሆኑ በቅርፁ "ተውኔታዊ ግጥም"[37] የሚባል ይመስለኛል። ለአስረጅነት፣ የግጥሙን የመጀመሪያ ሁለት አንጓዎችን ጠቅሰን ጭብጣዊ ትንታኔያችን እናጠናክር።

ሀ፡ ንገሩኝ እናንተ፣ ገባን የምትሉ
ይሄ ነው ብላችሁ፣ የሰው ልጅ ባህሉ
ክፋቱን ጥፋቱን፣ ባንድ ፊት አርጉና
ልማት ደግነቱን፣ ወደዚህ ለዩና
አንፍሱ አንጓሉና፣ ብጥር አድርጋችሁ
ንገሩኝ የሰው ልጅ፣ ይሄ ነው ብላችሁ።

ለ፡ በሰፌድ ተንጓሎ፣ ምርትና እንክርዳዱ
የሚለይ አይደለም፣ አንደኛው ከአንዱ።
እንደ ስንዴ አይደለም፣ የሰው ልጅ ፍጥረቱ
ተንጓሎ የሚለይ፣ ገለባና ምርቱ።
ስንዴና እንክርዳድ ነው፣ ባንድነት ታምሶ
ምርቅና ፍትፍት ነው፣ ባንድ ተለውሶ
ተዋሕዶ ያለ፣ ባንድ አካል ባንድ አምሳል
ጥፋትና ልማት፣ የሰው ልጅ ይባላል። (ገጽ፥ 1 እና 2)

ከአንጓዎቹ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው በ"ሀ" የተወከለውን ሀሳብ በግጥሙ ውስጥ ጥያቄ አቅራቢና ለጥያቄዎቹ የሚሆኑ ማጣያ መላምቶችን አመንጪ ሆኖ ቀርቧል። የሰው ልጅ ጥፋቱንና ልማቱን አንጓሎ ሲያዩበት ሰዋዊነቱ ምን ሊሆን እንደሚችል፣ "ይሄ ነው" ተብሎ ሁሉ እንዲገለፅ ይጠይቃል። በ"ለ" የወከለው ምስለ ገፀ ሰብ ግን የሰው ልጅ እንደ ስንዴና እንክርዳድ በሰፌድ ተንጓሎ ጥፋቱንና ልማቱን አይለይም በማለት ይመልሳል። የሰው ልጅ፣

---

[37] ይህን በሚመለከት፣ የብርሃኑ፣ <u>የአማርኛ ሥነ ግጥም</u> (1999 ዓ.ም.) ገጽ 367 መመልከት ይቻላል።

እኩይና ሰናይ ምግባር በአንድ ተዋህደው የነገሱበት፣ ሰይጣን ወይ መልአክ መሆን የማይቻለው ፍጡር እንደሆነ ተገልጿል። ሁለትዮሽ በአንድነት ስጋ ወደሙ ሆነው የተጣቡት፣ ሰይጣናዊ መልአክ ወይም መላካዊ ሰይጣን" የሆነ ዘረሰብ መሆኑ ተወስቷል።

ቀደም ሲል በቀረቡት አስረጂ አንጓዎች አይነት የውክሎቹ ምልልስ ይቀጥላል። በመጨረሻ ቀድሞ የጠየቀውና የተለያዩ ማንፀሪያ መላምቶችን እየሰነዘረ የተመራመረው ውክል ገፀሰብ ("ሀ")፣ "ብፈልግ ባልፈልግ፣ ቁምነገርም የለው /የሰው ልጅ እንደሆን እሬትና ማር ነው" በማለት የሰው ልጅ እኩይና ሰናይ ምግባር የተካለሱበት ፍጥረት መሆኑን አረጋግጦ፣ "ዐውቆ አለመቻሉን፣ ይህን ለመለወጥ /በከንቱ ሳይደክም ሰው ዐርፎ ይቀመጥ" በማለት ለጥያቄው ምላሽ ማግኘቱን በመግለፅ ግጥሙ ይጠናቀቃል።

እዚህ ላይ የግጥሙ ተናጋሪ፣ የሰው ልጅ ክፉና ደግ ባህሪያት ያሉት ፍጡር ነው ብሎ ብቻ አይደለም ያበቃው፤ ይልቁንም "ሰው" ወይም "ሰውነት" የክፋትና የደግነት ጭምር ፍጥረት እንደሆነ አድርጐ ነው የገለፀው።

ይህ ግጥም ሰዋዊ አጠይቆትን የሚመረምር፣ በጭብጣዊ ዘውጉ "ሀሳባዊ" ወይም "ፍልስፍናዊ" የሆነ ግጥም ነው ማለት ይቻላል። ገጣሚውም፣ "የሰው ልጅን እንቆቅልሽነት" ለመጠየቅና ለመረዳት፣ ያለበት አካባቢ፣ የዩኒቨርሲቲው አውድ መነሻ ወይም መሠረት ሆኖት ይሆን? ብሎ መጠየቅ አይከፋም፤ ከሰው ልጅ ገቢራዊ ሕይወት ተነስቶ፣ የሰው ልጅን ሰዋዊ ውስጠት ሁሉ ለመመርመር የነቃበት ማህበራዊ መስተጋብሩ፣ ይብዛም ይነስም ፖለቲካዊ እርሾ ይኖረው ይሆን? ብሎ መጠርጠርም ይቻላል።

በዚህ ግጥም ላይ ያነሳናቸውና ወደ ፊት የምናነሳቸው ቀርነቶች ወይም ጥርጣሬዎች ምላሽ ካላቸው ወደኋላ ላይ ሌሎች ግጥሞችን ስንተነትን እያናበብን የምንመረምረው ጉዳይ ይሆናል። ከተገኘ ግጥም ቀጥሎ፣ የ1952 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች መተንተን ነበረባቸው፤ ነገር ግን፣ አንድም ግጥም ስላልተገኘ[38]፣ ወደ ሚቀጥለው ዓመት አሸናፊ ግጥሞች እንዘልቃለን።

4.2 የ1953 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና

በዚህ ክፍል ሦስቱን አሸናፊ ግጥሞች እየተናበቡ ይተነተናሉ። ግጥሞቹ፣ የመጀመሪያው የታምሩ ፈይሳ "ደሀው ይናገራል"፣ ሁለተኛ የዮሐንስ አድማሱ "የገደል ስር

[38] የዚህ ጥናት አቅራቢ ግጥሞቹን ለማፈላለግ ቢሞክርም አልተሳካለትም፤ የአሸናፊ ገጣሚዎቹን ማንነት ግን በምርምሩ ለማረጋገጥ ሞክሯል። ከምዕራፍ ሦስት "የ1952 ዓ.ም. ..." የሚለውን ይመልከቱ።

አጥንት" እና ሦስተኛ የከበደ ካሳ "ወይዘሮ ዓለሚቱ ቤቷን አሳየችኝ" ሲሆኑ፣ ሦስቱም ግጥሞች በተመሣሣይ መልኩ የግጥሞቹ ተናጋሪዎች በአንደኛ መደብ አንፃር "እኔ" እያሉ የሚተርኩ መሆናቸው ያመሳስላቸዋል። ለገጣሚዎቹ ስሜቶች የቀረቡ የሰው ልጅ ከንቱነትን፣ ፍርደ ገምድልነትን፣ ጨካኝነትን፣ እራስ ወዳድነትን፤ ከዓለማዊ ሕይወት አላፊነት ወይም ከምድራዊ ኑሮ ጠፊነት ጋር በትይዩ በማቅረባቸውም ይመሳሰላሉ፤ የሰው ልጅን ከንቱነትና የዓለምን ጠፊነት ለማሳየት የተጠቀሙባቸው ማህበራዊ መልኮች፣ የነፍስ ወይም የስሜት ጥያቄዎቻቸውን ያስጓዙባቸው የታሪክ ማጓጓዣዎች (vehicles) በተወሰነ መልኩ ቢቀራረቡም ልዩነታቸው ግን ያይላል።

ግጥሞቹ፣ በበረደ ድንገትም በሰከነ የሕይወት ዑደት ውስጥ የተገጠሙ፣ መንፈሰ ቀዝቃዛ፣ ("ሞት ጠሪ") መሆናቸውም፣ በተመሣሣይ የደበዘዘ አውድ ውስጥ ስለመገጠማቸው እንድንጠረጥር ያነቃሉ። ሞት ጠሪነታቸው፣ መቃብር ቆፋሪነታቸው ወይም ቀዝቃዛነታቸው ደግሞ በእነዚህ አሸናፊ ግጥሞች ላይ ብቻ የታየ አይደለም፤ በእዚህ ዓመት ለውድድር የቀረቡት አስሩም ግጥሞች ይሄን የቀዘቀዘ መንፈስ መጋራታቸውን News and Views (Vol. Iv; No. 60, 1961: 1) የተባለው የተማሪዎች ጋዜጣ በወቅቱ ዘግቧል። ግጥሞቹ ድባባቸው ብቻ ሣይሆን ጭብጣቸውም እንደሚመሳሰል ጋዜጣው፣ "such serious themes as death, life, hereafter and injustice" በማለት ጠቁሟል። ገጣሚዎቹ፣ በተመሣሣይ ርዕሠ ጉዳዮችና ድምፀቶች ስሜታቸውን ለመግለፅ መታተራቸው፣ ከጥቂት ወራት በፊት የተነሣው የታህሳሱ ግርግርና ከመፈንቅለ መንግስት ሙከራው ጋር በተያያዘ ሕይወታቸው ያለፉት ዜጎች ጦስ የፈጠሩባቸው አጋጣሚዎች ይሆኑ? አጠቃላይ ሁኔታው ከየግጥሞቹ ማሳያዎችን እየነቀስን እናስተንትን።

"ደሀው ይናገራል" ታምሩ ፈይሳ

ይህ ግጥም፣ የደሀውን የህብረተሰብ ክፍል ችግር፣ መከራ፣ ስቃይ፣ እንግልት የተለያዩ ማሳያዎች ዋቢ አድርጐ ይናገራል። የዘመኑን ሰው፣ ስግብግብነት፣ እንስሳነት፣ ፍርደ ገምድልነት በፅኑ ይሄሳል። የግጥሙ ተናጋሪ "እኔ" እያለ፣ የገጠመውን መከራና ስቃይ፣ ማህበራዊ መስተጋብሩ የፈጠረበትን ክስተት ማንፀሪያ አድርጐ ይተርካል። ግጥሙ የአንጻርና የድምፀት መዘበራረቅ የሚታይበት ይመስላል። ይህም ግጥም፣ እንደ የተገኘ "ሰው እንቆቅልሽ ነው"፣ የሰው ልጅ፣ ሁለትዮሽ በአንድነት የነገሰበት ፍጡር መሆኑን ያስረዳል። የተገኘ ግጥም፣ "ሰው"፣ እኩይነትና ሰናይነት ስጋና ደም ሆነው ያቆሙት

ስለመሆኑ፣ "ብፈልግ ባልፈልግ ቁምነገርም የለው /የሰው ልጅ እንደሆን፣ አሬትና ማር ነው" (ገጽ፥ 5) ያለውን በመጥቀስ የታምሩ ግጥም፣ "ሰው"፣ በሕይወትና በሞት መካከል የተወጠረ ከንቱ ፍጡር ሆኖ መሣሉን ከገለፀባቸው፣ "መንትያ ነገሮች ሁለቱም አሬት/ ናላን አቃውሰዋል መኖርና ሞት" (ገጽ፥ 10) ከሚሉት ስንኞች ጋር እያፈካከሩ ማንበብ ይቻላል፤ በአንድ ይሰምራሉም፡፡

ታምሩ፣ በግጥማቸው የሰው ልጅን ባህሪ የሚመረምሩ ስነምግባራዊ ጭብጦችን ማንሳታቸው፣ ግጥማቸው ሁለንተናዊ ጭብጥ የሚያስተጋቡ፣ ርዕሠ ጉዳዮችን ማንሳታቸውን ያፀናሉ፡፡ ሰው ሰው የሚሸቱ፣ ከማህበራዊ ሕይወት በጥልቀት የተፈተሹ ሰዋዊ እውነቶችን በማመላከት፣ ብዕራቸው ማህበራዊ ሂስ ለማቅረብ ያለውን ድፍረትም አሳይተዋል፡፡ የሚከተሉት ስንኞችም ይህን እውነት ያስረግጣሉ፤

በገንዘብ መንጠቆ ዓለም ወጥመድ ገብቶ
አዳም ምስጥ ሆነብኝ ሰውነቱን ትቶ፡፡
አለበት አየበት ወደ ነፈሰው
እስስት ሆኗል አሉ የዘመኑ ሰው፡፡ (ገጽ፥ 9)

እዚህ ላይ፣ የግጥሙ ተናጋሪ በታዘበው ዘመን ያሉ ሰዎች፣ በአንድ በኩል እንደ ምስጥ ውስጥ ውስጡን የሚሄዱ ፍቅረ ነዋይ ወኔያቸውን የሰለባቸው፣ ለሆዱ አደር ፈሪዎች መሆናቸውን ተመላክቷል፤ በሌላ በኩል፣ እንደ እስስት ባህሪያቸውን እየቀያየሩ በሞቀበት እንደሚዘፍኑ ተጠቁሟል፡፡ በተለዋጭ ዘይቤነት (Metaphor) ለባህሪ ማንፀሪያነት የገቡት "ምስጥ" እና "እስስት"፣ እራስን ሆኖ ያመኑበትን ነገር በፊት ለፊት ከመጋፈጥ ይልቅ፣ ከነጭራሹ ሣይታዩ ውስጥ ውስጡን መጓዝን ወይም መመሣሰልን ያመላክታሉ፡፡ የራስ የሆነን ቋሚ ነገር ማጣትን ሁሉ ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ ጀርባ ታዲያ፣ እራስን አለመሆን ምን አመጣው? ሆድን ስመሙላት ["ሆድ" ሌሎች የጥቅም ጉዳዮችን ሁሉ እንደሚወክል ማሰብ ብልህነት ነው እንዲሉ] አድር ባይ መሆን ለምን አስፈለገ? ሲባል፣ "ፍርሃት" የሚል ምላሽ መስጠት ይቻላል፤ የራሱ የሆነ ነገር የሌለው ደሃ፣ "ራሱን መሆን" እንዴት ይቻለዋል!? ስለዚህ ጦም የማደር ፍርሃት፣ ደሃ ሆኖ የመቅረት ፍርሃት ገጣሚው የታዘባቸው ሰዎች "ፍርሃት" ነው ቢባል ያስኬዳል፡፡

ይህ "ፍርሃት" ግን ማህበራዊ ሕይወት የወለደው ብቻ አይመስልም፣ "ፍርሃት" ከመደባዊ ባህሪው የተነሣ ፖለቲካዊ መልክም አለው፤ ፈሪ ካለ የሚፈራ ነገር አለ ማለት ነውና፡፡ ደሃው እንዲናገር፣ ደሃውን የሚያናግር ወይም ደሀውን "የሚያደምጥ" ("የሚሰማ" የሚለው የሚሻል ይመስለኛል) አካል ያስፈልጋል፤ በዚህ አውድ "ሀብታም" ሊባል ይችላል፡፡

ስለዚህ፣ በማህበራዊ ሕይወት የተፈጠረው ፍርሃት በማህበራዊ መስተጋብር የማይሽር፣ ርዕዮተ ዓለማዊ የሆነ መሠረት ያለው፣ ድንገትም መንግስታዊ ውሳኔዎችን (የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጦችን) የሚጠይቅ ፖለቲካዊ መልኮች አሉት ቢባል ያስኬዳል፤ ማስረጃዎችን እያጣቀስን በአነሳነው ሀሳብ እንግፋበት፤

ያችን አህያዬን የገዛኒትን
አርፎባታል አሉ የጅቦች አይን።
ብለቃት ይሻላል እንደው ዝም ብዬ
ላስጥላት አልችልም ከጅብ ተታግዬ።
ጅቡ ሲቦድሳት እንዳትጮህ ደግሞ
ልታናፋ አትችልም አፏ ተለጉሞ። (ገጽ፥ 7)

የግጥሙ ተናጋሪ “እኔ” እያለ ስለ ድህነቱ፣ እየተናገረ መሀከል ላይ “አህያ” ስለመግዛቱ “ይዘባርቃል”፤ ይሄ መዘባረቁም በራሱ የሚናገረው ነገር እንዳለው መገመት ይቻላል፤ አህያዋ ላይ የጅብ አይን እንዳረፈባትና ከጅብ ጋር መታገልና ማስቀረት ስለማይችል አሳልፎ እንደሰጣት ይተርካል፤ እዚህ ላይ፣ የግጥሙ ተናጋሪ፣ በድንገት ስለ “አህያ” እና “ጅብ” ማውሳት ለምን ፈለገ? ስለመናጢ ድህነቱ እየተናገረ አህያ መግዛት መቻሉን ለመተንፈስ መቻኮሉ ከምን የተነሳ ነው? ቢባል መልሱ ብዙ መመራመር የሚጠይቅ አይመስለኝም። የግጥሙ ተናጋሪ፣ በአህያና በጅብ ማሳያነት፣ ሊገልፅልን የፈለገው ጉዳይ አለ። የአህያዋን ጉዳይ የሚያወሱት ስንኞች በአንድ ተዋቅረው አንድ አሊጎሪያዊ ትረካ ፈጥረዋል፤ ስለዚህ አህያና ጅብ የተለያዩ ሰዎች ባህሪና ግብር የወከሉ ትዕምርቶች ናቸው። እነዚህ ትዕምርቶች ደግሞ ሁለት አይነት ፍች ይነግሩናል። “አንደኛው ፍቺ የታሪኩ ላዕላይ ፍቺ ወይም ዝርው ፍቺ ሲሆን ሁለተኛው አንባቢ በራሱ ትርጓሜ የሚደርስበት የአንድምታ ፍቺ ነው” (ብርሃኑ፣ 1979፥ 322)። የግጥሙ ተናጋሪ ሁለተኛውን ፍቺ አስቦ እንዳወሳቸው መገመት አይከብድም።

እዚህ ላይ የገጣሚውን ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት እጦት ሁሉ እንድናስብ እንገደዳለን። ገጣሚው አህያንና ጅብን የሃሳቡ ማሄጃ አድርጐ ለመጠቀም የተገደደው፣ ያለ አህያና ጅብ ሀሳቡን እንዳለ በቀሙ መናገር፣ ማስተላለፍ ባለመቻሉ እንደሆነ ማስተንተን ይቻላል። አሊጐራዊ ትረካ[39] የመጠቀም ብልሃት የመጣው፣ ከዚህ ሀሳብ ከመግለፅ ነፃነት እጦት ነው ሊባል ይችላል። የግጥሙ ተናጋሪ የደረሰበት በደል የገዛትን አህያ በመወሰዷ ብቻ

[39] ብርሃኑ (1999፥ 321) አሊጐሪያዊ ትረካ አራት ባህሪያት እንዳሉት ጠቁመዋል፤ እነሱም፤ ግጥሙ አንድ ታሪክ መናገሩ፤ ባለታሪኮቹ ብዙ ጊዜ እንስሳት፣ ዕጽዋት፣ የተፈጥሮ ክስተቶች፣ ወዘተ.፣ መሆናቸው፤ ሁለት ፍች ያለው (አንደኛው ላዕላይ /ዝርው/ ፍቺ ሲሆን ሌላኛው አንባቢው በራሱ አረዳድ የሚደርስበት የአንድምታ ፍቺ) መሆኑ፤ ግጥሙ የሚጨርሰው ገጣሚው ሊገልፀው የፈለገውን በመናገር መሆኑን ገልፀዋል።

አያበቃም፤ የጅቦቹን ግፍና መከራ ትንፍሽ እንዳይልም፣ በፍርሃት ተለጉሟል። አህያዋ እንዳታናፋ አፏን የመለጐሚ ክስተትም ከተናጋሪው ደሀ ጋር በትይዩ የሚናበብ ሀቅ ነው። የግጥሙ የመጨረሻ አንጓም የተባለውን ሀሳብ ያፀናል።

> ኧረ ቀኑ መሽ 12 ሰዐት
> ሠፈሩ እርጭ አለ እንደ ወና ቤት
> ጅቡም ይጮህ ጀመር ወሮቹም በረሩ
> ታሪኬን አቆምኩኝ በሉ ደህና እደሩ። (ገጽ፥ 11)

የግጥሙ ተናጋሪ ወይም ደሃው ተናጋሪ፣ ንብረቱን በጉልበት በዘረፉት ሆዳሞች የደረሰበትን ድህነት በተለያዩ ማህበራዊ ማንፀሪያዎች አዋገርነት ዘርዝሮ አልጨረሰም። የሚያስፈራው "ጅብ" አሁን አያየኝም ብሎ ስለ ድህነቱ እየተናዘዘ እያለ፣ በድንገት የጅቡን ጩኸት ሲሰማ ነው፣ "ታሪኬን አቆምኩኝ ..." ለማለት የተገደደው። በፍርሃት ንግግሩን ባያቆም ኖሮ፣ "ታሪኬን ጨረስኩኝ" ባለ ነበር፤ እሱ ግን አላለም። ግጥሙ ጥልቅ ፖለቲካዊ ቁዘማ መሆኑን እንደዚህ ከቅርፁም ማስተንተን ይቻላል።

አሁን ግጥሙ፣ በወቅቱ የነበረውን የፊውዳል ስርዓት ሽንቋጭ ስለመሆኑ ሊያጠራጥር አይገባም። ጭሰኛንና ፊውዳልን፣ ድሃንና ሀብታምን፣ ተገዢንና አገረ ገዢን በአህያና በጅብ ወክሎ፣ "ነበር" የሚባለውን መደባዊ ክፍፍል ለማሳየት የጣረው። በተለይ ይህን አሽሙራዊ ግጥም፣ በንጉሡና በሹማምንቶቻቸው ፊት በድፍረት መቅረቡ ብዙዎቹን አስገርሟል[40]። የገጣሚው ድፍረትም፣ የታህሳሱ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ከፈጠረው የዘመን መንፈስ ጋር ሊናበብ የሚችል ይመስላል።

---

[40] ይህን ጉዳይ አስመልክቶ፣ Richard Greenfield የሚባሉ መምህር "A NOTE ON A MODERN ETHIOPIAN PROTEST POEM" በሚል ርዕስ የዮሐንስ አድማሱን "እስኪ ተጠየቁ" ወደ እንግሊዘኛ ተርጉመው በተከታተኑበት መጣጥፋቸው መግቢያ ላይ፣ ስለታምሩ ፊይሳ "ደሀው ይናገራል" አንዳንድ ነገሮች አውስተዋል። "... when a poem, read before the emperor and entitled 'The poor Man speaks', was written and delivered in a manner which could easily be interpreted as sever criticism of government and <u>ipso facto</u> therefore (in Ethiopia) of the Emperor" (ገጽ፥ 18) በማለት የግጥሙን ፖለቲካዊ ሂስነት ዕፊዋል። ግጥሙ፣ የመነጋገሪያ ትልቅ ርዕስ መሆኑን፣ የግጥሙ የተወሰኑ ቅጆች ወዲያው ተሽጠው ማለቃቸውን፣ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ቅጆቹ ማታ ላይ በአዲስ አበባ ጭፈራ ቤቶችና ቡና ቤቶች ውስጥ ቀን ከተሸጡበት በብዙ እጥፍ መቸብቸባቸውን Greenfield በማስታወሻቸው (ገጽ፥ 18) ላይ አስፍረዋል።

“የገደል ስር አጥንት”[41] ዮሐንስ አድማሱ

ከመነሻው፣ “የገደል ስር አጥንት”ን ሳነብ ርዕሡ ጉዳዩ ከሌሎች የኮሌጅ ቀን ግጥሞች ወጣ ያለ መሰለኝ፤ ዮሐንስ በምናባቸው የፈጠሩት ወይስ፣ በገቢራዊ ሕይወታቸው ያጋጠማቸው አጥንት ይሆን? የሚል ጥያቄ በአእምሮዬ አቃጨለ። ግጥሙን ደጋግሜ ሳነበው ግን በገቢር ያጋጠማቸው ክስተት መሆኑን የሚጠቁሙ ስንኞች ለመመርመር ሞከርኩ። የሚከተሉትን ስንኞች በአስረጂነት እንመልከት፡-

ለኔ የሚሸተኝ የዚህ የደን ሽታ፣
መዓዛው ጣዕሙ ዓለም የሚፈታ፣
የየወፉ ዜማ ስልቱ የዝማሬ፣
እኔ የምሰማው በሕሊና አንጽሬ፣
ምንድር ነው ስሜትህ ተነስ ንገረኝ፣፣
ነገርህን ባውቀው ደግሞም ቢገባኝ። (ገጽ፥ 23)

ስንኞቹ፣ ገጣሚው፣ የወደቀውን አጥንት ካገኙበት ቦታ፣ ወፎች ዝማሬያቸውን የሚያሰሙበት፣ ማዕዛው የሚሸት ደን ያለበት እንደሆነ ይገልፃሉ። ታዲያ ይሄን አካባቢያዊ ገለፃ ገጣሚው በሌሎች ስራዎቻቸው ላይ ባልተለመደ መልኩ፣ ስዋዊ አጠይቆት በሚናጥበት በዚህ ግጥም መሀከል ላይ ለምን ሰነቀሩት? ብሎ መጠየቅ ይቻላል። ምላሹ፣ ገጣሚው ምናልባት ተፈጥሮን እያደነቁ እያለ በድንገት የገደል ስር አጥንቱን በመመልከታቸው፣ የነበረውን ድባብ እና ስሜት በብዕራቸው ከትበውት ይሆናል ብሎ መጠርጠር አይከፋም።

ይህ ግጥም፣ መቃብር ንቆት ከገደል ስር የወደቀ አጥንትንና እኔ እያለ የሚተርከውን የግጥሙን ተናጋሪ በፊት ለፊት አገናኝቶ የሚያዋራ፣ በቅርፀ የተለያዩ ሀሣቦች በቅደም ተከተል የሚያወሳ ተራኪ ግጥም ነው። ሰው በናቀው አጥንት መነሻነት ብዙ ሰዋዊ የሕይወት እውነቶች፣ በማህበራዊ ሂስ ማንፀሪያነት ቀርበዋል። የግጥሙ ተናጋሪ፣ የወደቀውን አጥንት ሲያይ፣ ነገ እሱ ሲሞት የሱም አጥንት እንዲህ አስታዋሽ ያጣል ብሎ ስጋቱን ይገልፃል። በሃብትና በንብረት መለያየት በሕይወት እያሉ እንጂ ሲሞቱ ሁሉም እኩል እንደሆኑ በመግለፅ የሰው ልጅን ከንቱነት ያስረዳል። የሚከተሉትን ስንኞች በዋቢነት እንመልከት።

---

[41] ገጣሚው፣ በ1953 ዓ.ም ያሸነፉበት ግጥም ሲሆን፣ በየኮሌጅ ቀን ግጥሞች መጽሐፍ ላይ ግን 1954 ዓ.ም ተብሎ ተገልጿል። እስኪ ተጠየቁ በሚለው መድበል ውስጥ “1954(?)” በማለት፣ አሳናኙ መጠራጠራቸውን ማመላከታቸው ግን፣ ጥንቃቄን የሚያስተምር ይመስለኛል።

ያየሁትን አጥንት መቃብር ንቆት፣

ከገደል ሥር ወድቋል ሰው ሁሉ ረስቶት።(ገጽ ፥ 17)

....

ለየትኛው ዓለም ይህ ዘመነ ቅጽበት መላ የሌለው

ለየትኛው ጊዜ ለተራቆተው፣ (ገጽ፥ 21)

የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች፣ የሰው ልጅ እስትንፋሱ ከተቋረጠ በኋላ በድኑን ቢጤውም እንደማያስታውሰው፣ ግዑዙ ማረፊያ ቦታውም እንደሚንቀው የሚያነቁ ሥነ-ምግባራዊ ጭብጥ የያዙ ናቸው። ቀጣዮቹ ሁለት ስንኞች የሰው ልጅን ከንቱነት፣ የዓለምን ወይም የምድራዊ ሕይወትን በቶሎ አላፊነት ያስታውሳሉ፣ አለፍ ሲልም፣ የግጥሙ ተናጋሪ በዓለማዊ ኑሮ ተስፋ መቁረጡን ያወሳሉ። "የገደል ስር አጥንት" ቀጥለው ከሚተነተኑ ግጥሞችም ጋር ይናበባል።

"ወይዘሮ ዓለሚቱ ቤቷን አሳየችኝ" ከበደ ካሳ

የከበደ ግጥም ከርዕሡ ጀምሮ "ወይዘሮ ዓለሚቱ" ስለምትባል እንስት የሚተርክ ይመስላል። ነገር ግን፣ "ዓለሚቱ" በተፀውኦ ስምነት የሚያገለግል ቃል አይደለም። ይልቁንም፣ ዓለምን (world'ን) ይመለከታል። የግጥሙ ተናጋሪ፣ የዓለምን ወይም የምድርን ሁኔታ ለመታዘብ መብቃቱን፣ ወይም ወደ ምድረ-ዓለም መቀላቀሉን እና በዓለም ላይ በሚያየው የሰው ልጅ ባህሪና ግብር ማዘኑን ያወጋበት በቅርፁ ተራኪ የሚባለው የግጥም አይነት ነው። ጭብጡ ስነምግባር ላይ ያተኮረ፣ የዓለም አላፊነት፣ የሰው ልጅን መሰሪነት፣ ምንዱባንነትና ባለፀግነት ብሎም ከንቱነት (ሟችነት) የተለያዩ ማህበራዊ ማሳያዎችን ማንፀሪያ አድርጐ የሚተርክ ግጥም ነው። ከየተገኘ፣ ከታምሩ በተወሠነ መልኩ ከዮሐንስ ግጥሞች ጭብጦችና ርዕሠ ጉዳዮች ጋር ይመስላል።

የከበደ ግጥም፣ እንደ "ሰው እንቆቅልሽ ነው" እና "ደሀው ይናገራል" የሰው ልጅን መልአካዊ ሰይጣንነት ወይም ሰይጣናዊ መልአክነት ይገልጣሉ። እንደ ልዩነት ከተነሳ ሁለቱ (የተገኘ እና የታምሩ) ግጥሞች፣ "ሰው"ን በቀጥታ የሚያመለክቱ ሲሆኑ፣ "ወይዘሮ ዓለሚቱ ቤቷን አሳየችኝ" ግን በ"ዓለም" ወይም በ"ምድር" ማሳያነት ነው፣ ሰውነትን ወይም ሰዋዊ ባህሪያትን ሊበይን የሞከረው። ቀጣይ ስንኞችም ዋቢ ይሆናሉ፤

እስኪ እንመልከተው ያለሚቱን ጓዳ

ጥቅጥቅ ያለበትን ሕያውና ግዑዝ ጠቃሚና ጐጂ አውሬና ለማዳ። (ገጽ፥ 140)

የከበደ ግጥም፣ "የሰው አጥፊው ሰው ነው" የሚለውን የነተገኘን ማህበራዊ ፍልስፍና በፅኑ ይጋራል። የሰውን ከንቱነት፣ የሰውን አጥፊነት የተመለከቱበት መንገድ ሁሉንም ግጥሞች በእጅጉ የሚያመሳስላቸው ይመስለኛል። ማስረጃ ልጥቀስ፤

ጉንፋን ራስ ምታት፣ ሰውን መች ገደለው
የሰው ልጅ እኮ ነው፣ ሰውን የጨረሰው
("ሰው እንቆቅልሽ ነው" ገጽ፥ 4)

በገንዘብ መንጠቆ ዓለም ወጥመድ ገብቶ
አዳም ምስጥ ሆነብኝ ሰውነቱን ትቶ።
("ደሀው ይናገራል" ገጽ፥ 9)

የዓለም ሰው ገበሬ አርሰኸው ነበር፣
ከንቱነት አዝመራን ይኸው ልታዘምር።
("የገደል ስር አጥንት" ገጽ፥ 18)

ተግታችሁ መርምሩ ዘወር ብላችሁ ዕፁት ጉዱ የራሳችሁ
ሰው ሰውንስ መብላት መቼ ተወላችሁ።
("ወይዘሮ ዓለሚቱ ቤቷን አሳየችኝ" ገጽ፥ 141)

እነዚህ ከየግጥሞቹ የተቀነጨቡ መንቶዎች፣ ገጣሚዎቹ ሰውን የሚያዩበት፣ ሰውን የተረዱበት፣ መንገድ ይጠቁማሉ። ገጣሚዎቹ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ የሰው "አጥፊው ሰው ነው" የሚል ማህበራዊ ፍልስፍና ማርቀቃቸው ወይም ማቀንቀናቸው ለተመሳሳይ አውድ የተጋለጠ የሕይወት ገጠመኝ በማሳለፋቸው ይሆን? ብሎ መጠየቅ ይጠቅማል። በሰው ላይ እምነት ማጣትና የሕይወትን ዘበትነት ማቀንቀን፣ የጥርጣሬ በሽታ (skepticism) ተጠቂ መሆንን ወይም ለበሽታው መጋለጥን የሚያመለክት ይመስለኛል። የገጣሚያኑን ህመምተኛነት ወይም ጤነኝነት ደፈር ብሎ ለመናገር፣ የቀጣዮቹን ዓመታት አሸናፊ ግጥሞች እየተነተኑ ማናበብ ይረዳል።

4.3 የ1954 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና

በዚህ ክፍል፣ በ1954 ዓ.ም. በተደረገው የኮሌጅ ቀን ውድድር ላይ አሸናፊ የሆኑ ስራዎች ይተነተናሉ። የመጀመሪያው ግጥም፣ የዮሐንስ አድማሱ "እስኪ ተጠየቁ" ሁለተኛ የይልማ ከበደ "ኑሮ"፣ ሶስተኛ ደግሞ የመላኩ ተገኝ "ሜዳ የቀረኸው" ሲሆኑ የዳኛቸው

ወርቁ "እንቧ በሉ ሰዎች"[42] በአራተኛነት የተመረጠ ስራ እንደነበር በዚህ ጥናት ተረጋግጧልና ዝርዝሩን ከምዕራፍ ሦስት ላይ መመልከት ይቻላል።

እነዚህ ግጥሞች፣ የታምሩ ፈይሳ "ደሀው ይናገራል" በፈጠረው ፖለቲካዊ አንድምታና በታህሳሱ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ሳቢያ ይመስላል ቅድመ ምርመራ (ሳንሱር) ካልተደረጉ አይቀርቡም ተብለው በተማሪዎች መማክርትና በገጣሚያኑ እንቢ ባይነት የቀረቡ ግጥሞች ናቸው። ከነ ታምሩ ግጥሞች ጋር የሚጋሩት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ምልከታ ቢኖርም፣ የነ ዮሐንስ ግጥሞች ግን በማህበራዊ ሂሳቸውም ሆነ በፖለቲካዊ ጉሸማቸው ጠንከር እንደሚሉ ማስተንተን ይቻላል።

"እስኪ ተጠየቁ" ዮሐንስ አድማሱ

"እስኪ ተጠየቁ" በርካታ ርዕሠ ጉዳዮችን ያነሣ፣ ብቻውን ቢጠናም የወጣበትን ዘመን የማሳየት አቅም ያለው፣ የኮሌጅ ቀን ግጥሞች ያነሷቸውን ሀሳቦች ሁሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አስሮ የያዘ ኪናዊ ስራ ነው። እስከ አሁን ከተገኙት የኮሌጅ ቀን ግጥሞች መካከልም መንግስታዊ ስርዓቱን፣ የስርዓቱን አቀንቃኝና አስፈፃሚ የነበረችውን ቤተክርስቲያንን [እምነቱን ሳይሆን ስርዓቱን እንደሆነ ልብ ይባል] በቀዳሚነት በፊት ለፊት የሞገተና የተቸ ስርነቀል ለውጥ አመላካች አብዮተኛ ግጥም ነው ብዬ አምናለሁ።[43]

የግጥሙ ተናጋሪ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ጠይቋል። የተማረውን፣ ወጣቱን፣ ገበሬውን፣ ጸሐፍቱን፣ ፖለቲከኛውን ደብተራውን፣ ባለሥልጣኑን፣ ደሃውን፣ ጭሰኛውን፣ ወጣቱን፣ ፊውዳሉን በየደረጃው "እስኪ ተጠየቁ" ብሏቸዋል። እነዚህን ሰብአዊያን ሁሉ የሞገተው ግን በቀጥታና በፊት ለፊት አይደለም፤ ህላውያን አልሆኑለትም፤ ምላሽ ስላልሰጡት፣ ህያውያን እንዳልሆኑ አስረግጦ ወደ ሙታን መንደር ያቀናል። በህላውያን ዓለም ተስፋ በመቁረጡም በሙታን ላይ አድሮ የሙታን ዓለም ሲያናግር ይታያል። ያን

[42] እነ ዮሐንስ ግጥሞቻቸውን፣ እንዳያቀርቡ ሲከላከሉ፣ "ዮሐንስ አሻፈረኝ ብሎ ..." ሲያነብ ሌሎቻችን ተውን በማለት ዳኛቸው አለማንበባቸውን ገልፀዋል (ኃይሉ፣ 1972፥ 92)። "እንቧ በሉ ሰዎች" በምፀታዊ ስልት የቀረበ፣ በቅርፁም ሆነ በጭብጡ ከ "ጉሮ" እና ከ"ሜዳ የቀረሽው" የሚሻል፣ ኪናዊ ብቃት ያለው ግጥም ነው ብዬ እንደማስብ መግለፅ እፈልጋለሁ። ያሲን ዑመር፣ በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቱ ላይ፣ "የዳኛቸው ወርቁ፥ 'እንቧ በሉ ሰዎች' (1954) በተማረው ወጣት ውጫዊ (ደመ ነፍሳዊ) አኗኗር ማሳያነት፣ ከባዕዳን አገር የቀሰመው ዘመናዊ ስልጣኔ በውስጣዊ ማንነቱ ላይ ያደረሰበት ረቂቅ የማንነት አሻራ እጦት ችግር ወደ ግዙፍነት የተሸጋገረበት የኪነጥበብ ውጤት ነው" (1998፥ 41) በማለት ማስተንተኑን ልብ ይሏል።

[43] ይህ ጥናት፣ የሀሳብ ታሪክ (history of Ideas) ላይ የሚያተኩር የሥነ ጽሁፋዊ ታሪክ (Literary history) ጥናት ዘር በመሆኑ፣ "እስኪ ተጠየቁ" አይነት ሥራ ተገቢውን ደረጃና አክብሮት እንዲያገኝ ለማመላከት የሞከርኩት እነ Wellek፣ Theory of Literature (1984) በሚለው መጽሐፋቸው ላይ የመከሩትን ተቀብዬ ነው።

ሁሉ የሚተገትን ሰዋዊ አጠይቆቶችን የሚያፈሰው በቀዘቀዘ ድባብ፣ በለሆሳስ ድምፀት ነው፡፡ የዮሐንስ ግጥም የሙታን ዓለም ለጥያቄዎቹ (ለፍልስፍናዎቹ) ማሄጃነት በመገልገል፣ በርካታ ማህበራዊና ፖለቲካዊ የሰሉ ሂሦችን አንስቷል፡፡ በርግጥ ሂሶቹ ማህበራዊነታቸው ይጐላል፤ አብዛኞቹ ፖለቲካዊ የሚባሉ ርዕሠ ጉዳዮች ከማህበራዊ ሂሶቹ ጋር እየተሸረቡና እየተዋዙ የቀረቡ ናቸው፤ ጥቂት ማሳያዎችን እየነቀስኩ ላስተንትን፡፡

ሌላ ወገን ደግሞ አለ ወይ ደብተራ ቂሱም መነኮስ፣

በኑሮው በሥራው በስብከቱ ሁሉ የሚግበሰበስ፣

ብዛቱስ እንዴት ነው 'ሚፈላ እንዳንበጣ፣

ልኩ የማይታወቅ ፍፁም ቅጡን ያጣ፡፡

....

ዛሬ ክቡር ሰንበት ነገ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቀጥለው ደግሞ አቦ

አዘክሩ ጠላ አዘክሩ ዳቦ፡፡

....

ብሎ ይሰብካል ወይ ባገር መቃብር

በዚያ ላለው ሁሉ ላስከሬን ፍጡር፡፡ (ገጽ፥ 30)

እነዚህ ስንኞች ቤተክህነትን የሚሞግቱ፣ የደብተራውን፣ የቄሱን ነቢባዊና ገቢራዊ ሕይወት የሚመዝኑ ስር ነቀል ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ለዘመናት በሃገሪቱ ላይ ተንሰራፍቶ የቆየውን የቀሳውስቱን ለሆዱ አደርነት የሚያጠይቁ፣ በሃይማኖት ሽፋን የራሳቸውን ግብስብስ አስተሳሰብና አሠራር የሚያካሂዱ ስለመሆኑ ግጥሙ ይሄሳል፡፡ በየአድባራቱ ሳይሰሩ ቁጭ ብለው መጽሐፍ እየጠቀሱና እያስፈራሩ ዝክር የሚበሉ ተቀማጮች መብዛታቸውን (ልካቸው የማይታወቅ መሆኑን ሁሉ) ይታዘባል፡፡ የዮሐንስ ግጥም፣ አፄ ቴዎድሮስ፣ ካህናቱ በየአድባራቱ ተጠልለው፣ ሰፊ መሬት ይዘው እያከራዩና ምዕመኑን እያዘከሩ መቀመጣቸው ሲያሳስባቸው ለየደብሩ የሚሆን አገልጋዮችን ወስነው በመግለጻቸው ሳቢያ ከቤተክህነት ጋር የከፋ ጥል ውስጥ የገቡበትን አጋጣሚም ያናብባል፡፡

ከ1953ቱ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ጋር በተያያዘ የጠበቀ የሳንሱር አሰራር እንደተጀመረ[44] Molvaer (1996) የገለፁት የመፃፍ ነፃነት እጦት ጉዳይ በቀዳሚነት በዮሐንስ "እስኪ ተጠየቁ" በይፋ ተተችቷል።

ስነ ጽሑፋችሁ በልጽጓል ደርጅቶ፣

ወይንስ ኮስምኗል በሳንሱር መቃብር ወዙ ተበላሽቶ።

ምን አይነት ጽሑፍ ነው የምታሳትሙ፣

በከንቱ ውዳሴ በርካሹ ወግ የተያዘ ትልሙ (ገጽ፥ 38)

ከተጠቀሱት ስንኞች በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው፣ ዮሐንስ በዘመኑ የነበረውን ሀሳብ የመግለፅ ነፃነት እጦት በይፋ ሞግተዋል። የሚታተሙ ፅሁፎች እንኳ ቢኖሩ "በከንቱ ውዳሴ" የረከሱ፣ አድር ባይ ጸሐፊ የጻፋቸው እንደሚሆኑ በስላት ጠቁመዋል፤ የምልከታው ወይም የጥቆማው ገላጭነት ፍንትው ብሎ የሚታየን፣ በወቅቱ የሚታተሙ መጻሕፍት፣ "... ባሪያዎ ከዙፋንዎ ሥር ቆሜ ሞገስ ያገኘልኝ ዘንድ ይህንን መጽሐፍ በታላቅ ትሕትና ለግርማዊነትዎ አበረክታለሁ" (ዝክረ፡ ነገር። 1962፣ ገጽ 1) አይነት የይለፍ ቃል የሚመስል ውዳሴ ይዘው ከሚታዩበት ሀቅ ጋር ስናናብበው ነው።

ዮሐንስ ሲሞግቱት የነበረው ፊውዳላዊ ሥርዓት ቅንቅን እንደበላው ግንድ አንድ ቀን ሊገረሰስ እንደሚችል እንደብሉየ ሞክሻቸው መጥምቁ ዮሐንስ በትንቢት ስለማስጠንቀቃቸው፣

ይዘልቃል ወይ ከቶ በንዲህ አይነት ስልት፣

ወጋግራውን ሁሉ ምሰሶውን ሁሉ ቁንቁን ጨርሶት። (ገጽ፥ 42)

የሚሉት ሸንቋጭ ስንኞቹ ዋቢ ይሆናሉ።

ዮሐንስ፣ መንግስታዊ ስርዓቱን እና አቋመ ማህበሩን ብቻ የሚያወግዙ ጭፍን ብዕረኛ አልነበሩም፤ እራሳቸውንና እሳቸውን መሰል የጊዜውን ምሁራን ጭምር ማህበራዊ እውነቶች የወለዷቸውን መሪር ጥያቄዎች ጠይቀዋል፤

ዐዋቂውስ ሁሉ (ምናልባት እንዳለ) እንዴት ይኖራል፣

ፈርቶ መካን ሁኗል ወይስ ያፈራል (ገጽ፥ 32)።

[44] የካቲት 7 ቀን 1927 ዓ.ም. ስለ ጋዜጦችና መጽሔቶች ማሳተም በተቋቋመ ህግ "ጨዋታ መርማሪ" በሚል ስም ስለ ሳንሱር አዋጅ እንደወጣ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ዝክረ፡ ነገር (1942፥ 700) በሚለው መጽሐፋቸው ገልፀዋል።

እነዚህ ስንኞች የግጥሙ ተናጋሪ፣ "አዋቂ" የሚባለው ክፍል የተማሩ፣ የሰለጠኑ፣ ያወቁ ዜጎችን እያፈራ ነው ወይ? ወይስ አእምሮው በፍርሃት ቆፈን ተቀፍድዶ መክኗል? የሚል ጥያቄውን ከማንሳቱ በፊት፣ እንደውም ከነጭራሹ "አዋቂ" የሚባል አለ ወይ? የሚል የገዘፈ ጥያቄ አቅርቧል። የአዋቂዎችን መኖር ተጠራጥሯል፤ የግጥሙ ጭብጣዊ ጥልቀት ይህን የዘመን መንፈስ የሚጠቁም ከሚመስለው ከተማረው ወጣት የጥርጣሬ በሽታ (Skepticism) ሊመዘን ይችላል።

"እስኪ ተጠየቁ" በርካታ ርዕሠ ጉዳዮችን አስሮ ይዟል። ስለዛ ዘመን ታሪክ ለሚያጠና ሰው ጥሩ የሀሳብ ሰነድ መሆን የሚችል አቅም ስላለው፣ ወደፊት ከሌሎች ግጥሞች ጋር ሁሉ እየተናበበ ይተነትናል። የዘመን አቻዎቹ፣ "ኑሮ" እና "ሜዳ የቀረኸው" በአንድም ሆነ በሌላ በኩል ያናብቡታል፣ ወደ እነሱ እንዝለቅ።

"ኑሮ" ይልማ ከበደ

የይልማ "ኑሮ" ከመነሻው ፍልስፍናዊ ጭብጥ ያለው ይመስላል። የዓለማችን ታላላቅ ሊቃውንት ምድር አልበቃቸው ብሎ ህዋውን ሲያስሱ የ"ኑሮ"ን ምንነት ግን ማወቅ እንደተሳናቸው ቀድሞ ይሞግታል። ኑሮ ገበናዋን በውስጧ ይዛ እራሷን በደበቀች በድፍን ሾላ ተመሥላ ቀርባለች። ተመራማሪውም የኑሮን ድፍንነት ሳይሰለች ሲያሰላስል የድፍኑን ቂስ መክፈቻ ቁልፍ ማግኘቱን እና በሐሳብ መነጽር አትኩሮ ማየቱን ያስረዳል። ኑሮ ግን ከተመራማሪው እውቀት በላይ እንደሆነችና ውስጠቷን በመደባዊ ልዩነት አጉልብታ እንደታየች ይጠቁማል። በመጨረሻም ኑሮ በውስጧ፤ "አንዱ የጌታ የዳበረ ኑሮ ሌላው የድህነት የመኖር እሮሮ" እንዳለባት በመጠቆም በማህበረ-ኢኮኖሚ ልዩነት ሳቢያ የተፈጠረውን የመደብ ልዩነት አጉልቶ ያሳያል። በደሀና በሀብታም ኑሮ መካከል ያለው መደባዊ ክፍፍል፣ የተለያዩ የኑሮ ደረጃ ማሳያዎችን በመጠቀም የሚያወሳ ግጥም ነው። በ"እስኪ ተጠየቁ" ላይ ለተወተወተው የዝቅተኛው ህብረተሰብ ክፍል የኑሮ ጉዳይ ማሳያም ነው። የተወሰኑ ስንኞችን እንጥቀስ።

> ከመላው ዓለም ሕዝብ ሲሶ ለሚሆኑት፣
> በኃብት ጥላ ስር የተሰበሰቡት፣
> ግንደ ቆርቁር ሆነው ቦርቡረው ጨረሱት።
> በዓለም ያለው ሕዝብ እንደታወቀው፣
> ከሀብታሙ ይልቅ ብዙው ደሃ ነው። (ገጽ፥ 49)

እነዚህ ስንኞች የገጣሚውን ዓለማቀፍ ምልከታ ያነፅራሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ በደሃና በሀብታም መካከል ያለውን የሀብት ልዩነት ተጨባጭ በሚመስል ሂሳብ ("ሲሶ ወይም አንድ ሦስተኛ የሚለውን ልብ ይባል) በማስረዳት፣ የህዝብ ሀብት በጥቂቶች እጅ እንዳለ የሚጠቁም በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና የተቃኘ ግጥም ይመስላል። ማህበራዊ ማንፀሪያዎቹ የጐሉ ቢሆንም፣ ሃገር በቀሉ የፊውዳል ስርዓት ጥቂት የመሬት ከበርቴዎች ብዙሃኑን ጭሰኛ ያደረጉበትን በለሆሳስ የሚሞግት ፖለቲካዊም ግጥም ነው። ከታምሩ ፈይሳ "ደሀው ይናገራል" ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል፣ ከዮሐንስ[45] "እስኪ ተጠየቁ" ጋር በሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለማዊነቱ የሚናበብ፣ መንግስታዊ ስርዓቱ የቆመበትን መሠረት በስሱም ቢሆን ለመነቅነቅ የሚሞክር የተቃውሞ ግጥም ነው።

"ሜዳ የቀረሽው" መላኩ ተገኝ

የመላኩ "ሜዳ የቀረሽው" ያልተወራረደውን የ1953 የመፈንቅለ መንግስት መሪ እውነት የሚያወሳ ይመስላል። ከዮሐንስ "የገደል ስር አጥንት" ጋር ሲናበብ የሚችል፣ አንድ የተዘረረን አስከሬን የሚጠይቅ፣ ሙሾ አውራጅ ግጥም ነው።

የሚጠየቀው አስከሬን የወታደር መሆኑ ሲነገረን ደግሞ፣ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ አድራጊ ወታደሮችን ለመዘከር የተገጠመ ይሆን? ብለን እንጠረጥራለን። ጥርጣሬያችንን እንድንገፋበት የሚያደርጉ ስንኞችን ከግጥሙ እየቀነጨብን እናስተንትን።

> ስማኝ ልጠይቅህ
> እዚህ ከተዘረርክ ስንት ነው ዘመኑ
> ማንስ ትሰኝ ነበር ወቴ መኮንኑ
> ....
> ለዚህ ያደረሰህ ምንድን ነው ነገሩ።
> ጉጉት ተአብዮ ክብር ይሆን ሳገሩ።
> እስቲ ያነሳሳህ ምን ነበር ንገረኝ
> እንዴትስ ፈፀምከው ሳትደብቅ አጫውተኝ። (ገጽ፥ 51)

[45] ሰለሞን ደሬሳ፣ መስከረም 1991 በታተመ <u>ሪፖርተር</u> (ቅጽ 2፥ ቁጥር 13) መጽሔት ላይ፣ "ዮሐንስ አድማሱ በኔ ግምት የራሱ የከረረ አቋም ስለነበረው እፈራለት ነበር። እሱ ወደ ሶሻሊዝም ድሮውንም ዝንባሌ ነበረው፤ እነ ኃይሌ ፊዳ፣ እነ መንግስቱ ኃ/ማርያም ገና ስማቸው ሳይሰማ። ግን የሁሉም ሰው ሶሻሊዝም አንድ አይደለም። እንደ ዮሐንስ ያለ ሰው ማርክስን ወይም ኤንግልስን አንብቦ እራሱ ውሳኔ ላይ የሚደርስ ሰው ነው ብዬ ነው የምገምተው።" (ገጽ፥ 24) የሚል ምስክርነት ሰጥተዋል።

እነዚህን ስንኞች ስንመረምር፣ ግጥሙ ከመነሻው ምንም አይነት የታሪክ ዳራ ሳይጠቁመን፣ ወደ ኋላ ሳይም ምንም ፍንጭ ባልተሰጠበት ሁኔታ፣ በቀጥታ "ለዚህ ያደረሰህ ምንድነው ነገሩ" ይላል። ለምን ያደረሰው? ብለን ብንጠይቅ፣ ድንገት ሞቶ ስለመዘረሩ ለመጠቆም ነው ሊባል ይችላል። ዝቅ ብሎ ግን ምን እንዳነሳሳው? እንዴት እንደፈፀመው የግጥሙ ተናጋሪ አስከሬኑን ይጠይቃል። እዚህ ላይ፣ ገጣሚው በግልፅ ለመፃፍ ባይፈቅድም ወይም ባይችልም፣ ለአገር ክብር ሲባል የተፈፀመ አንድ ገድል እንዳለ ግን በውስጠ ወይራ ዘይቤው ይጠቁማል። ሞቱም ከዚሁ "ለአገር ክብር" በተፈፀመ ሁነት እንደሆነ ከሚነግሩን ስንኞች ጋር እያናበብን፣ በዚያው ሰሞኑ ከተፈፀሙ የታሪክ እውነቶች ጋር በትይዩ እያነፀርን ስንመረምር፣ በርግጥም፣ የታህሳሱን ግርግርና የሞቱ ወታደሮችን የሚዘክር ግጥም እንደሆነ እንረዳለን። የተመለከተውን የጭብጥ አቅጣጫ ፅኑነት ለማንፀር፣ የዩኒቨርሲቲውን ሁኔታ እና የገጣሚያኑን ዳራ የሚያስቃኘውን ክፍል (ምዕራፍ ሦስትን) ማንበብ ይጠቅም ይመስለኛል። በዚህ ክፍል ያየናቸውን ግጥሞች ከ1955 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ጋር እያነበቡ መተንተን አልተቻለም። ስለዚህ፣ ወደ ሚቀጥለው ዓመት አሸናፊ ግጥሞች ትንተና እንዝለቅ። "ሜዳ የቀረሽው"፣ በተለይ ከአበበ ወርቄ "ሙት ወቃሽህ መጣሁ" ጋር የበለጠ መናበቡን ማየት ይቻላል።

4.4 የ1956 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና

የዚህ ዓመት አሸናፊ ግጥሞች፣ የሙታንን በድን የሚያናግሩ፣ የገጣሚያኑን ተስፋ ቆራጭነት የሚያጋልጡ፣ በስከነ ድባብ ውስጥ የተዋቀሩ የሚመስሉ፣ የቀዘቀዘ ድምፀት የሚጐላባቸው ግጥሞች ናቸው። እነዚህ ግጥሞች፣ የመጀመሪያው የአበበ ወርቄ "ሙት ወቃሽህ መጣሁ" ሁለተኛው የዮናስ አድማሱ "ምህፃረ ኑሮ"፣ ሦስተኛው ደግሞ የወንድ ወሰን ገ/ኢየሱስ "አንተ ያንቀላፋኸው" ሲሆኑ፣ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ገጣሚያን ጥያቄያዊ አቀራረብን ለሃሳብ ማሄጃነት እንደስልት መጠቀማቸው፣ ከስነምግባር ጭብጥ አንፃር እውነት የሚናገር ትውልድ በመፈለጋቸው፣ ከሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መካከል በመናገር ነፃነትና በእኩልነት ላይ የበለጠ በማተኮራቸው ይመሳሰላሉ። የኑሮ መራራ ክንፍ ላይ ብዕራቸውን ቸክለው በማቀንቀናቸውም ይዛመዳሉ። የተወሰኑ ማመሳከሪያ ስንኞችን እየነቀስን እናስተንትናቸው።

"ሙት ወቃሽህ መጣሁ" አበበ ወርቄ

ይህ ግጥም፣ የገጣሚው ጥልቅ የሆነ ማህበራዊ ሂስ የታየበት፣ ከማህበራዊው የኑሮ አረንቋ ውስጥ ያለውን ዝቃጭ ሕይወት መነሾ ወይም ምክንያት በስልት እየጠየቀ፣ ጥያቄው እራሱ በትይዩ መልሱን እንዲያነፅር የተደረገበት ጥበብ ነው። የአበበ ግጥም አንድ ያንቀላፋን የድሃ አፅም ይሞግታል፤ "ተነስ እንዋቀስ/ ከእንቅልፍህ ተቀስቀስ፣" በሚል አዝማች እያነቃ። የግጥሙ ተናጋሪ፣ አስከሬኑን ከመነሻው ለምን ተፈጠርክ? ስትሞት ማን ተከተለህ? እንዴትስ ብለህ ኖርክ? የሚሉ ጥያቄዎችን ያነሳል። ለምን አገባህ? ደግሞስ ለምን ወለድክ፣ "ሰው ሳትሆን ለምን ሰው ፈጠርክ" የሚሉ ጥልቅ መራር ጥያቄዎችም ያክላል።

የአበበ ግጥም፣ አስከሬኑን በሌሎች ጥያቄዎች እያዋዛ መሠረታዊ ሙግቶችን ያቀርብለታል። ግጥሙ፣ ከጥያቄው ጋር ተሻርቦ ፖለቲካዊ አንድምታው አየል የሚል፣ እና የመሪነት ሚና የሚያጠይቅ ("አስጋጋሪ"ን ልብ ይሏል) ምላሽ፣ "በራብ ነወይ የሞትህ አጥተህ ፍርፋሪ፣ /እረ እንጀራ ሞልቷል ጠፋ እንጅ አስጋጋሪ፣/ አብልቶ እሚበላ አሠርቶ ሠሪ፣" በማለት አቅርቧል።

"ሙት ወቃሽህ መጣሁ" የተለያዩ የማህበራዊ ህይወት ማንፀሪያዎችን ተጠቅሞ የሞገተው የደሃ አስከሬንን ብቻ አይደለም፤ የሀብታም ሙት ገላንም፣ በስጋዊ ወመንፈሳዊ ጥያቄዎች ያካልበዋል። ግጥሙ መደባዊ ልዩነትን ወይም ማህበራዊ ደረጃን በሰው ልጅ ሙት ገላ ማንፀሪያነት አጉልቶ አቀንቅኗል። ይህ የሀብታም አስከሬን የላይኛውን መደብ፣ የባላባታዊ ሥርዓቱን አስፈፃሚዎች የሚወክል ተምሳሌታዊ ሚናም አለው። የግጥሙ ተናጋሪ፣ ለዚህ የሃብታም ሙት ገላ ያቀረበውን መደባዊ ጥያቄ መመርመር ይቻላል፤

መንገድ ተሠርቷል ወይ ካንተም ተቀንሶ፣
ንጉሥ ባዘዘው ቃል አዋጅ ተንተርሶ፣
....
ቀንስ ብሎ ሄደ ከኪሥህ ነዋይ፣
ደዌ መፈወሻ ሀኪም ቤት ሠርቷል ወይ፣ (ገጽ፥ 73)

እነዚህ ስንኞች ሀብታሙ ሰው ከመሞቱ በፊት የነበረውን ገንዘብ ዛሬ ከሞተ በኋላ እንኳ ለህብረተሰቡ የሚያገለግሉ ተቋማት በከፍትበት መልካም እንደሆነ ይጠይቃሉ። በመጨረሻም፣ የግጥሙ ተናጋሪ የሰው ልጆችን ሁሉ እያስጠነቀቀ የሚሰብክ ሁለንተናዊ

ጭብጥ ያነሳል። የግጥሙ የመጨረሻ ስንኞችም በዓለም ላይ የምንግዴ አይነት የሚኖሩ ሰዎችን፣

የሞተውን አይተህ ያለህ ሰው ተጠንቀቅ
ቀን ማለፉ አይቀርም፣ ምላሽ እንዳይጠፋ
ታሪክህ በታሪክ በጊዜው ሲጠየቅ።
ዓለም እንዲሁ እንደሁ የሚመለከትህ
ሙት ካለህ ተጠንቀቅ በኖረ ሰው ኑረህ
ዕውቀት ባንተ ሲነግሥ ኋላ እንዳይጸጽትህ። (ገጽ፥ 77)

በማለት፣ በሰው ትከሻ ላይ የሚኖሩ፣ በሰው እውቀት የሚያጭበረብሩ "በኖረ ሰው" ኗሪዎችን፣ ሞት አይቀርምና በድናችሁ ቢጠየቅ ማጠፊያው እንዳያጥራችሁ የሚል ጥቅል ሀሳብ ያቀነቅናል። ይህ ግጥም፣ ከዮሐንስ "የገደል ስር አጥንት" ጋር በብዙ መልኩ ሊናበብ እንደሚችል ልብ ይሏል።

"ምሕፃረ ኑሮ" ዮናስ አድማሱ

የዮናስ አድማሱ፣ "ምህፃረ ኑሮ" በጊዜው የነበረውን ልጆች እንዳይናገሩ የሚቀይደውን (constraint) ባህላዊ ሥርዓት በግልፅ የሚተች ግጥም ነው። ጠንከር ያለ ሙግት ካነሳባቸው ማህበራዊ ተቋማት አንፃር፣ ከታምሩ "ደሀው ይናገራል" እና ከይልማ "ኑሮ" ጋር በእጅጉ ይናበባል። ግጥሙ በዋናነት፣ እራሳቸውን "የእግዜር ጠበቃ" ያደረጉና የወጣቱን የመናገር ነፃነት ያቀቡ ሽማግሌዎች ላይ አትኩሯል። የሽማግሌዎችና የወጣቶች አለመስማማትን ማሄጃ አድርጎ ጠንከር ያለ የእኩልነት ጥያቄ ያነሣል። ግጥሙ በየመካከሉ ለዘብ ያሉ፣ ተስፋ አስቆራጭ አስተሳሰቦችን የሚያቀነቅኑ ስንኞች የታጨቁበት፣ ስነ ጽሁፍ እንደ ባህል ሞጋች (Literature as subverter of culture) ሆኖ የቀረበበት ግጥም ነው። ስንኞችን እየመዘዝን እናስተንትን።

ጥ. ለምንት አንገለጉ እሕዛብ ወሕዝብኒ ነበቡ ከንቶ፣
መ. መቼ በከንቱ ነው ልባቸው ተነክቶ።
ኑሮ፣ኑሮ፣ኑሮ ከንቱ ኑሮ፣
ኑሮ ምን ሠራልኝ ከቶ ከኔ አብሮ (ገጽ 87)

ከመጀመሪያዎቹ ስንኞች ፊት ላይ ሁለት ምሕፃረ ቃላት አሉ። የመጀመሪያው፣ "ጥያቄ" የሚል ቃል የወከለው "ጥ" ሲሆን፣ በ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በአማርኛ ትርጉም፣

"አሕዛብ ለምን ያጉረመርማሉ? ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ?" (መዝ.፣ 2፥ 1) የሚለውን የግዕዝ ጥቅስ በቁሙ ይጠይቃል። ወዲያው በ"መ" በተወከለው ምህፃረ ቃል ("መልስ") አማካይነት፣ አህዛብ በከንቱ አይደለም ያጉረመረሙት፤ ይልቅ፣ "ልባቸው ተነክቶ" ነው የሚል ምላሽ ይሰጣል - የግጥሙ ተናጋሪ። ምህፃረ ቃላቱ፣ (ጥ እና መ) እንዲያጥር፣ በአጭር እንዲቀጭ የተፈለገውን ኑሮን፣ የግጥሙ ዋና ማጠንጠኛ "ምሕፃረ ኑሮ"ን በትይዩ የሚያናብቡ ገቢራዊ ትዕምርቶች ናቸው ማለት ይቻላል። "ኑሮ፣ ኑሮ..." የሚሉትም ስንኞች፣ ግጥሙን ከመነሻው ቀዝቃዛ ድምፀት የረበበበት መሆኑ ከመጠቆማቸው ባለፈ፣ የግጥሙን ተናጋሪ የታከተ ኑሮ፣ የጠቆረ ተስፋ የሚጠቁሙ ይመስላሉ። የሚከተሉት ስንኞች ደግሞ የግጥሙን ማዕከላዊ ጭብጥ ያስተነትናሉ።

> ዐይን ሲያይ እያየሁ ጆሮም ሲያዳምጥ
> ምንም ሳላወራ እንዴት ልቀመጥ፣ (ገጽ፥ 92)
>
> ....
>
> ግብሬ መናገር ነው እለፈልፋለሁ፣
> ውሸት ውሸት ትቼ እውነት አወራለሁ፣ (ገጽ፥ 93)
>
> ....
>
> ልሙትና ልረፍ ሞታችሁ ዕረፋ እንደሰው ተፈጥሮ
> ይኸው ነው ባጭሩ ለምሕፃረ ኑሮ፣ (ገጽ፥ 94)

ስንኞቹ ዐይን ብዙ ጉድ እያየ፣ ጆሮም ብዙ ጉድ እየሰማ አፍ ምንም እንዳይተነፍስ መደረጉ የሚፈጥረውን ሰብአዊ ጥያቄ ያጐላሉ፤ ጥያቄው፣ ከማህበራዊ ተቋማት የዘለሉ፣ (ከሃገረሰባዊ የ"ልጅ አይናገርም" ብያኔ ያፈነገጡ) ፖለቲካዊ አንድምታ ሁሉ እንዳላቸው የምንጠረጥረው "ውሸት ውሸት ትቼ እውነት አወራለሁ" የሚለውን ስንኝ አጥብቀን ስንመረምር ነው። ስንኙ፣ አንድም የግጥሙ ተናጋሪ ባለበት አካባቢ ውሸት ተናጋሪዎች ያሉ መሆኑን፤ አንድም፣ ጥያቄው ዝም ብሎ የመናገር መብት ጥያቄ ሳይሆን ያዩትንና የታዘቡትን፣ (እውነቱን) መናገር መፈለጉን መሆኑን የሚያጐሉ ይመስላሉ። መናገር (ያውም እውነትን መናገር) ካልተቻለም፣ የኑሮ ጊዜን አሳጥሮ ("ምሕፃረ ኑሮ" እንዲሉ) ሞቶ ማረፍ የሰው ተፈጥሮ የሚፈቅደው ሰዋዊ እውነት እንደሆነ ያስረዳል። የዮናስ "ምሕፃረ ኑሮ"፣ ወደፊት ከሌሎች ሥራዎች ጋር እየተናበበ ይጠቅሳል።

4.5 የ1958[46] ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና

በዚህ ክፍል፣ በ1958 ዓ.ም. ተወዳድረው ያሸነፉና በኮሌጅ ቀን በዓል ላይ የቀረቡ ግጥሞች ተተንትነዋል። ግጥሞቹ የመጀመሪያው የመሐመድ ኢድሪስ "ከምሽቱ እስከ ጎሕ"፣ ሁለተኛው የአበበ ወርቄ "ምላሴን ተዉልኝ"፣ ሦስተኛው የኢብሳ ጉተማ "ኢትዮጵያዊው ማን ነው?" ሲሆኑ፣ ግጥሞቹ፣ በቅርጽም ሆነ በይዘት ከተመሳስሏቸው (similarity) ይልቅ ልዩነታቸው (difference) አየል የሚልባቸው ይመስላሉ።

አሸናፊ ግጥሞቹ፣ በመንግስታዊ ስርዓቱ ላይ በፈጠሩት ፖለቲካዊ አንድምታቸው (በተለይ ስለመናገር መብት ማቀንቀናቸው)፣ የትውልዳቸውን (የተማሪዎችን) ጥራዝ ነጠቅነት በማጋለጣቸው፣ በተስፋ ቆራጭነታቸው ተመሳስሎ ይታይባቸዋል። ግጥሞቹ፣ ያነሷቸውን ዋና ዋና ርዕሠ ጉዳዮች እና ያተኮሩባቸውን ዋና ዋና ማዕከላዊ ጭብጦች በማስረጃዎች ተደግፈው እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

"ከምሽት እስከ ጎሕ" መሐመድ ኢድሪስ

የመሐመድ ግጥም፣ ለቅስቀሳ (agitation) ወይም ለፕሮፓጋንዳ ተግባር ታልሞ የቀረበ፣ ፖለቲካዊ ትችት የጐላበት ጥበባዊ ሥራ ነው ማለት ይቻላል። ገና ከመነሻው፣ "ገነኛ ምላስ ጫዋታ ጀምሪ" በማለት የግጥሙ ተናጋሪ፣ አስተዋይ አእምሮ ላለው ተማሪ ምላሱ ሀሳቡን እንድታደርስለት ሰከን ያለ ትዕዛዝ በማስተላለፍ ይጀምራል፤ "ይድረስ ለግብ ብለሽ ላስተዋይ አእምሮ /አነጣጥረሽ ለጊ ለህሊና ጆሮ" የሚሉ ስንኞችን በማስቀደም። መንግስታዊ ስርዓቱን በ"ተባይ"፣ የአገዛዝ ዘመኑን ደግሞ በ"ለሊት መርዘም" ወክሎና የተለያዩ ታሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጠቆምቶችን (Allusions) ማንፀሪያ አድርጎ፣ ከ"ዛር"ጋር ያመሳሰለውን የአፄውን ስርዓት ይወቅሳል፤ ስርዓቱ እንዲለወጥ የተለያዩ ነገረ ሀሳቦች በማቀንቀን ይቀሰቅሳል። ግጥሙ፣ ነፃነት ፍለጋን፣ በጭሰኛውና በከበርቴው ማጉሊያነት የመደብ ልዩነትን፣ "ምሁር የተባለው … ፈላስማ" ገጠር ሄዶ ለማገልገል ፈቃደኛ አለመሆኑን እና በብዙ መልኩ ጥራዝ ነጣቂ መሆኑን ይጠይቃል፤ ይተቻል። ማሳያዎችን እያጣቀስን እናስተንትን።

[46] የሚተነተኑ የ1957 ዓ.ም የኮሌጅ ቀን ግጥሞችን ማግኘት ቀርቶ፣ ከነጭራሹ የኮሌጅ ቀን በዓል ስለመከበሩ መረጃ አላገኘሁም፤ ዝርዝሩን በምዕራፍ 3፣ የ1957 ዓ.ም. ክስተቶች የተጠናቀሩበትን ክፍል ይመልከቱ።

የንጉሱን የአገዛዝ ዘመን "በሌሊት መርዘም" ተምሳሌት የወከለው የግጥሙ ተናጋሪ፣ ከማህበራዊ ተቋማቱ መካከል "አይደፈሬ" በሚመስለው "ተማልሉአዊነት"[47] (Mysticism) ላይ አልሞ፤

ታዲያ ለምን ይሆን ሌሊቱ መርዘሙ

እግዜር ታሞ እንደሆን በወዳጁ ስቅለት ባፈሰሰው ደሙ። (ገጽ፥ 115)

በማለት በማህበራዊ አውድ ውስጥ የእምነት ታላቅ ትዕምርት በሆነው በ"እግዚአብሔር ልዕለ ኃያልነት" ላይ ጥርጣሬ (skepticism) ሁሉ እንዳደረበት ይገልፃል። በህብረተሰቡ የእምነት ተቋም ላይ እየተሳለቀ፣ "የሌሊቱን እርዝማኔ" ያሳጥሩልኛል ያላቸውን ሌሎች አማራጮች ይሞክራል። የግጥሙ ተናጋሪ "አይደፈሬ" የሚመስለውን የእምነት ተቋም፣ በማርክሳዊ ሌኒናዊ የቁስ አካላዊያን ፍልስፍና ሊተካ መፈለጉን በሚከተሉት፣ በስመ ሃዳሪ ዘይቤ በተዋቀሩ ስንኞች ይገልጣል፤

መስኮብ ልጠይቅሽ የኮሚኒስት ዓለም

ጨረቃን የሚወድ ከቶ እንዳንች የለም፣

እንደምን ተሻገርሽ የዛርን ጨለማ?

በጠበልሽ ነው ወይ በጸሎት አውድማ፣

መደሻና ማጭድ ደሙ ላይ የተኛው እንደምን ይሠራል?

....

እንዴት አርጎ ገባ ፈረንጅ አገር ዛር

ያንጉል ሲቃውንቶች ባበሻ አገር

ብቻ ነው እያሉ ሲያወሩ ነበር? (ገጽ፥ 116)

ስንኞቹ፣ በዓለማችን ጨረቃ ላይ ለማረፍ ቀዳሚ የሆነችውን ራሻን ("ሞስኮብ"ን) ይጠይቃሉ። ራሻ ወይም ሶቬት ህብረት የማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም አራማጅ ኮሚኒስት አገር መሆኗንም ያስታውሳሉ። የግጥሙ ተናጋሪ "ዛር" የሚለውን ቃል በሁለት በኩል የተሳለ ሰይፍ አድርጎ ተገልግሎበታል፤ ቃሉ በአውዱ ውስጥ ለሁለት ትላልቅ ፍቾች መቆሙን ለማስተንተን ታሪካዊ ጠቆምት መሆኑን ማወቅ ይገባል። በአንፃራዊነት በፊት ለፊት የቀረበው "ዛር"፣ ውቃቢ ወይም በሚያስጓራ ክፉ መንፈስ በሚወክለው ሃገርኛ ፍቺ

---

[47] የማርክሳዊ ሌኒናዊ መዝገበ ቃላት፣ "ተማልሉአዊነት [Mysticism] በፍልስፍና አግባቡ ሃይማኖታዊና ሀሳባዊ የሆነ ንጽረተ ዓለምና አስተሳሰብ ነው ... የዚህ አስተሳሰብ ዓይነተኛ ባህርይ ጸሎት በሚደረግበትና መስዋዕት በሚቀርብበት ወቅት ሰው ከእግዚአብሔር ወይም ከአንድ ከሁሉም በላይ ከሆነ ኃይል ጋር ሊገናኝ ይችላል የሚል ሐሳብ ነው" (ገጽ 222) በማለት ገልጾታል።

ነው። የግጥሙ ተናጋሪ፣ በአገር ውስጥ የሚታወቀው ክፉ መንፈስ በሃበሻ አገር ብቻ እንደሚኖር የሃበሻ "ሊቃውንት" ተናግረው ሳለ፣ እንዴት በፈረንጅ አገር ሊኖር ቻለ? በማለት የሚጠይቀውን ልብ ይሏል።

ስንኞቹ፣ የሃበሻ ክፉ መንፈስ ተደርጎ የሚቆጠረው "ዛር"፣ ሞስኮን ጨለማ እንዳደረጋትና ይህን የጨለማ ዘመን የተሻገረችው "በፀበሏ" ወይም "በፀሎቷ" እንደሆነ ጠቆም አድርጎ ያልፋል። በዚህ የትንታኔ አቅጣጫም ጐልቶ የሚታየው ማህበራዊ ሂሱ ነው፤ ይኼ ደግሞ ሰሙ ነው ማለት ይቻላል። የግጥሙ ማዕከላዊ ጭብጥ የተገለፀበት ወርቁ ግን ለዘመናት የገነነ ፖለቲካዊ አንድምታ አለው። የግጥሙ ጥበባዊ ብቃትም፣ ከዚህ ከገነነ ሃገረሰባዊ የክፉ መንፈስ (ዛር) ጋር ተሸርቦ፣ ሆን ተብሎ በብልሃት ከተገለፀው ፖለቲካዊ ጭብጡ ውስጥ ይመዘዛል።

አሁን በማህበረሰባዊ ሂሱ ማሄጃነት ተሸርቦ ወደ ቀረበው የግጥሙ ፖለቲካዊ ጭብጥ ወደ ማስተንተን እና ሁለተኛውን የ"ዛር"ን ትርጓሜ ወደ መመርመር እናምራ። እዚህ ላይ "ዛር" በታሪካዊ ጠቆምትነት (historical Allusion) መግባቱን ማስተዋል ያስፈልጋል። "ዛር"፣ የራሻን ባላባታዊ የፊውዳል ስርዓት የሚወክል፣ ከተፀውኦ ስም ጋር እየተነገረ ንጉሳዊ ማዕረግ የሚገልፅ ቃል ነው፤ በኢትዮጵያ "አፄ"፣ በግብፅ "ፈርኦን" እንዲሉ። የግጥሙ ተናጋሪ ራሻን (ሞስኮን) የጠየቀው በድንገት አይደለም፤ የግጥሙ ተናጋሪ የአፄው ስርዓት የፈጠረውን የጨለማ ዘመን፣ ከራሻው የዛሩ ስርዓት ጋር ሆን ብሎ በትይዩ ማናበቡን መረዳት ያስፈልጋል።

የሃገር ውስጡ ባላባታዊ ስርዓት ያሰፈነው የጨለማ ዘመን በብልሃት ለማለፍ በተመሣሣይ አፄያዊ አገዛዝ ውስጥ የነበረችውን ሩሲያን እንዴት እንዳለፈችው ይጠይቃል፤ "በጠበልሽ ነው ወይ በፀሎት አውድማ" የሚል ሃይማኖታዊ ምላሿን ይጠቁማል፤ የግጥሙ ተናጋሪ ለማለት ያህል ሃይማኖታዊ ምላሽ በአማራጭነት ጠቆመ እንጂ፣ በተማልሉአዊነት (Mysticism) ላይ ጥርጣሬ እንዳለው ("እግዜር ታሞ እንደሆን..." የሚለውን ስንኝ እዚህ ላይም ማናበብ ይቻላል) እንረዳለን። ይኸውም፣ ሞስኮ፣ "የዛር ጨለማ"ን ያለፈችው፣ በሩሲያ ሶሻሊስተ አብዮት መሪነት ባራመደችው "የማርክሳዊ ሌኒናዊ ዲያሌክቲካዊና ታሪካዊ ቁስአካል" ፍልስፍና እንደሆነ (ከሃይማኖታዊ ፀሎቷ በተቃራኒ ማለት ነው) የምንገነዘበው ቀጣዩን፣ "መደሻና ማጭድ ደሙ ላይ የተኛው እንደ ምን ይሰራል?" የሚለውን ስንኝ ስናነብ ነው።

ጉዳዩ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ይመስላል። እናም፣ በቀይ ቀለም መደብ ላይ ብዙ ጊዜ በነጭ ቀለም የሚሳሉት "መዶሻና ማጭድ" የሶሻሊዝም (የማርክሳዊ ሌኒናዊ ዲያሌክቲካዊ ቁስ አካል አስተምህሮ አርማ) ስርዓት የሚወክሉ ዓለም አቀፍ ተምሳሌቶች መሆናቸውን ማጤን ቁልፍ ጉዳይ ነው። የግጥሙ ተናጋሪ፣ መስኮብን፣ "እንደምን ተሻገርሽ የዛርን ጨለማን?" በማለት ከጠየቀ በኋላ፣ "በጠበልሽ ነው ወይ በጸሎት አውድማ፣" የሚለውን ሃይማኖታዊ ምላሽና "መዶሻና ማጭድ ደሙ ላይ የተኛው ..." የሚለውን የሶሻሊዝምን ርዕዮተ ዓለም ትዕምርት እንደ አማራጭ የመፍትሔ ሀሳቦች በተከታታይ ስንኞች አቅርቧል። ይህ አመክንዮዋዊ ቅርፁም፣ በራሱ የሚናገረው ነገር አለ። ይኸውም፣ የገጣሚው ትውልድ ሃይማኖታዊው በተለይ ኦርቶዶክሳዊ ቀኖና፣ ከማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና ጋር ይካለስበት፣ እንዲያ ሲልም ይሳከርበት እንደነበር የሚጠቁም ይመስለኛል። እዚህ ላይ ባህሩ ዘውዴ፣ "... በኦርቶዶክሳዊ ቀኖና ላይ የተዋቀረ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ቀኖና ሲታከልበት [የደርጉ] አገዛዙ ርዕዮተ ዓለማዊ ምልዓት አገኘ። በዚህ ረገድ የሩሲያና የኢትዮጵያ የታሪክ ሂደት የመመሳሰል ባህሪ ነበረው። ሁለቱም አፄያዊ አገዛዝና የኦርቶዶክስ እምነት ስር የሰደዱባቸው አገሮች ነበሩ" (2000፥ 260) ያሉትን ማጣቀስና ማናበብ የግጥሙን ጥልቅ ፖለቲካዊ ጭብጥ ለመመርመር ያግዛል።

የመሀመድ "ከምሽት እስከ ጉሀ"፣ እንደ ርዕሱ የአፄው ስርዓት ካጨለመው ዘመን (ከምሽት) እስከ ጨለማው የሚገለጥበት አብዮታዊ ንጋት (ጉሀ) ድረስ ይተርካል። ግጥሙ፣ ፊት ለፊት ፈጦ ከሚታየው ማህበራዊ ሂሱ ጋር እየተሸረበ የቀረበው ጥልቅ ፖለቲካዊ ፍካሬው፣ አለፍ አለፍ እያለ በሚያቀርባቸው የፕሮፖጋንዳና የቅስቀሳ ስንኞቹ ይጕላምሳል። የሚከተሉትን ስንኞች ይመልከቱ፤

> ያገሬ ተማሪዎች ያገሬ ዲንቢጦች
> ምነው አትዘምሩም ፍዝዝ ብላችኋል አተኩሬ ሳይ
> ፖለቲካ ፍትፍት አነቃችሁ ወይ?
> ትእምርተ መንግስቱ ይውጣ ይውለብለብ
> ነጋ እኮ ለሊቱ ይነጣ ይህ ሕዝብ። (ገጽ፥ 120)

የግጥሙ ተናጋሪ፣ ያገሩን ተማሪዎች ("ዲንቢጦች") ለምን እንደማይዘምሩ ለምን እንደሚፈዙ ይጠይቃል፤ ከመጠየቅም አልፎም ምሽቱ ተገልጧል፤ ንጋቱ ጉሀ ቀዷል እና ህዝቡ መንግስትን የሚወክል ትዕምርት (ባንዲራ ሊሆን ይችላል) እያውለበለበ ይውጣ፣ ለለውጥ ይነሣ እያለም፣ በግልፅ የሚቀሰቅስ ግጥም ነው ማለት ይቻላል።

ስንኞቹን፣ ካጠቃላዩ ከግጥሙ መንፈስና ቀደም ብለን ከተተነተኑት ሌሎች ስንኞችና ግጥሞች ጋር እያናበብን ጠንከር አድርገን ከፈከርናቸው፣ ግጥሙ ከቀረበበት 1958 ዓ.ም. ላይ ቆመን የ1966ቱን አብዮት አይቀሬነት እንድናውቅ የተነገረ የትንቢት ቃል (prophetic speech) ይመስላል፡፡ በፍካሬው እንግፋበትና፤ "ትእምርተ መንግስቱ ይውጣ ይውለብለብ" የሚለውን ስንኝ ስንመረምር፣ መንግስታዊ ስርዓቱን የሚወክል ትዕምርት (symbol) ይዘው ተማሪዎች እንዲያውለበልቡ መቀስቀሳቸውን እናጤናለን፡፡ እዚህ ላይ ታዲያ አንድ አይቀሬ ጥያቄ ይነሳል፤ ተማሪዎች የሚያውለበልቡት መንግስታዊ ትዕምርት (አሁን "ትዕምርት"፣ በ "አርማ" ቢተካ ይሻላል) ለማወቅ፣ ቀደም ሲል የግጥሙ ተናጋሪ የጠየቀውን "የመስኮብ የዛርን ጨለማ" የተሻገረችበትን "የኮሚኒስት ዓለም" እና "መዶሻና ማጭድ" የወከሉበትን የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም ያስተነተኑትን ስንኞች ማገናዘብ ይበቃል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የሶሻሊዝም ስርዓት ዓለም አቀፍ ተምሳሌት የሆነውን "መዶሻና ማጭድ" ያላት አርማ ነበር እንዲያውለበልቡ የተቀሰቀሱት ማለት ይቻላል፡፡

"ምላሴን ተውልኝ" አበበ ወርቁ

የአበበ ግጥም፣ ገና ከርዕሱ በጊዜው የነበረውን ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት እጦት አግዝፎ ይናገራል፡፡ በቅርፁም ሆነ በይዘቱ ከዮናስ "ምሕፃረ ኑሮ" ጋር የበለጠ ይናበባል፡፡ ልዩነታቸው፣ "ምሕፃረ ኑሮ" በማህበራዊ ተቋሙ (ባህላዊ የአትናገሩ ቅየዳ /constraint/) ላይ ያነጣጠረ፣ ማህበራዊነት የጐላበት ሂስ ሲሆን፣ "ምላሴን ተውልኝ" ግን መንግስታዊ ስርዓቱ ላይ የሚያተኩር፣ ፖለቲካዊነቱ የጐላ የተቃውሞ ትችት በመሆኑ ነው፡፡

"ምላሴን ተውልኝ" ላይ ያለው የግጥሙ ተናጋሪ፣ ከመነሻው ሁሉን ለማወቅ የሚጥር ተማሪ እንደሆነ፣ በሆዳቸው የተደለሉና የፈሩ አዋቂዎች አለመናገራቸውን እንደተጠየፈ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል እንደጠየቀና ስለሁሉም ነገር ሲያስብ በሰው ልጅ መወለድ ትርጉም እንዳጣ ይተርካል፡፡ "ከፀጉሬ ጀምሬ እስከ እግር ጥፍሮቼ/ሁሉንም አልፈልግ አንድ ብቻ ትቼ፣" (ገጽ፥ 79) እያለ፣ ምላሱን ብቻ እንዲተዉለት፣ "ሁሉንም ውሰዱት ምንም አይጠቅመኝም/ ግን ምላሴን ተዋት ሰው አልጐዳባትም" (ገጽ፥ 79) በማለት ይማፀናል፡፡ የግጥሙ ተናጋሪ፣ ሁሉንም የአካል ክፍሎቹን እየጠራ (ለምሳሌ፡- ጆሮው ሳያጣራ ወሬ ከመለቃቀሙ በላይ አስቃቂ እሮሮ ከመስማት ስላላመለጠ እንዲቆርጡት፣ አይኑንም ወንጀልን ከሚያይበት ጉልጉለው እንዲያወጡት ወዘተ.) በትይዩ ፖለቲካዊ አንድምታቸው በጐላበት ሁኔታ እንደተወገዱለት

ይተርካል። በጨረሻም፣ የግጥሙ ተናጋሪ፣ "እፎይ አሁንስ ምን ቀረ ምላሰ ብቻዋን ነች/ በሉ ደህና ሁኑ ትሁን እንደሆነች፣" (ገጽ፥ 84) በማለት ይሰናበታል።

ግጥሙ፣ በሁለት ተራኪ የቀረበ፣ ከተወሰኑ አንጓዎች በኋላ በአሊጐራዊ ስልት የተዋቀረና በግጥም ያልተለመደ አይነት የትርካ አንፃር ስልት፣ ያስተዋወቀ ሥራ ነው። የመጀመሪያው ተራኪ ሁሉን አካሉን አጥቶ ሲሰናበት፣ ምላስ የተራኪነት ሚናዋን፣ "ከጸጉሩ ጀምሮ እስከ እግሩ ጥፍሮች/ሁሉን አሰናብቷል እሱም ሆኗል ሟች፣" (ገጽ፥ 84) በማለት ትጀምራለች፤ የመጀመሪያው ተራኪ ሁሉንም አካሉን አጥቶ መሞቱንም ታረዳናለች። ምላስ ስራዋ "ወሬ" እንደሆነ ገልፃ፣ ማንንም ሳትፈራ መናገር እንደምትችል በተለያዩ ማንፀሪያዎች ታሣያለች። የሚከተሉት ስንኞች፣ ዋቢ ይሆኗታል፤

ምላስ ለብቻዬ ምን አደርጋለሁ
ምኔን ምን ሊያደርጉት ማንን እፈራለሁ፣
ለመስቀል አልመች የታለና አንገት
ባለቤቱ ፈርዶ ድሮ ሸኝቶት፣ (ገጽ፥ 85)

እነዚህ ስንኞች፣ ምላስ ማንንም እንደማትፈራ፣ "ድፍረት" እንደምታሣይ ያቀነቅናሉ። በርግጥም ምላስ በድፍረት ትናገራለች። ድፍረቱ ግን ከህልውና ማጣት፣ ከሰብአዊነት መንጠፍ (dehumanization) ተንጦ የወጣ፣ ተፈልጐ ብቻ ሳይሆን ተገዶም የመጣ፣ የተስፋ መቁረጧ የመጨረሻው ደረጃ እንደሆነም በሰው ሰውኛው መለፈፉን ስንረዳ፣ የግጥሙ ምፀታዊ (satirical) ትችት ጐልቶ ይሰማናል። "ቢያፌጡ ቢይጐርጡ በምን እንዳያቸው/ ዓይኔ ድሮ ፈስሶ እያዩት ባይናቸው" (ገጽ፥ 86) እያለች ሁሉንም የተወገደ አካላት ማሣያ አድርጋ ምላስ የምታጋልጠው የሰውነት እጦት፣ የሰዋዊነት ዝቅጠት እና ንቅዘት የገጣሚውንም ምፀተኝነት (satirist መሆን) የምታሣብቅ ይመስለኛል። የገጣሚው ጥልቅ ምልከታም ሆነ የግጥሙ ጭብጥ ጥልቅነትና እረቂቅነት፣ ከኪናዊ ቅርፁ ጋር የሰመረና ከእሱው የተመዘዘ ነው ማለት ይቻላል።

ከአበበ "ምላሴን ተውልኝ" በተለየ የትውልዱን የማንነት ጥያቄ ያንፀባረቀ፣ ፅንፈኛ ተጠራጣሪነትን ያመላከተና የትውልዱን ባይተዋርነት ከዛ ትውልድ ገጣሚያን ከነዮሐንስ አድማሱና ዳኛቸው ወርቁ ጋር ተጋርቶ በራሱ መልክ ያቀነቀነ የኢብሳ ጉተማ "ኢትዮጵያዊው ማን ነው?" የሚለው ግጥም ነው። ከመነሻው፣ "ያገር ፍቅር መንፈስ ያደረበት ሁሉ /ማንነቱን ሳያውቅ በመንቀዋለሉ/ ማነኝ ብሏቸዋል መልሱን ቶሎ በሉ" (ገጽ፥

109) በማለት የትውልዱን (የተማሪውን ቢባል ይሻል ይሆናል) የማንነት ጥያቄ አግዝፎ ያቀርባል፡፡

ኢትዮጵያዊ የሚባለው፣ "ከሆድ ያበጠ ቦርጫም መኮንን ነው/ወይስ ኮሰስ ያለው መናጢ ድሃ ነው" እያለ፣ የኅበረተሰቡን የመደብ ልዩነት የሚያነፅሩ የተለያዩ ማሣያዎችን በመጠቀም በሽሙጥ ይጠይቃል፤ "ጋላው ነው አማራው ትግሬው ነው ጉራጌው/ወላሞው ነው ኮንታው አፏኩ ነው ጉጂው/ጭንቅ ብሎኛል ኢትዮጵያዊ ማን ነው? (ገጽ፥ 110) እያለ የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔሮችን እየጠራ፣ የማንነት ፍለጋው፣ ከጥያቄው አልፎ ሁሉ ጭንቀት እንደፈጠረበት ያወሳል፡፡

የግጥሙ ተናጋሪ፣ የ1957 የተማሪዎችን የመሬት ላራሹ ጥያቄና ከእዚህ ጋር ተያይዞ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ሳይቀር በፖሊሦች ሲደርስባቸው የነበረውን በደል፣ ከአነሣው መሠረታዊ የማንነት ጥያቄ ጋር ሸርቦ በብልሃት ያወሳል፡፡ የሚከተሉትን ስንኞች ተመልከቱ፤

መሬት ላራሹ ሲል ከተማ እየዞረ
ባልቸገረው ነገር ሕዝቡን ያሸበረ
ሕፃን ተማሪ ነው?
ወይስ በቆመጡ ራስ እየሰባበረ
ሕፃን ከጐረምሳ ሳይለይ የኖረ
ፈጥኖ ደራሹ ነው
ድምፃችሁን ልስማ ኢትዮጵያዊው ማን ነው? (ገጽ፥ 110)

የግጥሙ ተናጋሪ፣ መሬት በሌለበት በከተማ እየዞረ የጭሰኛውን ጥያቄ የሚያነሳ፣ ባልቸገረው ጉዳይ (ሰላማዊ ሰልፍ ሁሉ እየወጣ) ህዝብ የሚያምስ "ጥራዝ ነጠቅ ተማሪ" ነው? ወይስ ከሰልፈኛው፣ ከአብዮተኛው መካከል ህፃናቱን ከጐረምሶቹ ሳይመርጥ በቆመጥ የሚሰባብር ቅጥረኛ ወታደሩ ነው ኢትዮጵያዊ የሚባለው? በማለት በአሽሙራዊ ስንኞቹ፣ በሁለት ፅንፎች ላይ የቆሙ የህብረተሰብ አካላት ላይ ይሳለቃል፤ የኢብሳን ግጥም ስንኞች እያንዳንዳቸውን እየመረመርን ከፊከርናቸው ህብረብሔራዊ ስሜት፣ ከጠባብ ብሔርተኝነት እንደተሳከሩባቸው ማስተንተን ይቻላል፡፡ አንዳንዶቹ ርዕሠ ጉዳዮች ከቀጣዩ ዓመት ግጥሞች ጋር በትይዩ ይተነተናሉ፡፡

4.6 የ1959 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና

በዚህ ዓመት አሸንፈው ለመድረክ የቀረቡ ግጥሞች አራት ናቸው፤ የመጀመሪያው የኃይሉ ገብረ ዮሐንስ "በረከተ መርገም"፣ ሁለተኛው የጸገየወይን ገብረ መድሕን "ናስተማስለኪ."፣ ሶስተኛ የዮናስ አድማሱ "እስከ ማዕዜኑ" እና በአራተኛ ደረጃ የቀረበ የመስፍን ሀብተማርያም "ስሞታ" እንደሆኑ በምዕራፍ 3 ተገልጿል። እነዚህ ግጥሞች የጭብኛውን ግፍ በማጋለጥ፣ የቤተክርስቲያንን ሥርዓት በመሄስ፣ የተማሪዎችን ጥራዝ ነጣቂነት በመውቀስ ቢመሳሰሉም፣ በብዙ መልኩ ልዩነታቸው ጉልቶ ይታያል። በማዕከላዊ ጭብጣቸው ሊናበቡ ቢችሉም፣ በአተኮሩበት ርዕሠ ጉዳዮችም ሆነ ርዕሠ ጉዳዮቻቸውን በኪሉባቸው ቅርፃቸው ልዩነት አይሎ ይታያል። አስረጂዎች እያጣቀስን እናስተንትን።

"በረከተ መርገም" ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ

"በረከተ መርገም" ገና ከርዕሱ ጀምሮ ጥያቄ የሚያጭር፣ እርግማን "በረከት" አለው እንዴ? የሚያስብል "አነጋጋሪ" ግጥም ነው። ርዕሱ፣ በሁለት ቃላት ተቃርኖ ውስጥ፣ የሕይወት እውነት የረቀቀበት የአያዎ (Paradox) ዘይቤ ግርፍ ስለሆነ፣ አነጋጋሪነቱ ቅርፁ ከፈቀደለት "አደናጋሪነቱ" የመነጨ ነው ማለት ይቻላል። ግጥሙ፣ "ሰው" እየተባለ በዓለም ላይ እንዲኖር የተፈቀደለት "ትልቅ ፍጡር"፣ "የሆነውን ትቶ ላለመሆን ሲሻ፣ ከንቱ ሲቀናጣ" ሌላ ሆኖ በመቅርቱና የተፈቀደለትን የሕይወት መስመር በማለፉ መረገም እንዳለበት ይገልፃል። የሰው ልጅ የእረግማን በረከት እንዲወርድበት የተደረገው፣ በተለይ በብዙ ድካም እና ህሊናዊ ተሰጥኦ የደረሰባቸውን ከፍተኛ ጥበቦቹና የሳይንስ ግኝቶቹን ሁሉም ሰው በእኩልነት እንዲጠቀምባቸው ባለመደረጉ በዓለም ላይ እስከፊ የኑሮ ገፅታ ለመታየቱ ምክንያት ሆኗል በሚል ነው። ገጣሚውም ይህንኑ ማዕከላዊ ጭብጥ በአፅንኣት ይገልፃል።

ግጥሙ፣ መደባዊ ሥርዓትን የሚጠየፍ የሰው ልጆችን እኩልነት የሚያቀነቅን በብዙ መልኩ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም የተቃኘ፣ የርግማን መዐቱን በስልት አደራጅቶ ባቀረበበት ቅርፁ በተለይም በስንኝ ምጣኔው ከኮሌጅ ቀን ግጥሞች በተወሰነ መልኩም ቢሆን ልዩነት መፍጠር የቻለ ሥራ መሆኑን መመስከር ይገባል፤ በሌላ በኩል፣ "በረከተ መርገም" በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ ሚናው ከልክ በላይ ገዝፎ በገጣሚው በኃይሉ ገብረ ዮሐንስም ሆነ በሌሎች አንዳንድ አፈ ልሂቃን የሚነገርለትን ያህል ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም ለማስረፅ አቅም የሌለው፣ በትግሉ ውስጥ የሚፈለገውን ለውጥ በትክክል

ማሣየት ያልቻለ፣ ከልክ በላይ ተስፋ ቆራጭነትና ባዶነት (Nihilism) የተጠናወተው ግጥም መሆኑንም መሞገት የሚቻል ይመስለኛል። አንዳንድ አስረጅዎችን እያጣቀስኩ ማስተንተኑን ልግፋበት።

"በረከተ መርገም"፣ በፈጠራ ስራቸው የተለየ ከበሬታ ያላቸውን ሳይንቲስቶችና ፈላስፎች ባልተለመደ ሁኔታ፣ ምናልባትም በተለየ "ድፍረት" የእርግማን በረከት ያወረደበት ወይም ግብራቸውን ያዋረደበት አቅም በራሱ የአድማጭን ወይም የአንባቢን ስሜት ሰቅዞ የመያዝ አቅም አለው፤ ይህን ሁሉ እርግማን፣ በተደላደለ የቋንቋ ጉልበት በተለየ ቅርፅ ማቅርቡ ደግሞ የታዳሚውን ቀልብ ከመግዛት አልፎ ኪናዊ ውበቱን አንድ ጠርዝ ላይ ያስቀመጠው ይመስላል። ለዚህ ደግሞ፣ "በእንክሮ ምጥቀት፣ ስናየው የኖርነው፤/ ሲነድ ሲቃጠል የሚስቅ እሣት ነው" የሚለው በአንጓዎቹ መሃከል በስልት የሚደጋገመው አዝማች ብቻ የሚናገረው መሪር እውነት ወኪናዊ ውበት አለ።

የግጥሙ ማዕከላዊ ጭብጥም ሆነ ይሄን ጭብጥ ለማግዘፍ የተጠቀመባቸው ማባያ ርዕሥ ነገሮች ከሃገራዊነታቸው ይልቅ አለማቀፋዊነታቸው ይጎላሉ። የግጥሙ ተናጋሪ የወጣበትን ዩኒቨርሲቲ፣ የወቅቱን ሃገራዊ ሁኔታ እና የዘመኑን መንፈስ እያናበብንና እያነፃፀርን ከመረመርናቸው፣ በአለማቀፋዊ ርዕሥ ነገሮች ውስጥ ሃገራዊው ተጨባጭ ጉዳይ በረቂቁም ቢሆን ይታያል፤ ይደመጣል፤ ለስሜት ይቀርባል። አስረጂ ልጥቀስ፤

ትግል ቅጥ እንዲያጣ፣ ተውሣክ የሆናችሁ፣
ኢምፔሪያሊስቶች፣ ኰሊኒያሊስቶች ደቂቀ ቾችሊ፣
ፋሽስቶች ሁላችሁ፣ (ገጽ ÷130)

እነዚህ ሁለት ስንኞች ብቻ እንኳ ስንመረምር፣ የትኛው ትግል ነው ቅጥ የሚያጣው? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ከዓለም አቀፍ ትግል የበለጠ፣ ለገጣሚው የራሱና በዙሪያው ያለው ትግል መነሻ ሊሆነው እንደሚችል መገመት ይቻላል። እናም፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ትግል ማንፀሪያ ያደረገ ይመስላል ቢባል ያስኬዳል። ምክንያቱም ዩኒቨርሲቲው በአሜሪካዊያን ተፅዕኖ ስር ወድቋል በሚል ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ጋር ሲጋጩ ቆይተዋል። አሜሪካ በቬትናም ላይ ያደረገችውን ወረራ ተቃውመው ሰልፍ ወጥተዋል። እንደውም "በረከተ መርገም" በቀረበበት መድረክ ላይ ሁሉ፣ ኢምፔሪያሊስቷ አሜሪካ ከቬትናም እንድትወጣ የሚጠይቁ መፈክሮች ተፅፈው ተለጥፈው ነበር፤ የቬትናም ዜጎችን ሥቃይ የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች እንዲሁ ለእይታ ቀርበው ነበር።

በርግጥ፣ "በረከተ መርገም" የሰው ልጅን በተለያዩ ማንፀሪያዎች እያስተነተነ በተለያዩ አስተሳሰቦች ወይም ፍልስፍናዎች ሲያዳክረው ይቆይና በመጨረሻም በሁሉም ነገር ተስፋ ቆርጦ፣ ሁሉንም ነገር አፍርሶ ባዶ አድርጐ ያስቀረዋል። አብርሆነት (enlightenment) ለቅኝቱ ማንፀሪያ መሠረት ቢሆነውም፣ ገቢራዊነቱን ሳያፀናለት አባክኖ አስቀርቶታል። ከመነሻው፣ ለዓለማችን፣ ታላላቅ ሥራ ያበረከቱትን ሲቃውንት ያን ያህል መራገም ለምን አስፈለገ? ብለን ስንጠይቅ፣

> የአንዲቷ ምድራችን ሲቃውንት ለሰው ልጅ ዘር ያበረከቱት ከፍተኛ የጥበብ ጸጋ ለሁሉና ለእያንዳንዱ እንዲደርስ አድርገው ያልፈለሰፉት ከሆነ በእኔ ግምት አሁንም ቢሆን፤ ሰዎችን ለመለያየት ያቀዱበት ተንኮል ነውና፤ ወንጀለኞች ናቸው ባይ ነኝ፤ ለዚህም ወንጀላቸው መረገም ሲያንሳቸው ነው (ገጽ፥ ረ)።

በማለት ገጣሚው በረከተ መርገም በሚለው መጽሐፋቸው መግቢያ ላይ ይመልሳሉ።

ግጥሙ፣ የተገጠመው በዚህ ጭራሽ ሲሞክር በማይመች የተሣሣተ ፍልስፍና (አይናለም /1972/ "ቅዠት" ብሎታል) መሠረት ላይ ነው። እዚህ ላይ ገጣሚው የተቃወሙት ቴክኖሎጂ ለሰው ልጆች በእኩል ያለመድረሱን ወይም ኢ-ፍትሃዊነቱን ይመስላል እንጂ ተጨባጩ ጉዳይ ቴክኖሎጂውን እራሱን ነው ማለት ይቻላል። በሌላ አነጋገር፣ አንድ ቴክኖሎጂ፣ ቴክኖሎጂ ሆኖ ለሰው ልጆች እስኪያገለግል ድረስ የሚያልፍበትን ሂደት ወይም የህልውናውን መሥመር ሁሉ አለመፍቀድ ማለት ነውና። ምክንያቱም፣ አንድ ጠቢብ፣ አንድ ቴክኖሎጂ ሲፈጥር እንዴት ብሎ ነው ለሁሉ እና ለእያንዳንዱ ማዳረስ የሚችለው? ጠቢቡ፣ በራሱ ማዳረስ ከቻለ ወይም ያዳርስ ከተባለ ሌሎች ሰዋዊ መዋቅሮች ሁሉ ይፍረሡ ማለት ነው? ወይም እያንዳንዱ ጠቢብ በፈጠረው ሥራ ባለቤቱ እሱ ብቻ ይሁን ማለትስ አይሆንም? እንደዚያ ካልሆኑ ከጠቢቡ ተቀብለው የማድረሱን ሥራ የሚወጡ ሌሎች መዋቅሮች ለምሳሌ መንግስትና ሌሎች ድርጅቶች ማስፈለጋቸው አይቀርም። አሁን እየሆነ ያለውም ይኸው ነው።

መንግስት ወይም ሌሎች አካላት ፍትሐዊ ሁነው ሊያዳርሱት ካልቻሉ ደግሞ መረገም ያለባቸው እነዚህ አካላት ናቸው። ጠቢቡም ለዚህ "ኢፍትሃዊ" አስተሳሰብ አሰራር ደጋፊ ወይም አስፈፃሚ ከሆነ በዚህ ጊዜ ሊረገም ይችላል። በሌላ በኩል አንድ ጠቢብ የፈጠረውን ሌላው ቁጭ ብሎ ሣይለፋ እንዲካፈል ማድረጉ ፍትሃዊነት ነው!? ከዚህ አንፃርም ከተወሰኑ ቀድመው ከተገኙ ጠቢባን እየተካፈለ ለአካባቢው ችግር መፍትሔ ከሚፈጥር ይልቅ ቁጭ ብሎ "የሚደድብ" ሰው መፍጠርስ አይሆንም!? ይሄ ደግሞ ዞሮ ዞሮ አዲስ የቴክኖሎጂ ውጤት እንዳይታይ፣ የተወሰኑ ጠቢባን "ፀጋ" ተደርጐ ብቻ እንዲታሰብ አያደርግም? የገጣሚው ማጠንጠኛ መሠረት ሀሣብ የዚህን ያህል የተሣሣተ ነው ማለት ይቻላል። ከግጥሙ የተወሰኑ ስንኞችን እየመዘዝን እንመልከት።

የግጥሙ ተናጋሪ፣ "አዎን፣ ነፃነትና ፍርድ፣ መብትና ሰላም፣ /ፈርጥጠው የመጡ፣ ናቸው ከሌላ ዓለም" እያለ፣ እነዚህ እረቂቅ ስሞች በመንግስተ ሰማያት መላእክት የሚገለገሉባቸው እንደሆኑ ወስኖ ይነሣል። በመቀጠል፣

በተፈጥሮ ያለው እውነተኛው ሕይወት፣ እንዳለ ካለበት፣
ኑሮአቸው ከዚያ ነው፣ መብትና ሰለም፣ ፍርድና ነጻነት
ምድራዊያን ናቸው፣ እያልን በማሰብ፣ በከንቱ እንዘብት።

በማለት እነ መብትና ሰላም ድሮም በመሬት ላይ ተግባራዊ እንዳልሆኑ፣ ወደፊትም እንደማይሆኑ፣ የግጥሙ ተናጋሪ፣ ሀልውናቸውን በከፍተኛ የጥርጣሬ በሽታ (skepticism) ቀስፎ ይዞ፣ በኋላም ምድራዊ መሆናቸውን ከነጭራሹ ይክዳል። ገጣሚው ይዞት የተነሣው ሀሳብ ከመነሻው ተግባራዊ ሊሆን የማይችል በመሆኑ፣ ያነሣውን የምጣኔ ሀብት ፍትሃዊነት፣ በራሱ የሀሣብ ምህዋር እንኳ በትክክል ሳያስከብረው እንደውም ሲያረክሰው ይታያል። የግጥሙ የመዝጊያ ስንኞችም፣

እኔስ በበኩሌ ከእንግዲህ ወዲያ፣ ሰው የተባለውን
ስሙን አላነሣም።
ለመርገም ተፈጥሮ፣ ተረግሞ ያለውን፣ መርገም ላይ መልሰው፣
ሁለተኛ አልረግምም።
የሆነው ሆኖ፣ እንደሆነ ይኑር፣ ለዓለም-ዓለም።
"በቃኝ"

በማለት ለኔ መብትና ሰላም የሚቆመውን፣ የሚታገለውን የሰው ልጅን ከንቱነት ይጠቁማሉ። የግጥሙ ተናጋሪ፣ የሰው ልጅ ለመርገም እንደተፈጠረ፣ የተረገመም እንደሆነ፣

መረገምም የማይመልሰውና የማይለውጠው እንደሆነ ስላረጋገጠ ለዘላለም "የሆነውን ሆኖ እንደሆነ" እንዲኖር ደመደመ። የፍትሐዊነት ጥያቄ አንስቶ የሞገተላቸው የዓለማችን ምንዱባን ሁሉ፣ ተመክሮ በማይመለስ የተረገመ ዓለም ውስጥ እንደተዘፈቁ ለዘላለም እንዲኖሩ እንደተፈረደባቸው አሣወቀ። "በረከተ መርገም" ከዚህ በኋላ የተማሪዎችን እንቆቅልሽ፣ አብዮት፣ ማርክሲስዝም፣ ሶሻሊዝም፣ መብትና ሰላም፣ ፍርድና ነፃነት ወዘተ. ለምን ያስፈልጋል? ለመሆኑ በምድር ላይ አሉ ወይ? ብሎ ስለመጠየቁ፣ ስመጠራጠሩ፣ ተስፋ ስለመቁረጡና ከነጭራሹ ባዶነት (Nihilism) የሠፈነበት ስለመሆኑ ደግሞ እኛ እናረጋግጣለን። እንደውም፣ የ"በረከተ መርገም" ጭብጣዊ መዋቅር በቁም (ባለበት ይዞታው) ሲፈከር፣ በጠራ፣ በበሰለ፣ የግጥም ቅርጽ በሚፈቅደው ምፀታዊነት በተዋጀ ውብ ቋንቋ፣ የትውልዱን ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም መሳከር፣ የሚያዘውና የሚጨብጠው ማጣት፣ ጥራዝነጣቂንት የሚመሰክር ግጥም ነው ማለት ይቻላል።

"ናስተማስለኪ" ጸገየ ወይን ገብረ መድህን

የጸገየ ወይን "ናስተማስለኪ"፣ ተለጣጣቂነትና ተከታታይነት ያላቸው የማይመስሉ የተለየዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በተለያዩ ማንፀሪያዎች እያጐላመሰ የሚተርክ፣ ቅኔያዊነት ጕልቶ የሚደመጥበት፣ ስከን ያለ ድምፀት ያለው ግጥም ነው። "ናስተማስለኪ" የሚለው የግጥሙ ርዕስ የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም "እንመስልሽ" ማለት ሲሆን፣ የግጥሙ ተናጋሪ፣ "ሰማሽ ወይ እናቴ ሰማሽ ወይ ቅድስት" እያለ የሚያናግራት፣ መልኳ ትልቅ መሣፍርት የሆነች፣ አንዳንዶች "መሰቦ ወርቅ ንጽሕት" ስለሚሏት የተቀደሰች እንስት ይተርካል። መገለጫዎቹን ስንመረምር፣ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም የሚናገር ይመስላል። ለግጥሙ ርዕስ የሆነው "ናስተማስለኪ" (እንመስልሽ) የሚለው ቃል ጋር እያወራረድን ነገረ ትርጓሜ ካረቀቅን ግን በድንግል ማርያም የተመሰለችው ኢትዮጵያ ልትሆን እንደምትችል እንገምታለን። የግጥሙ መነሻና መዝጊያ ላይም ሆነ መካከል ላይ ያሉት አንጓዎች የሚያነሱት ርዕሠ ጉዳይ ጠጣርነትና ሰምለበስ ወርቅነት ከድንግል ማርያም ሃይማኖታዊ ቀኖናዎች የሚረቁና ምናልባትም በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ተቀላቅለው መንግስታዊ ስርዓቱን የሚተቹ ስለሚመስሉ፣ "ሰማሽ ወይ እናቴ" የተባለችው ሃገረ ጦቢያ ትሆናለች ማለት ይቻላል። የግጥሙን መነሻ ስንኞች ዋቢ አድርገን፣ የገጣሚውን ማህበረ-ፖለቲካዊ ሂስ እንመርምር፤

የሚገለጥበት አሳብን አሳክቶ
መግጠም ቀርቷል አሉ በስድ ተተክቶ
ምንኛ ጅል ናቸው በጣምኑ ጅል
መግጠም ተቀረማ ሐረግ ይጠፋል፣ (ገጽ፥ 103)

የእነዚህን ስንኞች፣ ላዕላይ ፍካሬ ብንመለከት፣ የተሣካ ሀሳብ የሚገለፅበት የግጥም ጥበብ ተወግዶ፣ በዝርው ("በስድ") ፅሁፍ መተካቱ፣ "መግጠም"ን እንዲቀር ያደረጉት "ጅሎች"፣ መግጠም ከቀረ፣ ቃልና ቃል ማዋደድ ካልተቻለ፣ ቀጥሎ ያለውን ቋንቋዊ መዋቅር ("ሐረግ") ከነጭራሹ ሊጠፉም እንደሚችል ይጠቁማሉ፡፡ ታህታዊ ፍካሬ ስናደርግ ግን ዘመድ ከዘመዱ "እየገጠመ"፣ እየተዋደደ እና "ሐረግ" እየሣበ ለሥልጣን መብቃት ቀርቷል፤ የዘር ሐረግ መዋቅሩን ባልጠበቀና "በማይገጣጠም" አካል ("በስድ") መተካት ተጀምሯል በማለት የነገስታቱን ወገን የሚይሸሙሩ ይመስላሉ - ስንኞቹ፡፡ ጥርጣሬያችን ትክክል መሆኑን ለማስረገጥ፣ "እኔ ምን ተዳዬ ሐረጉ ቢጠፋ/ለተወዳሹና ላወዳሽ ታልከፋ፣" (ገጽ፥ 103) የሚሉት ተከታይ ስንኞች ከአውዱ ጋር አዋደን መመርመር ብቻ የሚበቃ ይመስላል፡፡ የግጥሙ ድብቅ ሀሳብ ተጠቅልሎ ያረፈው "ሐረጉ" እሚለው ቃል ላይ ነው፡፡ ይህ ኃይለ ቃል ለወርቁ ሀሳብ ተብሎ የገባ እንጂ ለሰሙማ (ለላዕላዩ ፍቺ) ብዙም አያስኬድም፡፡ "መግጠም" ሲቀር ከ"ሐረግ" ይልቅ "ስንኝ" ይጠፋል ቢባል ይመረጣል፡፡ በግጥም መዋቅር ውስጥ ከሀረግ የበለጠ ሰፊ ሀሳብ የሚሸከመው "ስንኝ" ነውና፡፡ የውክልና ጉዳይ ሲነሣም ትልቁ ትንሹን ቢወክል ወይም "ስንኝ" ሐረግን ተክቶ ቢገባ የመረጣል፤ አመክንዮዋዊም ነው፡፡ እዚህ ላይ ታዲያ የግጥሙ ተናጋሪ ሀሳቡን በግጥም ጥበብ ላይ ብቻ የወሰነ ቢሆን ኖሮ "መግጠም ከቀረማ ሐረጉ ይጠፋል" ከማለት ይልቅ፣ "መግጠም ከቀረማ [ስንኙ] ይጠፋል" ቢል ሊገልፀው የፈለገውን ጉዳይ እንደሚያሻሽለው አያውቅም ማለት ይከብዳል፤ ይልቅ ርዕሰ ጉዳዩ ስለ ዘር ሐረግ ማውጠንጠን ስለፈለገ "ሐረግ"ን ሆን ብሎ ተገለገለበት ማለት ይቻላል፡፡ እናም ግጥሙ፣ ከላይ ባስተነተንኩት መሠረት ማህበረ-ፖለቲካዊ ሂሱን በሰም ለበስ ቅኔ ማቅረብን እንደ ስልት ሆን ብሎ የተገለገለበት ይመስላል፡፡

ገጣሚው፣ "ናስተማስለኪ" ያላትን ሀገረ-ጦቢያን፣ በቤተ መቅደስ ወክሎ ሊሰግድላት፣ ማህሌት ሊቆምላት ሲሞክር ሰዎች የሚስተናገዱበት "መቆሚያ መተንፈሻ" እንደሌለ ይረዳል፡፡ "በወርቅ የተለበጥሽ ታቦት ነሽ ለሌላው /መቅደስ ለሚገባው ቅባት ለተቀባው" በማለት ያለውን መደባዊ ልዩነት ይጠቁማል፤ "ለሌላው" የሚለውን ቀደም ሲል "ሐረግ" ተብሎ ከተወከለው (ተመርጦ ከሚሣሣበው የዘር ሃረግ) ጋር ይቆራኛል፤ ይተካካል፡፡

የግጥሙ ተናጋሪ የተቀባ የዘር ሃረግ ስለሌለውና ወደ "መቅደስ" መግባት ስለማይገባው፣ በሌላ በኩል ጅል ሆኖ እስኪቆሳስል ሲሰግድ "እረፍ" የሚለው በማጣቱ፣

ከቶ እንዴት ይበለኝ ዝም ብለህ ስገድ
ጉልበቴ መቁሰሉን፣ አጥንቴ መግጠጡን ያላየልኝ ዘመድ፣
ባፍንጫዬ ይውጣ በታቦት ማመኔ
ነቀዝ ሲጨርሰው እያየሁት ባይኔ፣ (ገጽ፥ 104)

በማለት ከነበረው ሃገረ-ሃይማኖታዊ ተቋማት አፈንግጦ ይወጣል። እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ እናንሳ። የግጥሙ ተናጋሪ በአንድ በኩል "የተቀባ" ባለመሆኑ፣ በሌላ በኩል የተመረጠ የዘር ሐረግ ያለው ባለመሆኑ ቤተ መቅደስ ውስጥ እንኳ መግባት አለመቻሉ እየታወቀ፣ "ታቦቱን" ነቀዝ ሲጨርሰው ማየቱን ይመሰክራል። እዚህ ላይ ታዲያ ሊነገር የተፈለገው ጉዳይ ሌላ መሆኑን መጠርጠር ይገባል። ነገረ ሀሣቡ፣ የታቦቱን ትዕምርትነት ማስተንተኑ ላይ ነው። ግጥሙ፣ የሀሳብ ፍሰቱን ጠብቆ ከመውረድ ይልቅ፣ እንዲህ በየመካከሉ፣ በተለያዩ ተምሳሌቶችና ትዕምርቶች በተዋቀሩና የተለያዩ ርዕሠ ጉዳዮችን በሚያነሱ ቅኔያዊ አንጓዎች መገንባቱን መገንዘብና የተበታተኑ ትዕምርታዊ ቅኔዎች ከወዲያ ወዲህ እያገናኙ ማናበብ ያስፈልጋል።

በነገራችን ላይ፣ ገጣሚው፣ በግጥሙ የመነሻ አንጓ ላይ፣ በላዕላይ ፍቹ ግጥም መግጠም እንደቀረ ሲናገሩ፣ "የመገጣጠም ስልት ሲወገድ ታገር/የመሰናበቻ ስንኝ ልደርድር፣" የሚሉ የመግቢያ ስንኞች አስፍረዋል። እነዚህ ስንኞች ታዲያ፣ "ግጥሙ፣ የተለያዩ ቅኔዎችን፣ በተምሳሌት የተዋጁ አጫጭር ግጥሞችን በአንድ ላይ እያሰባጠርኩ ደርድሬበታለሁና በብልሃት አንብቡት" እያሉ ማንቃታቸው ይሆን? መጠርጠር ደግ ነው። "ናስተማስለኪ"፣ ከዘመን አቻው ከ"እስከ ማዕዜኑ" ጋር ሲነፃፀር፣ ልዩነቱ ያይላል፤ የኮሌጅ ቀን ግጥሞች በአንድ በተደራጀ መዋቅር፣ ለአንድ ዓላማ ተሰልፈው እንደነበር ተደርጎ ተጋኖ የሚወራውን ነገር፣ ጥያቄ የሚነሳበት ይመስለኛል። "እስከ ማዕዜኑ" ከ"በረከተ መርገም"ም ሆነ ከ"ናስተማስለኪ" የሚለይባቸው ነገሮች ይጐላሉ። እናብራራው።

"እስከ ማዕዜኑ" ዮናስ አድማሱ

የዮናስ "እስከ ማዕዜኑ" በርካታ ርዕሠ ጉዳዮችን ያነሣ፣ የተለያዩ ማህበራዊ መልኮችን ማዋሃ እያደረገ የሚያስተነትን ተራኪ ግጥም ነው። በዚህ ግጥም፣ የግጥሙ ተራኪ "ነፍስ"፣ ለእውነት ተስላ ቁማለች። ህሠተኞች፣ ፈሪዎች፣ ስሜታዊ ወጣቶች፣ ጥራዝ

ነጣቂዎች፣ የአፍ ሰዎች፣ ከእውነት፣ ስለ እውነት፣ በእውነት እንዲታነቁ ለፍርድ ተሰይማለች። በብዙዎች ስለ ዘላለማዊነቷ የሚነገርላት "ነፍስ"፣ እውነትን እንድትፈርድና እንድታፀና የተመረጠችበት አግባብ፣ በስነ መለኮት ማንፀሪያነት የምትፈከር ሰዋዊ ተቋምነቱን ታሣቢ ያደረገ ይመስላል፤ ይህ ከሆነ ደግሞ ፣ የግጥሙ ጭብጣዊ ጥልቀትም ሆነ ኪናዊ ውበት አንድም ከነባቢነቷ፣ ሁለትም ከልባዊነቷ፣ ሦስትም ከሕያዊነቷ ጋር በትይዩ እየቆመና እየተመዘነ የግጥሙ ነገረ ሃሳብ ጭምቅ ከመሆኑ ይመነጫል።

የግጥሙ ተናጋሪ፣ በገዛ ራሱ "ነፍስ" ላይ አድሮ፣ ማህበረ ተቋማትን የጠየቀበት፣ ስለ እውነት የተሟገተበት አካሄድ፣ ነገሮችን ከራስ አንፃር ማየትን ስለሚያነቃ፣ ወደ ራስ ውስጥ ለመመልከትም (introspection) እድል የሚሰጥ ይመስለኛል፤ ለዚህ ሳይሆን ይቀራል "እስከ ማዕዜኑ" ትውልዱ ጥራዝ ነጠቅ እንደሆነ በማጋለጥ ላይ የበለጠ አትኩሮ፣ በግልባጩ ትውልዱ እራሱን እንዲፈትሽ፣ እንዲመረምር መትጋቱና ማትጋቱ። እናም፣ የግጥሙ ተጋሪ ነፍሱን፣ "የሕጉን ቤት በይው የፍርድ ቤቱን/ ሲያከስል መኖሩን፣" ብለሽ ስለ ፍትህ እጦት ጠይቂ ማለቱ፣ "ንገሪው ገበሬን መጋቤ ፍጥረቱን/ጥሬን ብቻ ሳይሆን ፍራትን ማምረቱን፣" (ገጽ፥ 98) ብለሽ የገበሬውን ፈሪነቱን እንዲመረምር አንቂው ማለቱ፣ "ምን ሰራህ ተማሪው/ላገርህ አሳቢው፣" (ገጽ፥ 98) ብለሽ ተማሪው እራሱን እንዲጠይቅ አርጊው ማለቱ፤ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ወደራሱ እንዲመለከት ለመቃተቱ ዋቢ የሚሆኑ ይመስለኛል። የሚከተሉትን ስንኞች እንመርምር፤

ንገሪው አጽንተሽ ዳግም በጽሞና
ደሀ ገነት ገቢ ይሉት ፍልስፍና፣
ከንቱ የመነመነ ገባር መፈንገያ፣ (ገጽ፥ 97)

እነዚህ ስንኞች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጠቀምትን (Biblical Allusion) በብልሃት ነቃሽ አድርገው ትልቅ አቋመ ማህበርን (ሃይማኖታዊ አስተምህሮን) የሚኰንኑ አብዮተኛ ስንኞች ናቸው። የአብዮታዊነታቸው ሰይፍ የተመዘዘው ደግሞ በቤተ ክህነት ላይ መሆኑ እራሱ፣ ሂሱ ወይም ትችቱ ከማህበራዊነቱ የበለጠ ፖለቲካዊ ንጽረቱ እንዲያይል ያደረገው ይመስለኛል። ምክንያቱም፣ ስንኞቹ፣ የቤተክህነት ሰዎች፣ "እናንተ ድሆች ብፁዐን ናችሁ፥ የእግዚአብሔር መንግስት የናንተ ነውና" (ሉቃ፣ 6፥21) የሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል እያጣቀሱ ጭምር፣ ድሆች (ጭሰኞች) ለባለባቶቻቸው ስጥ ለጥ ብለው እንዲገዙ፣ የገባርነታቸውን ሰማያዊ በረከት እንዲያስቡ መሰበካቸውን በብልሃት ለማጋለጥ ተግቷል።

የስንኞቹ አብዮተኝነት የበለጠ ገኖ የሚወጣው፣ የሰላ ሂሳቸው ከተቋማቱ አልፈው መሠረተ እምነቱ ወይም ቃለ ሀይማኖቱ ላይ ጭምር ያነጣጠሩ መሆናቸው ሲታሰብ ነው። ዮሐንስ አድማሱ፣ "የዋሁ ገበሬ" በሚለው ግጥማቸው ውስጥ፣ "ይሰማል ሲሰበክ የክርስቶስ ትምህርት በሄደ ቁጥር፣/ ድሆች ብጹዕ ናቸው የሚባል ነገር።"[48] (እስኪ ተጠየቁ፣ ገጽ፥ 97) በማለት የቋጠሯቸውን ስንኞች ከዮናስ አድማሱ አብዮተኛ ስንኞች ጋር ማነበብ ይቻላል።

የመስፍን ሀብተማርያም "ስሞታ" ከዮናስ "እስከ ማዕዜኑ" በተወሰነ መልኩ የሚናበብ፣ በሰው ልጆች መካከል ያለውን የኑሮ ደረጃ በተወሰነ መልኩ የሚያናብብ፣ በሰው ልጆች መካከል ያለውን የኑሮ ደረጃ የሚያሳይ፣ የመሬት ለራሹን ጥያቄ የሚይስተጋባ፣ የድህነትን አስከፊ ገፅታ ማንፀሪያው አድርጐ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም የተቃኘ የእኩልነትጥያቄን የሚያራግብ፣ የግጥሙ ተናጋሪ በህልሙ የሄደበትን ሰፈር እና ያጋጠሙትን ድሆች፣ ጭሰኞች እያናጋረ በህልም የሚያስቆዝም ተራኪ ግጥም ነው (አባሪ "ሀ" እና "ለ" ይመልከቱ)።

ዮናስ "እስከ ማዕዜኑ" የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ውስጣዊ ማንነት ገላልጦ በማሳየት ከኮሌጅ ቀን ግጥሞች ሁሉ ብልጫ እንዳላው መመስከር ይገባል። የሚከተሉትን ስንኞች ለዋቢነት እንመልከት፤

ያንተ ዲሞክራሲ /ያንተ ማርክሲዝም/ያንተ ኮሚዮኒዚም

ማጆሪቲ ቮቲንግ፣ ኢንፎርሜሽን ኦርደር

ጨርሶ አይገባውም/ ለጀሌው ገበሬ፤ ለጀሌው ባላገር፤ (ገጽ 101)

....

ኧረ ወኔው የወጣቱ/ኧረ ፍሬው የትምህርቱ፣

ለምንድነው ባፉ ብቻ መፋፋቱ፣

[48] ተስፋዬ ገብረአብ፣ የደራሲው ማስታወሻ (2002ዓ.ም.) በሚለው መጽሐፍ ላይ "ያልተፃፈ መፅሃፍ" በሚል ርዕስ የዮሐንስ አድማሱ የቀድሞ ተማሪ የውሎ ማስተወሻ ጠቅሶ እንደሚከተለው አስፍሮታል፤ "... መንፈሳችን እስኪቃጠል ድረስ ገጣሚው ዮሐንስ አድማሱ ንቁ እንድንሆን አድርጎናል። አንድ ቀን ማለዳ በአንደኛው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ጋሽ ዮሐንስ ክፍል ውስጥ እንደገባ እንዲህ አለን፤ 'መጽሐፍ ቅዱስ ላይ 'ድሆች ብፁዓን ናቸው' የሚል ቃል አንብባችኋል? በሌላ ቦታ ደግሞ 'ላለው ይጨመርለታል' የሚል ሰፍሮአል። እስኪ እነዚህን መርምሩ? ዮሐንስ አድማሱ ይህን ብሎን ሲያበቃ ከእኛ ምላሽም ሳይጠብቅ በቀጥታ ወደ መደበኛ የማስተማር ስራው ገባ። በኔ በኩል የተቃጠለ ኮሚኒስት መሆን የጀመርኩት በዚህ ዕለት ሳይሆን አይቀርም... ጋሽ ዮሐንስ አንዲት ድንቅዬ ድንክ ቡና አይነት ውሻ ነበረችው። እሷን አስከትሎ ሲሄድ እስከ አሁን በአይኔ ላይ ይታየኛል" (ገጽ፥ 261)።

እነዚህ ስንኞች፣ የግጥሙ ተናጋሪ፣ የዘመን አቻ ጓደኞቹን (ተማሪዎችን) "ያንተ ዲሞክራሲ …" እያለ ያጣጥልባቸው እንደነበር ይገልፃሉ። ያንተ ማርክሳዊ ሌኒናዊነት ለገበሬው ምኑም አደለም፤ በቀላሉ ተናገርህም ልታስረዳው አትችልም እያለ፣ ተማሪው ከሃገሪቱና ከሃገረሰባዊው እውነቱ ጋር እንደተፋታ ያስተነትናል። ግጥሙ፣ ተማሪው ከማንነቱ ስረመሰረት (ከገበሬ ወገኑ) እንደማይተዋወቅ፣ ከሃገረሰባዊ ማንነቱ ጋር እንደማይናበብ እንዲሁም "ለሃገሩ ባዕድ እንግዳ" አይነት ባይተዋር (alienated) እንደሆነ ይጠቁማል። የትምህርቱ ፍሬም፣ ተማሪውን ከተግባሩ የሌለበት የአፍ ሰው እንዳደረገውና ጥራዝ ነጠቅነት መለዮ እንደሆነው ያመለክታል።

የዮናስ "እስከ ማዕዜኑ" የትውልዱን፣ በተለይ የተማሪውን መለዮ ባህሪያት ከጠቆመበት ማዕዘን ጋር ቁመን፣ በትይዩ የዳኛቸው ወርቁን አደፍርስ እና "እምቧ በሉ ሰዎች"፣ ዮሐንስ አድማሱን "ባይተዋር የሆነው ብቸኛው ወጣት" የሚሉትን ኪናዊ ሥራዎች ብቻ እንኳን እርስ በርስ እያናበብንና እያመሳከርን፣ የተማሪውን ጥራዝ ነጣቂነትና ባይተዋርነት አስረግጠን ማስተንተን እንችላለን። ዮናስ አድማሱ፣ በተማሪነታቸው ጊዜ ወደ ውስጣቸው ለመመልከት ቀድመው የነቁ በመሆናቸው ይሁን ወይም በኋለኛው ዘመናቸው ነገሮችን በሰከነ መንፈስ የማጤን እድል ስለ ገጠማቸው፣ እንኳ ብቻ፣ "የኔ ትውልድ በትንሹም ቢሆን ጥራዝ ነጣቂ የመሆን አዝማሚያ ነበረው። የንድፈ ሀሣቡም ይሁን የሚያቅዳቸው እቅዶች መሠረት በብዙው ድምፁን ያሰማለትና ደሙን ያፈሰሰለት ህዝብ እውነት"[49] መሆን እንዳልቻለና ተደናግሮ እንዳደናገረ መግለፃቸው፣ እስከ አሁን ከተተነተነው ጭብጥ ጋር በእጅጉ የሚናበብና የሚሠምር ይመስለኛል።

4.7 የ1960 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች ትንተና

በዚህ ክፍል የሚተነተኑ የ1960 ዓ.ም. አሸናፊ ግጥሞች፣ አንደኛ የጌታቸው ሰይፉ "አርአስት የለሽ ቅኝት"፣ ሁለተኛ የዓለማየሁ ዓለምነህ "በማር ተለውሶ"፣ሦስተኛ የመስፍን ሀብተማርያም "ፍለጋ" ሲሆኑ፣ አራተኛ ደረጃ ወጥቶ የተሸለመው የተክሉ ሚናስ "እርባዕተ ፀሐይ" ግን ተፈልጐ ባለመገኘቱ በዚህ ጥና አልተካተተም (ዝርዝር መረጃውን በሚመለከት፣ በምዕራፍ ሦስት የ1960 ዓ.ም የዩኒቨርሲቲውን ተማሪዎች እንቅስቀሴና የግጥም ውድድሩን ዳራ የሚያስቃኘውን ክፍል ይመልከቱ)።

---

[49] ጦቢያ (7ኛ ዓመት፣ ቁ.3፣ ጥቅምት፣ 12 ዓ.ም.) ላይ ይመልከቱ።

የዚህ ዓመት ግጥሞች ከ1959 ዓ.ም አሸናፊ ግጥሞች ጋር ሲነፃፀሩ ደረጃቸው ዝቅ እንደሚል፣ ገጣሚዎች በወቅታዊው ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በአንፃራዊነት ጠንከር ያለ ሂስ እንዳቀረቡ፣ Strugel (Vol. II, NO. 3, 1963: 3) የተማሪዎች ጋዜጣ ዘግቧል። በርግጥ ግጥሞቹ ማህበራዊ ሂሣቸው ጐላ ብሎ ቢታይም፣ ከማህበራዊ ሂሱ ጋር ተሸርቦ፣ አንዳንድ ጊዜም በግልፅ ደርጅቶ የቀረበው ፖለቲካዊ ምልከታና እና ስልታዊ ትችት ቀላል እንዳልሆነ በዚህ ጥናት ተረጋግጧል። የገጣሚያኑ የትኩረት አቅጣጫ፣ የርዕሠ ጉዳይ ምርጫና ለጭብጣቸው ማቀንቀኛ የተከተሉት ቅርፃዊ ማዋቀሪያ ሲመረመሩ፣ ልዩነቶች (difference) ጐልቶ ይታይባቸዋል።

"አርእስት የለሽ ቅፃት" ጌታቸው ሰይፉ

ይህ ግጥም፣ የግጥሙ ተናጋሪ እርሳሱን አውጥቶ ሲሞነጫጭር ሲታትር፣ እንቅልፍ ይዞት እንደሄደና ወዲያው ቅፃት እንደጀመረው ይተርካል። የግጥሙ ተናጋሪ፣ በቅፃቱ ውስጥ በርካታ ማህበራዊ መስተጋብሮች እና ሰዋዊ እውነቶች የሚያረቁ ርዕሠ ጉዳዮችን ያነሣል። የተነሱት ርዕሠ ጉዳዮች በርከት ቢሉም ሁሉም በአንድ መነጽር እየታዩ በማህበረ መዋቅሩ ውስጥ ያላቸው ደረጃ ተሰፍሮ ተመላክቷል። ሁሉንም ጉዳዮች በአንድ መነጽር እየታዩ በ"እውነት" ማንፀሪያነት እየተፈተሹ ተገልፀዋል። በግጥሙ ውስጥ፣ የሃገራት (የነ ራሽያ፣ የነ አሜሪካ) እውነት፣ የ"ዲሞክራት" እና "የሶሻሊስት" እውነት፣ የዩኒቨርሲቲዎች እውነት፣ የእንስሳቱ እውነት፣ የሃይማኖት ተቋማቱ እውነት፣ የእግዚአብሔር እውነት፣ የተለያዩ የህበረተሰብ ክፍሎች (የሴት አዳሪዎች፣ የሰካራሞች፣ የደላሎች...) እውነት ተጠይቋል። በነዚህ ማህበራዊና መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ የሰው ልጅ "እውነትን" እንዴት ብሎ እንደሚረዳ፣ "እውነት" በራሷ ያላት ሰፊና ተለዋዋጭ ገፅታ በተለያዩ ማንፀሪያዎች እየተብራራና እየተጐላመሰ ተወስቷል። በእነዚህ ሰዋዊ ተቋማት ውስጥ ያለችውን "ተለዋዋጭ እውነት" መፈለግ፣ ለግጥሙ ተናጋሪ "ቅፃት" ሆኖበታል፤ የተቋማቱ ወይም የርዕሠ ጉዳዮቹ መብዛት አርእስት ለመስጠትም አስቸግሮታል፤ ከገቢራዊ ጭንቀቱ የተፈጠረው ይህ ቅፃት በርግጥ "አርእስት የለሽ ቅፃት" ሆኖበታል። የተወሰኑ "ቅፃቶችን" በማስረጃ እናስተንትን።

> እንዲህ ስል ጀመርኩኝ
> አትቃዥ አልባልም ልቃዥ መብት አለኝ
> ቅፃቱን መናገር ማሣደም አይደለም
> ወይ ሰላማዊ ሰልፍ ፖሊስ የሚያደክም (ገጽ፥ 147)

እነዚህ ስንኞች በጥንቃቄ ስናነባቸው፣ በተለይ ከ1959 ዓ.ም. ከዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ዳራ ጋር ካናበብናቸው የሚናገሩት መሪር ፖለቲካዊ እውነት አለ። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ነግሶ የነበውን የፍርሃት ድባብ በለሆሳስ ይጠቁማሉ። የግጥሙ ተናጋሪ፣ ተኝቶ የቃዠውን "እውነት" እራሱ ተጠራጥሮታል። "አትቃዥ አልባልም ልቃዥ መብት አለኝ" የሚለው ስንኝ፣ የመቃዠትን "መብት" ሲነሣ፣ እንዳይቃዥ የሚያስገድድ ነገር እንዳለ በስተጀርባው ይነገራል። ደግነቱ ብዙ ሳንመራመር ቀጣዮቹ ስንኞች ፍርሃቱንና ስጋቱን በግልፅ ያሳብቁበታል። "ቅዠትን መናገር ማሳደም አይደለም" እያለ፣ "አሣድመሃል" ተብሎ እንዳይጠየቅ፣ ከወዲሁ "ሊያስጠይቅ የሚችል" ያለውን የሰላማዊ ሰልፍ ጉዳይ ማንፀሪያ አድርጐ ይከላከላል፤ እራሱን የማዳን ስራ ይሰራል። የዚህ ፖለቲካዊ ምፀት መራርነቱ የሚመነጨው፣ ሰዋዊ መብት የሆነውን ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ጉዳይ፣ መብትነቱ ሆን ተብሎ ተነፈጐ ወይም "ተክዶ"፣ ሊያስጠይቅ እንደሚችል ተደርጐ ከተገለፀበት እንቆቅልሽነቱ ይመስለኛል።

የገጣሚው ጭንቀት (የጌታቸው "ቅዠት") ውስጣችን ድርስ ዘልቆ የሚሰማን፣ የኮሌጅ ቀን ገጣሚውን ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ ጨምሮ፣ ተማሪ አሣድማችኋል የተባሉ፣ በዩኒቨርሲቲው የፋሽን ትርኢት (የሚኒስከርት) ሣቢያ በተነሣ ብጥብጥ ላይ ተሳትፋችኋል የተባሉ፣ በመጋቢት ወር 1960 ዓ.ም. በሮዴዥያ (ዛሬ ዜምባቡዌ) የነበረውን የIan Smith ቅኝ አገዛዝ በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ በወጡ፣ ተማሪዎች ላይ የደረሰው ድብደባ፣ እንግልትና እስራት ከታየበትና ከተመዘገበበት ከዩኒቨርሲቲው ወቅታዊ አውድ (contemporary context) ጋር እያገናኘን ስናነብበው ይመስለኛል።

> ግን እውነት ብትሰርቂ አምጾሽ ብተሸፍቺ
> ብትዋሽ ብትቀጥፊ ብትጨቁኚ ሰዎች
> ለማን አቤት ይሏል፣ ለዩኒቨርሲቲያችን ወይስ ላጥቢያ ዳኞች? (ገጽ፥152)

የሚሉት አይነት ለዘብ ብለው የቀረቡ፣ "የእውነትን" መራርነት የሚያነፅሩ ስንኞች፣ የያዙት መልዕክት ግዝፈቱና የግጥሙም ማዕከላዊ ጭብጥ ጥልቀቱ የሚታወቀው፣ ከተገጠሙበት አውድ አንፃር እየተናበቡ ሲፈከሩ ይመስለኛል። የጌታቸው "አርእስት የለሽ ቅዠት" ከዮናስ "እስከ ማዕዜኑ" ጋር ይናበባል፤ በተለይ ሁለቱም ግጥሞች "እውነት"ን የርዕስ ጉዳያቸው አስኳል አድርገው ከመጠቀማቸው አንፃር ከላዕላይ ተቃርኗቸው ውስጥም ቢሆን፣ ታህታይ ጭብጣዊ ምስስሎሽ እንደሚኖራቸው ይታወቃል።

"በማር ተለውሶ።" ዓለማየሁ ዓለምነህ

የዓለማየሁ "በማር ተለውሶ"፣ የግጥሙ ተናጋሪ በወከላቸው እንስሴ ገፀባህሪያት የሚከናወኑ ድርጊቶችን በቅደም ተከል የሚያቀነቅን ተራኪ ግጥም ነው። የግጥሙ ተናጋሪ፣ "ምሬትን ደብቆ በማር ተለውሶ/ቅርጽን በመለወጥ ድምፅን አለሳልሶ" (አባሪ "ሐ"፣ ገጽ፥ 1) እያለ የበግ ለምድ የለበሱ ሀሰተኛና አስመሳይ የሰው ተኩላዎችን ባህሪ ያስቃኛል። ቀጥሎ፣ "እስቲ ያየሁትን ልናዘዝ ቢቀለኝ" (ዘኒከማሁ፣ገጽ፥ 1) በማለት ስራፊቶ ሲጓዝ ካረፊበት የንቦች ከተማ የታዘበውን ይተርካል። ትንግርት የሚሠኝ ስልጣኔ በተመለከተበት በንቦች "ዐይነ ብልጥ" ከተማ፤ ነጋሪት ሲጐሰም፣ ዝማሬ ሲዘምር፣ እንቢልታ እየተነፋ ሆታና እልልታው ሲቀልጥ ያያል። ምክንያቱን ሲያጣራ ንቦች፣ ለ"ዝንብ መሪ" አቀባበል ሲያደርጉ እንደሆነ ይመለከታል። ግጥሙ፣ "በተዋዋሉት ውል ባደረጉት ፊርማ/ የዝንቦቹ መሪ እንዲህ ሲል ተስማማ" (ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ፥ 2) በማለት የዝንቦቹ መሪ ተናግሮ ሳያበቃ፣ የንባቹ መሪ፣ "ዝንብን ለማሰልጠን ታጥቀን ተነስተናል/ ሥራው እንዲፈጥን ፕላን አቅደናል" (ገጽ፥ 3) በማለት መግለጫ ማውጣቱን ግጥሙ ይተርካል።

በመቀጠል "የንብ ኤክስፐርቶች" ከዝንቦች ጋር ተባብረው ማር ማምረት ጀመሩ። "አስተዋይ ዝንቦች" ከንቦች ጋር ዝምድና እንደማያዋጣ፣ "መንፈስ ደካማ በሽተኞች ሁነን/ በገዛ ሀገራችን ባይተዋር እንዳንሆን" (ገጽ፥ 4) በማለት ቢመክሩም ተቀባይነት አጡ። ከዚያም የግጥሙ ተራኪ፣ "ንቦችም አጋዡ ያገሩን ጥሬ ሀብት/ ለንብ መጐልመሻ እንዲውል ለልማት" (ገጽ፥ 5) ይልና ዝንቦች ብጥብጥ ማንሳታቸውን ይተርካል። ብጥብጡ እየጠነከረ እንደሄደ፣ ንቦችም ማስጠንቀቂያ እንዳስተላለፉ፣ ሆኑን የጣሱ ዝንቦችም በሞት እንደተቀጡና በኋላም ዝንቦች ለተባበሩት "የትንኞች ሸንጐ" ክስ ቢያቀርቡም፣ ውጤት እንዳልተገኘበት፣ የዓለማየሁ ግጥም ያትታል።

"በማር ተለውሶ" አሊጐራያዊ ግጥም ነው (ብርሃኑ፣ 1999፥ 321 ላይ ዝርዝሩን ይመልከቱ)። "አሊጐሪያዊ ታሪክ [ደግሞ] ሁለት ፍቺዎች አሉት" (ብርሃኑ፣ 1999፥ 322)። ላዕላይ ፍቺው የገጣሚው ዋና ጉዳይ እንደማይሆን ይታወቃል፤ የንባቹና የዝንቦቹ መስተጋብር፣ በርዕሠ ጉዳዮች ደረጃ "ፋይዳ-ቢስና ፍሬከርስኪ" ነው። የሚፈለገው ሁለተኛው በአንባቢው ግንዛቤ የሚረቀው፣ የአንድምታ ፍቺ ነው። የሀሳብ ታሪክን የሚያጠና የምርምር ሥራ፣ ለአንድምታው ፍቺ "እውነተኝነት" (የዘመን መንፈስ ጠቋሚነት) የበለጠ መጨነቅ አለበት። እናም፣ የአንድምታ ፍቹ በአንፃራዊነት የተሻለ የሀሳብ ታሪክ እንዲናገር፣

የግጥሙን አሊጎሪያዊ ታሪክ ከወቅታዊው ሁነቶችና አውዶች ጋር እያቀናጁ መመርመር ያስፈልጋል። ስለዚህ፣ የዓለማየሁ ግጥም በስልጣኔ ያደጉት ምዕራባዊያን ሃገራት፣ በድህነት ከሚማቀቁ "ኋላ ቀር" ሃገራት ጋር ምሬታቸውን በማር ለውሰው፣ ተለሳልሰውና አስመስለው ስለታዊ ግንኙነት እንደሚጀምሩና በኋላ ላይ አንባገነን ቅኝ ገገሮች እንደሚሆኑ ለማስረዳት መታተሩን መገመት አይከብድም።

ከአሊጎሪያዊው "በማር ተለውሶ" የአንድምታ ፍቺ የበለጠ ለመቀራረብ በምዕራፍ ሦስት ላይ ከተባረሩት (የወቅቱ የተማሪዎች እንቅስቃሴና የዩኒቨርሲቲው አውድ) ማንፀሪያዎች ጋር እያገናኙ መመርመሩ ይጠቅማል። ከ1954 ዓ.ም. ጀምሮ እየከረረ የመጣው ተማሪዎች በአሜሪካ ጣልቃ ገብነት ላይ ያላቸው ጥላቻ (በጥር ወር 1960 ዓ.ም. የአሜሪካ ምክትል ፕሬዝዳንት ንግግር እንዳያደርጉ፣ የፕሬዝዳንቱ ምስልና የሃገሪቱን ባንዲራ እስከ ማቃጠል መድረሳቸውን ልብ ይሏል።)፣ በመጋቢት ወር 1960 ዓ.ም. የሮዴዥያ (ዝምባቡዌ) ክIan Smith ቅኝ አገዘዝ ነፃ እንድትወጣ (በ1959 ዓ.ም. የኮሌጅ ቀን በዓል ላይ የሮዴዥያን ቅኝ አገዛዝ የሚቃወሙ የተለያዩ ስራዎች መስራታቸውን ልብ ይሏል።) የአፍሪካ አንድነት ድርጅትንና የእንግሊዝ ኤምባሲን መጠየቃቸው ለአሊጎራዊ ፍቺ ማናበቢያ ወሳኝ መረጃዎች ናቸው። በነዚህ መረጃዎች ማንፀሪያነት፣ "የንቦች ቅኝ አገዛዝ" ታሪክ፣ "የIan Smith ቅኝ አገዛዝ" ታሪክ ነው ብሎ መናገር አያሳፍርም።

ገጣሚው ዓለማየሁ፣ ነፃነቷን እንድታገኝ እየተሟገትንላት፣ እየተደበደብንላትና እየታሰርንላት ያለችው ሮዴዥያ፣ እንዲህ ከገነነ የቅኝ አገዛዝ ማጥ ውስጥ የገባችው፣ የIan Smith መንግስት ሰላማዊ መስሎ፣ እየተቅለሰለሰ ከተግባባት በኋላ፣ ቀስ በቀስ ሥር እየሰደደ በመምጣቱ ነው ብለው አስበዋል፤ ከማሰብም አልፈው ጥርጣሪያቸውን ለዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ በዚህ አሊጎሪያዊ ግጥማቸው እንደ ኢየሱስም በምሳሌ ሊያስተምሩ (ሊሰብኩ) ሞክረዋል። በርግጥ፣ ስጋታቸውና የማንቂያ ደወላቸው የመነጨው ሮዴዥያ እጣ ፈንታ አሣስቧቸው አይደለም። ይልቁንም፣ በዩኒቨርሲቲያቸው ውስጥም ሆነ በአጠቃላይ በሃገራቸው ውስጥ፣ የአሜሪካ ጣልቃ ገብነት፣ ኢኮኖማያዊ ጠቀሜታዋ ላይ የተመሰረተውን ፖለቲካዊ የበላይነት፣ ወደ ለየለት ቅኝ አገዛዝ ውስጥ እንዳያስገባት አሳስቧቸዋል፤ አስግቷቸዋልም። ሙያዊ እገዛ ለመስጠት፣ ገንዘብ ለመርዳት የፈቀደችው ያለነገር አይደለም፤ በማር የተለውሰ መራራ ፖለቲካዋን ልትጭንብን ነው እንጂ ይላሉ። ገጣሚው፣ የአሜሪካ እርዳታና፣ ሙያዊ እገዛ፣ "በማር ተለውሶ" የቀረበ መራራ ወረራ እንዳያስከትል ከወዲሁ ይታሰበበት የሚሉ ይመስላሉ። ሊያሰርውት ለፈለጉት ንቃተ ህሊና

ደግሞ በንብና በዝንብ መንግስታት ማስተንተኛነት የሮዴዥያን የቅኝ አገዛዝ አሊጎሪያዊ ታሪክ ለመተርክ መትጋታቸውን ለብ ሊባልላቸው ይገባል።

የዓለማየሁ "በማር ተለውሶ"፣ ተማሪዎቹ ወደ ውስጥ እንዲመለከቱ የማትጋት ሚና ሁሉ አለው፤ ቬትናም እና ሮዴዥያ ከአስከፊ ቅኝ አገዛዝ ነፃ እንዲወጡ ትሟገታለችሁ፣ ትጮኻላችሁ፤ በጐን ግን፣ አሜሪካ በማር የተለወሰ ስልታዊ ግንኙነት መስርታ እናንተው እራሳችሁ ቅኝ ተገዢ ልትሆኑ መቃረባችሁን አልተረዳችሁትም የሚል የሰላ ሂስ ይሰነዝራል (ሃገረሰባዊው ፍልስፍና "የራሷ እያረረባት፣ የሰው ታማስላለች" እንዲል)። እዚህ ላይ፣ የግጥሙ ተራኪ፣ "የዝንብን መሪ" እጣ ፈንታ ካስተነተነ በኋላ "የትንኝ ሽንጐ" ሳይበተን፣ ጣልቃ ገብቶ፤

> ነገሩን ሰማችሁ የሆነውን ሁሉ
> እንዳይደርስባችሁ ተው እግዚኦ በሉ (ገጽ፥ 5)

በማለት ለታዳሚው ያስጠነቀቀበት ብልሃት እስከ አሁን ላስተነተነው ጉዳይ ዋቢ የሚሆን ይመስለኛል። በነገራችን ላይ፣ በግጥሙ ውስጥ "የዝንብ መሪ" ሥልጣኔ ላልገባቸው እንደ፣ ሮዴዥያ ላሉ ደሃ ሃገራት ወካይ ተምሳሌት መሆኑ ግልፅ ነው። ግጥሙ፣ ኢትዮጵያን የቅኝ ተገዢነት ስጋት እየገጠማት ነው የሚል የጐንዮሽ ወይም የሰያፍ ጭብጥ ማርቀቁም ቀደም ብሎ ተተንትኗል። ስለዚህ፣ "የዝንብ መንግስት" የኢትዮጵያ መንግስት፣ "የዝንብ መሪ" የኢትዮጵያን መሪ መወከሉ አይቀሬ ጉዳይ ባይሆን ጥሩ ነው፤ ለእኛም አይቀሬ ከሆነ ግን "ዝንብን" ሃገረሰባዊ ተግባቦት ከፈቀደላት "ተምሳሌትነት" ወይም ፎክሎሩ ካሸከማት ሰፊርተኛ ርዕዮተ ዓለም ነጥለን ልንመለከታት ይገባል፤ አለበለዚያ፣ የግጥሙ ታህታይ ጭብጥ፣ "በማር ተለውሶ" ቢቀርብም፣ መራርነቱ ሁላችንንም ሃገር አስከዶ እንዳያስኮበልለን ያሰጋል፤ "የላላውን ወጥረን" ከፈከርነው የግጥሙ ጭብጥ የዚህን ያህል ጥልቅ ሊሆን ይችላል፤ የተፈጥሮዋ "ዝንብ" እና የፎክሎር "ዝንብ" መካከል ያለው ልዩነትም ጥልቅ ነውና፤ "ፎክሎራዊው ዝንብ" ማለት [እኮ] ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ "በረከተ መርገም" ውስጥ፣

> አዎን፤ አንቺ ያገሬ ዝንብ፣ የሰይጣን ንቢቱ፣
> ከጥንት ጀምሮ አዳሜ ሲሰድብሽ፣ ያላግባብ በከንቱ
> ሙያሽን ሳያውቀው፣ ያላንዳች ምክንያት፣ እንዲያ
> ሲጠየፍሽ በደነዝ ስሜቱ፣
> አንች ግን በውነት፣ ለውነት ስትይ፣ ሀሞትሽን ኮስትረሽ፣ ስለኖርሽ በድካም፤
> የሀገር ጭነትን የብሔር ሸክምን የወገን አላልን፤ አርጋጁን፤ አንጋጁን
> ለማጥፋት ለማውደም፣
> ጠንቃዊ ነፋሳቱን፣ ጀርሙን ትላትሉን፣ ከዳሪ ወደ ቤት፣ ስታመላልሽ፣
> ለፈጸምሽው ጀብዱ፣
> አምላክ ተመልክቶ፤ በኪነ ጥበቡ፣ ሳምሶንን ያርግሽ፤ በለጋስ ልማዱ።።

(<u>የኮሌጅ ቀን ግጥሞች</u>፣ ገጽ 133) በማለት "ያወደሳት ዝንብ" መሆኗም አይደል? ይህ ሁሉ ርዕሡ ነገር የተነሣው፣ የሃገር መሪ ሳይቀር በ"ዝንብ" እስከመመሰል የደረሰው፣ ሃገራዊ

"ድህነት" የፈጠረው ቁጭት ይመስላል፤ ድህነቱን መራር ያደረገው፣ ከቁሳዊነቱ ይልቅ መንፈሳዊነቱ ላይ በማየሉ እንደሆነ በየግጥሞቹ ተጠቁሟል፤ በኮሌጅ ቀን ታሪክ የመጨረሻው አሸናፊ ግጥም፣ ለድህነታችን መፍትሔ "ፍለጋ" ላይ አትኩሯል፤ መፍትሔው ምን ይሆን?

"ፍለጋ" መስፍን ሀብተማርያም

የመስፍን "ፍለጋ" በርካታ ርዕሠ ጉዳዮችን ያነሣ፣ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ዲያሌክታዊ ቁሣካል መርህ የተቃኘ፣ በአብዛኛው በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን መደባዊ ልዩነቶች ከዘላቂ የኢኮኖማ አቅም አንፃር እየመዘነ፣ የዝቅተኛው ህብረተሰብ ክፍል ገመና ለማጋጥ የሞከረ ግጥም ነው። "ፍለጋ" የፊውዳሉንና የጭሰኛውን የኑሮ ልዩነት ማሄጃ አድርጐ ስለመናገር መብት እጦት፣ ስለ ደሀው ግፍና መከራ፣ ጭቆናና ሰቆቃ ይሟገታል። ለችግሩ መውጫ የሚደረገው የመፍትሔ "ፍለጋ"ም፣ የማያቋርጥ ዲያሌክቲክሳዊ የትግል እንቅስቃሴ እንደሚያሻው ይቀሰቅሳል፤ ግጥሙ "ፀሎተኞች ሁሉ፣ በያላችሁበት አድምጡ በቅጡ/ ሰላም አትለምኑ፣ በፊት ሳይሰጠን፣ እንጆራና ወጡ" (አባሪ "መ"፣ ገጽ፥ 6) በማለት አብዮታዊ ለውጥ መሻቱን አስተጋብቷል፣ የመስፍን ግጥም፣ እንደ ዮናስ "እስከ ማዕዜኑ" ትውልዱ እራሱን እንዲመለከት፣ ጥራዝ ነጣቂውን ትውልድ በሰላ ምፀት ይወርፋል፤ "ዘመናይ ወጣቶች፣ ለፓርቲው እስክስታ፣ ሁሌ ስትንጋጉ/ መፍትሔው ሽክላው ላይ ተለጥፎ እንደሆን ምነው ብተፈልጉ" አይነት ሽንቋጭ ስንኞችን በመደርደር።

የመስፍን "ፍለጋ"፣ "በማር ተለውሶ" ያተኮረበትን አሊጐሪያዊ የቅኝ ግዛት ሕይወት እንዲወገድ ብዕሩን ሰብቆ በፊት ለፊት ይሟገታል፤

በተፈጥሮ መዘዝ፣ በቆዳቸው መጥቆር፣ ልዩ እየተባሉ
ዛሬም ባለማችን፣ በባርነት ቀንበር የሚሰቃዩ አሉ።
በሮዲዢያና በደቡብ አፍሪካ፣ ይታያል ተገልጦ
በደም የሰከረው ነጫነጩ ጌኛ ጥቁሩን ተፈናጦ። (አባሪ "መ"፣ ገጽ፥ 9)

በማለትም በጥቁሮችና በነጮች መካከል የተፈጠረው አስከፊ የዘር መድሎ፣ የሰውነት መንጠፍን (dehumanization) ሁሉ እንዳስከተለ፣ "በደም የሰከረው ነጫ ነጩ ጌኛ ጥቁሩን ተፈናጦ" እያለ በተለዋጭ ዘይቤ አሽሙሮታል። ግጥሙ፣ "ፍለጋ"ው የደረሰበት የመጨረሻ መፍትሔ ደግሞ ከብዕር ውጊያ፣ ወደ ጠብመንጃ ውጊያ መሸጋገር ያስፈልጋል የሚል ይመስላል። እነዚህን ስንኞች እንመልከት፤

ታዲያ አንድነቶቹ ምነው ችላ አላችሁ፣ ምነው ዝም አላችሁ
የሥጋችሁ ቁራጭ፣ ድረሱልኝ ብሎ ሁሌ ሲጠራችሁ።
....

ማውገዝ ማውገዝ ብቻ ማውገዝ ምን ጠቀመ፣ ማውገዝ ምን ጨመረ
መጣፉ እንደሚለው፣ ሰይጣንም ተወግዟል፣ ሥራው መቼ ቀረ፡፡
ይህን አጉል ማውገዝ፣ ወዲያ ጣል አርጉና ይልቅስ ተነሱ
ትጥቅን አሟሉና፣ ለዛ ቅዱስ ጩኸት በፍጥነት ድረሱ፡፡ (አባሪ "መ"፣ገጽ፥ 9)

እነዚህ ስንኞች፣ በመጋቢት ወር 1960 ዓ.ም. ተማሪዎች ሮዴሽያ ነፃ እንድትወጣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን መጠየቃቸውን ያስታውሱናል፡፡ "ታዲያ አንድነቶቹ ምነው ችላ አላችሁ" እያሉ ቅኝ ግዛትን ከማውገዝ ያለፈ፣ መብታቸውን ለማስከበር በ"አንድነት" አለመታገላቸውን ይተቻል፤ መፍትሔውም የትጥቅ ትግል ነው ይላል፡፡

ይህን መፍትሔ፣ ቅኝ አገዛዝን ለማስወገድ ብቻ አይደለም የተመላከተው፤ ለኢትዮጵያ አጠቃላይ ችግር በዋናነት ተጠያቂ ያደረጉትን የአፄውን ባላባታዊ ስርዓት ለማስወገድም፣ መፍትሔው ጠብመንጃ ማንሳት (መጋደል) እንደሆነ ተጠቁሟል፤

ለጌቶቹ ግብር፣ በግፍ ለመዋሏ፣ ያችው ያመረተካት
ተሁሉም ተሁሉም፣ ደሳሳዋ ጐጆህ፣ መቼም ምስክር ናት
....
ይህ አልበቃ ብሎ፣ በብልጦች ስያሜ ጭሰኛ ተብለህ
ከምታገኛት ላይ፤ ለራስህ ሳትጠግብ፣ ላለው ትሰጣለህ፡፡
ገበሬ አታመንታ፣ ከቶ ጊዜ አትስጠው፣ ለዚህ ታላቅ በደል
መፍትሔ ፍለጋ፣ ተስፋህን አትቁረጥ፣ በጽኑ ተጋደል፡፡ (አባሪ "መ" ገጽ፥ 10)

እነዚህ ስንኞች፣ ተማሪዎች ያነሱትን ሥር ነቀል የ"መሬት ላራሹ" ጥያቄ ያጐላሉ፡፡ "ጭሰኛ" እየተባለ ያመረተው ለ"ጌቶቹ" እንዲሰጥ የተገደደውና እየተሰቃየ ያለው አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል፣ ከስቃይህ ለመገላገል ተስፋ አትቁረጥ፤ መፍትሔው በእጅህ ነው ያለው፤ እያሉ ይቀሰቅሳሉ፡፡ መፍትሔው ጠብመንጃ እንስቶ በፅናት መታገል እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ፣ ጥናቱ የዳሰሳቸው ዋና ዋና ነገረ ሀሣቦች ተጨምቀው እና የጥናቱን ዓላማ (ዝርዝር መሪ ጥያቄዎችን) እንዲመልሱ ተደርገው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ይህ ጥናት ከመነሻው፣ ከ1951-1960 ዓ.ም. በውድድር አሸንፈው በ"የኮሌጅ ቀን" በዓል ላይ የቀረቡ ግጥሞችን መርምሮ፣ በዋናነት፣ የገጣሚያኑን ማህበረ ፖለቲካዊ አመለካከታቸውን እና ሂሣዊ ስልታቸውን ማስተንተን ላይ ብቻ ሊያተኩር አስቦ ነበር። በጥናት ሂደቱ፣ በአንድ በኩል፣ ለትንተና የተመረጡትን ግጥሞቹ ባሰባሰበው የኮሌጅ ቀን ግጥሞች መድበል ውስጥ ተሟልተው አለመገኘታቸው፣ የተገኙትም ቢሆኑ ሙሉ በሙሉ "የኮሌጅ ቀን" በዓል ላይ ስለ መቅረባቸው እንኳ አለመረጋገጡና አንዳንድ የተጣረሱ መረጃዎች እንዳላቸው መታወቁ፤ በሌላ በኩል፣ ገነው የሚታወቁትን የኮሌጅ ቀን ግጥሞችና የገጣሚያኑን መረጃዎች እንኳ፣ በተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች፣ መፃሕፍትና በተለያዩ ወቅታዊ የመረጃ ምንጮች ላይ ተዛብተው ሲገለፁ ማጋጠሙ እና ግጥሞቹን አንብቦ ለመረዳትም ሆነ ለማስተንተን ከወጡበት ዘመን ወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር እያናበቡ መመርመር እንደሚያስፈልግ መታወቁ፣ "የኮሌጅ ቀን" በዓልን ታሪካዊ ዳራ እና የገጣሚያኑን ሚና መፈተሽ ጥናቱ የጠየቀው የማይታለፍ ጉዳይ ሆኗል፤ ስለዚህ ታሪካዊ ዳራቸውን መመርመር የጥናቱ አንዱ ዓላማ ነበር።

በ"የኮሌጅ ቀን" ገጣሚያኑ ላይ የተደረገው ይህ ጥናት፣ የስነ ጽሁፍ ታሪክ (Literary history) እና/ወይም የሀሳብ ታሪክ (history of ideas) ላይ ስለሚያተኩር የገጣሚያኑና የዩኒቨርሲቲያቸውን ዳራ በጥንቃቄ ለመመርመር ተሞክሯል። በዚህም፣ የግጥም ውድድሩ፣ በወቅቱ የተማሪዎች መማክርት መሪዎች በነበሩት በነአስፋው ዳምጤ አነሳሽነት በ1951 ዓ.ም. መጀመሩ እና እስከ 1960 ዓ.ም. ውድድሩ መቀጠሉ (ከ1960 ዓ.ም በኋላም እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ የተለያዩ ግጥሞች በትግል መሣሪያነት ይቀርቡ ነበር፤ "የየካቲቱ ገጣሚ" /የዮሐንስ አድማሱ/ ግጥሞችን ልብ ይሏል)፣ በ1957 ዓ.ም. የኮሌጅ ቀን በዓልም ሆነ የግጥም ውድድሩ ስለመደረጉ ምን ፍንጭ አለመገኘቱ፣ የኮሌጅ ቀን ግጥሞች መድበል የኢብሳ ጉተማንና የጸገየወይን ገብረመድህንን ግጥሞች፣ የ1957 ዓ.ም ውድድር አሸናፊ አድርጐ ማቅረቡ ስህተት መሆኑ ወዘተ. በዚህ ጥናት ተረጋግጧል።

በተጨማሪም፣ በሁሉም የውድድር ዓመቶች አሸናፊ የነበሩ ገጣሚያን፣ የግጥም ርዕሶቻቸው (በ1955 ዓ.ም. ካሸነፉ ሁለት ግጥሞች በቀር) እና አሸናፊ የሆኑበት ደረጃቸው (Rank) የቀዳማይ የመረጃ ምንጮችን (primary source) በመመርመር ታውቋል፤ በ1959 እና በ1960 ዓ.ም. ካሸነፉና ከተሸለሙ ግጥሞች ውስጥ <u>በኮሌጅ ቀን ግጥሞች</u> መድበል ያልቀረቡ ሦስት ግጥሞችን አጥኚው አፈላልጐ ከማግኘቱ በተጨማሪ በዚህ ጥናት ተመርምረውና ተረጋግጠው ለመተንተን በቅተዋል። በገጣሚያኑ ወይም በግጥሞቹ ማዕከላዊ ጭብጥ ላይ ከሚፈጥሩት ተፅዕኖ አንፃር እየተመዘኑ፣ በኮሌጅ ቀን በዓል፣ በተማሪዎች እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም በሌሎች በዩኒቨርሲቲው እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተከሰቱ አንኳር ሁነቶች፣ ከሃገር አቀፍ ማህበረ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ጋር በትይዩ እየተናበቡ ተጨምቀው ቀርበዋል። በዚህም፣ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ማህበራዊ መልካቸው የጐሉ ሀሳቦችና ድርጊቶች፣ እያደር ከረረ ያሉ የፖለቲካ ጥያቄዎች እየሆኑ መምጣታቸውን አጥኚው፣ ተመልክቷል።

ለዚህ ጥናት የመነሻና የመድረሻ ርዕሠ ጉዳይ የሆኑት ግጥሞች፣ በትክክል "የኮሌጅ ቀን" ግጥሞች መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ፣ ላነሷቸው ሀሳቦች ትኩረት ተሰጥቶ፣ ጭብጣዊ ትንተና (thematic analysis) ተደርጐባቸዋል። ግጥሞቹ ያላቸው ሚና ታውቆም በወጉ ለመተንተን እንዲቻል፣ ግጥም እንደ ትግል መሣሪያ፣ ግጥም እንደ ገጣሚዎቹ ዳራ እና ግጥም እንደ ርዕዮተ ዓለም ማቀንቀኛ ያለው ድርሻ፣ በባለሙያዎች ንድፈ ሀሳቦች ማንፀሪያነት ተቃኝቷል።

ግጥሞቹ ሲተነተኑ፣ ገጣሚያኑ በርካታ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ርዕሠ ጉዳዮች ማንሳታቸው ተረጋግጧል። የገጣሚያኑ ማህበራዊ ሂሶች፤ በሰው ልጅ ባህሪ፣ በማህበራዊ መስተጋብሩ በሚያሳያቸው ፀባይ፣ በስነ ምግባራዊ ጉዳዮች፣ ገነው በወጡ ሃገራዊ እምነቶችና ሃይማኖታዊ ስርዓቶች፣ በአጠቃላይ ሰውነት ወይም ሰዋዊነት በሚሞግቱ ማህበራዊ ፍልስፍናዎች ላይ አተኩረዋል። የማህበራዊ ሂሶቻቸው ጥልቀት፣ ገጣሚዎቹ እራሳቸውን እና ዘመነኛ ትውልዳቸውን ከጠየቁበትና ከገመገሙበት ማዕዘን ጭምር ሲመዘን እንደሚችል በጥናቱ ተወስቷል።

ገጣሚያኑ ካነሷቸውና ፖለቲካዊ መልካቸው ከሚጐላባቸው ርዕሠ ጉዳዮች ውስጥ በዋናነት፣ ሀሳብን ስለ መግለፅ ነፃነት እጦት፣ በጭሰኛውና በከበርቴው መካከል ስላለው የተራራቀና ኢፍትሃዊ የሆነ የኑሮ ልዩነት፣ በመልካም አስተዳደር እጦት ሳቢያ ሃገሪቱ

ስለምትዳክርበት እስከፊ ቁሣዊና መንፈሳዊ ድህነት ላይ ማተኮራቸውን የትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡

ገጣሚያኑ፣ ፖለቲካዊ ጭብጦቻቸውን በማህበራዊ ሂሶቻቸው ውስጥ ለማርቀቅ የሞከሩበት ስልት በየግጥሞቻቸው ጉልቶ ታይቷል፤ ግጥሞቹ በላዕላይ ፍቻቸው፣ ማህበራዊ ሂሣቸው ጉልቶ ቢታይም፣ ታህታይ ፍቻቸው ሲመረመር ግን የገጣሚዎቹ ሰበበ ማቀንቀኛ ፖለቲካዊ ርዕሠ ነገሮች እንደሆኑና የአንዳንዶቹ ግጥሞች አሊጎሪያዊ ቅርፃችም (ለምሣሌ፡- የ1960 ዓ.ም. አሸናፊው "በማር ተለውሶ"ን ልብ ይሏል) ከዚህ ጉዳይ ጋር እንደሚናበቡ ጥናቱ አመላክቷል፤ የግጥሞቹ ኪናዊ ውበትና ታዋቂነት፣ የገጣሚያኑን ፖለቲካዊ አመለካከትና ንቃተ ህሊና መሠረት ከመደረጋቸው ላይ እንደመነጨ ይታሰባል፤ ለምሳሌ፣ ቤተክህነት፣ የባላባታዊ ሥርዓቱ አድራጊ ፈጣሪ እንደሆነች ተደርጐ በሚታሰብበት ሃገራዊ አውድና የዘመን መንፈስ ውስጥ፣ በቤተክህነት ላይ ያነጣጠረ የሰላ ሂስ ከማህበራዊነቱ ይልቅ ፖለቲካዊነቱ እንደሚያመዝን እና በዚህ የፍካሬ ማዕዘን ሊታይ እንደሚገባ፣ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

ግጥሞቹ፣ ያነሷቸው ሀሳቦች እድገት፣ ከዓመት ዓመት እየጠነከረ በመጣው ፖለቲካዊ ጭብጦቻቸው ላይ ጉልቶ ታይቷል፤ በ1951 ዓ.ም.፣ የሰው ልጅ ውስጠት የተመረመረበትን ፍልስፍናዊ ጭብጥ በማቀንቀን ጀምረው፣ በ1960 ዓ.ም. ለሃገሪቱ ፖለቲካዊ ችግር መፍትሔው የትጥቅ ትግል እንደሆነ እስከ መግለፅ መድረሳቸው በትንተናው ክፍል ተብራርቷል፡፡

ማህበራዊና ፖለቲካዊ ርዕሰ ጉዳዮችን ማንፀሪያ ባደረገው በዚህ ጭብጥ ተኮር ትንተና (thematic analysis) በግጥሞቹ ውስጥ አንድ አይነት ገጽታዎች (patterns) እንዳለ ተስተውሏል፡፡ ግጥሞቹ በቅርፃቸው እረገኘዥም፣ በርዕሰ ጉዳይ አቀራረባቸው ዘርዛሪና በአብዛኛው ተራኪ መሆናቸው ታውቋል፡፡ ገጣሚያኑም እንደ ስልት ይሁነኝ ብለው ያድርጉት አያድርጉት በዚህ ጥናት ማረጋገጥ ባይቻልም፤ ከሃገር፣ ከመሪ፣ ከሥርዓቱ ጋር ያለመተዋወቅና ግራ የመጋባት ብሎም ባይተዋር (alienated) የመሆን አዝማሚያ (በተለይ ወደ መጀመሪያዎቹ ዓመታት) ታይቶባቸዋል፡፡ በኋላም፣ በሃገራቸው፣ በመንግስታቸው፣ በዩኒቨርሲቲያቸው አመኔታ እስኪያጡ መጠራጠር (skepticism) ተስፋ መቁረጥ (despairing)፣ ሁሉንም ነገር መቃወምና አለመፈለግ (Negation)፣ ያሉትን ነገሮች ሁሉ የመካድና እንደሌሉ አድርጐ የመቁጠር ፅንፈ ባዶነት (Nihilism) እንደ ጐላባቸው ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል በአንድ የውድድር ዓመት ባሸነፉ ገጣሚያን መካከል የማህበራዊ ሂስ ስልታቸውንም ሆነ ፖለቲካዊ አመለካከታቸውን የሚገልፁበት መንገዳቸው ከተመሳሳይነታቸው (similarity) ይልቅ፣ ልዩነታቸው (difference) እንደሚጐላ፤ ለምሣሌ፣ አንደኛው ገጣሚ ሞቅ ባለ ድምፀት (tone) የፖለቲካ ስርዓቱን ሲተች፣ ሌላኛው ገጣሚ ቀዝቀዝ ባለ ድምፀት የተማሪዎችን ጥራዝ ነጣቂነት፣ ግልብነት ወዘተ. ላይ ማህበራዊ ሂሱ ይሰላል፡፡ የአንዱ ግጥም፣ በተማሪዎች እንቅስቃሴ ጐልቶ የወጣውን ጥያቄ (ለምሳሌ "መሬት ላራሹ"ን) ደግፎ ሲሟገት፣ ሌላኛው በጋለ ስሜት፣ "ማርክሲስት"፣ "ኮሚኒስት" ነን የሚሉ "አብዮተኛ" ወጣቶችን በፅኑ እንደሚተች ጥናቱ ተመልክቷል፡፡

በአንድ መድረክ ላይ ተከታትለው የቀረቡ ግጥሞች የተቃረኑ ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለሞችን እና ማህበረ ፖለቲካዊ ጥያቄዎችን ማቀንቀናቸውን በማጤንና በሌላ በኩል ከገጣሚዎቹ ዳራ የተገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ፤ ገጣሚያኑ ግንባር ቀደም "አብዮተኛ" እንደነበሩ፣ በተማሪዎች እንቅስቃሴ "አራማጆች"ም ሆነ በሌላ በተደራጀ ቡድን አማካይነት ይሁነኝ ብለው "በግጥም" ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለምን ለማስረፅና የባላባታዊ ሥርዓቱን ግፍና በደል ለማጋለጥ እንደተጠቀሙበት ተደርጐ ተጋኖ መወራቱና በአንዳንድ ጥናቶችም ጭምር (ለምሣሌ፣ ግርማ 1976) መገለፁ፣ በበቂ መረጃ የተደገፈ እንዳልሆነ፣ (አንዳንድ ገጣሚያን በተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥም ሆነ በሌሎች መድረኮች ያሳዩት የነቃ ተሳትፎ እና "ቁርጠኝነት" በግላቸው እንጅ በአንድ በተደራጀ ኃይል ውስጥ ሆነው እንዳልነበረ ይናገራሉ[50]) ግምት ተወስዷል፤ በዚህ ርዕሠ ጉዳይ ተጨማሪ ጥናት ቢደረግ የተለየ ውጤት ሊመዘገብ እንደሚችል ጥናቱ ማመላከት ፈልጓል፡፡

በመጨረሻም፣ እንደ ዮናስ አድማሱ ያሉ የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች፣ ሥነ ጽሑፋዊ ጥናትና ምርምር ጥያቄ ማጫር (ማርቀቅ) እንዲችል ይመከራል ያሉትን ምርኩዝ አድርጌ፣ ይህን ጥናት ስሰራ በአእምሮዬ የተመላለሱብኝን ጥያቄዎች በማቅረብ ርዕሠ ጥናቱን አጠቃልላለሁ፤

---

[50] እሁድ የካቲት 10 ቀን 1960 ዓ.ም. ከወጣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ፣ "የኃይሉ ገብረ ዮሐንስ 'ጸለምተ እስራኤል' ብሎ የሰየመው … ብዙ ሰው የሚገኝበት የተቋም ድርጅት ለማስመሰል መሆኑ የምርመራው ክፍል በተጨባጭ ገልጿል … ይህ 'ድምፀ ድራጐል' የተባለው ድርጅት ልብ ወለድ ከመሆኑ በቀር፤ ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ የፈጠረው ፈጽሞ የሌላ የሐሰት ድርጅት መሆኑን ፖሊስ በተጨማሪ አብራርቷል" የሚለውን እና "የአዞዎቹ" ቆራጥ ታጋይ የሚባሉት ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ እራሳቸው፣ "… ያኔ በጣም የሚደንቀኝ ነገር፥ ትምህርት እናቁም ይሉና በጓዳ በር ተመልሰው የሚማሩ ልጆች ናቸው፡፡ በኋላም አንዳንዶቹ ፕሮፌሰር ተብለው መኮፈሳቸውን ሰምቼ፥ ዕፁብ አልኩ" በማለት ሥር ነቀል ለውጥ ፈላጊ የሚባሉት ተማሪዎች ሳይቀሩ አንድነት እንዳልነበራቸው፣ ከእማኝ (ቁጥር 1 መስከረም 1986 ዓ.ም.) መጽሔት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ የገለፁትን ልብ ይሏል፡፡

1. በሁሉም የኮሌጅ ቀን ግጥሞች በቀጥታም የሁን በእጅ አዙር፣ በጥቆማም ይሁን በማብራሪያ ሀሳብን ስለመግለጽ ነፃነት እጦት፣ “ምላሴን ተውልኝ” እያሉ በአፅንኦት መወትወታቸውና ይህን ጥያቄ እንኳ አጉልተው የገለፁበት ነፃነት (ንጉሱን በፊት ለፊት እስከማናገር የደረሱበት ድፍረት) ምንና ምን ናቸው? ብዕሮቻቸው ማንን ማንፀሪያ አድርገው ነበር የሚንተገተጉት?
2. ከኮሌጅ ቀን ገጣሚያን መካከል፣ በተለየ ሁኔታ አንድ ገጣሚ በየጊዜው በሚወጡ መጽሐፍት ውስጥ የተለያዩ አዳዲስ (በብዙ መልኩ ቀድሞ የተገኘ የዛ ትውልድ አባል መሆኑን የሚያረጋግጡ የሚመስሉ) መረጃዎች ይዘክሩለታል፤ ለምሳሌ በዚህ ዓመት (2002 ዓ.ም.) እንኳ በባህሩ ዘውዴ አርታኢነት፣ <u>Documenting the Ethiopian Student Movement: An Exercise in Oral History</u> (2010) በሚል ርዕስ ከሁለት ወር በፊት በወጣው መጽሐፍ እና ሰሞኑን በውጭ ሃገር በታተመው፣ የተስፋዬ ገብረአብ፣ <u>የደራሲው ማስታወሻ</u> (2002 ዓ.ም.) መጽሐፍ፣ ስለ ገጣሚው የገለፁትን አዳዲስ መረጃዎች ብቻ ዋቢ ማድረግ ይቻላል፤ በርግጥም፣ “የየካቲቱ ገጣሚ” ዮሐንስ አድማሱ (“ሰውዬው”) ማን ነው?

ዋቢዎች

አማርኛ

ሳህሉ አክሊሉ (1992)፤ "በሰምና ወርቅ ቅኔያዊ አሳጥሮ መረዳት በኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡ አቤ ጉበኛና ዮሐንስ አድማሱ ቅኔዎች ላይ"፤ *የቋንቋዎች ጥናት ተቋም አስራ ሁለተኛው ዓመታዊ ጉባኤ*፤ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ገጽ 59-81።

ቃለ ክርስቶስ አባይ (1997)፤ *የ1953ቱ የመንግስት ግልበጣ ሙከራና ከ1908-1966 ዓ.ም የኢትዮጵያ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ሂደት*፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ።

